

«የትልልቅ ህንፃዎች መሰራት ከከተማ ውበት ባሻገር እድገት እንዲመጣ አስተዋፅኦ አበርክቷል»

- ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል ዋተሮ

ገጽ 6

ቅድመ ስኳር በሽታ (Pre-diabetes)

ገጽ 8


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 337 ነሐሴ 7 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




ሶስተኛው ዙር የታላቁ ህዳሴ ግድብ የውሃ ሙሌት በስኬት ተጠናቀቀ

## ከዓባይ ውሃ በሚገባቸው ልክ መጠቀም እንዳለባቸው የማያምኑ ሃይሎች የተፈጥሮን ሕግ እያዛቡ እንደሆነ ተገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ከአባይ ውሃ በሚገባቸው ልክ መጠቀም እንዳለባቸው የማያምኑ ካሉ የተፈጥሮን ሕግ ያዛባሉ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በትናንትናው ዕለት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁን አስመልክቶ ባደረጉት የእንኳን ደስ አላችሁ ንግግር፤ የፈጣሪ ስጦታ የሆነውን የዓባይ ወንዝን በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ለዓባይ 85 በመቶ የሚሆነውን ውሃ

ከዓባይ ውሃ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት




## «የግድቡ ትርጉም ኃይል ከማመንጨት በላይ ኢትዮጵያውያን እንችላለን የሚለውን የሚያሳይ ነው»

- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ኃይል ከማመንጨት በላይ ኢትዮጵያውያን እንችላለን የሚለውን የሚያሳይ ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት

«የግድቡ ትርጉም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ስፖርት ኮሚሽን

## አንጸባራቂው ወጣት የአትሌቲክስ ቡድን አቀባበል ተደረገለት

**ብርሃን ፈይሳ**

ለስድስት ተከታታይ ቀናት በኮሎምቢያ መዲና ካሊ ሲካሄድ ቆይቶ ባለፈው እሁድ በተጠናቀቀው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ተሳትፎ አንጸባራቂ ድል ያስመዘገበው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ልኡካን ቡድን ወደ አገር ቤት ተመልሷል። ቡድኑ ትናንት ምሽት ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሲደርስ በከፍተኛ የመንግሥት የስራ ሃላፊዎችና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አመራሮች የጀግና አቀባበል ተደርጎለታል።

በአቀባበል ሥነሥርዓቱ ላይ የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ ቀጄላ መርዳሳ፣ የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ እንዲሁም ሌሎች የስፖርቱ ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች የተገኙ ሲሆን ለልኡካን ቡድኑ የአበባ ጉንጉን አበርክተዋል። "ወጣት አትሌቶቻችን እንኳን ደህና መጣችሁልን" በማለት በአቀባበል ሥነሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት ሚኒስትሩ ቀጄላ መርዳሳ "እንኳን ደስ አለን፣ ወርቅ እየዘነበ ነው ዝናብም እንደዛው፣ ውሃም እየሞላ ነው፣ በሁሉም መስክ ድል በድል ሆነናል" ሲሉ

አንጸባራቂው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


Maldives Promotion
SIGNAGE & PRINT
For all your signage & printing needs with well-established workshop & machineries
CNC cutting & engraving machine
Foam board, Aluminum panel, MDF...
Laser cutting & engraving machine
Mica, Leather, Fabric ...
UV flat bed for give away items
Pen, Flash disk, Notebook ...
Digital T-shirt & Fabric printer
High quality Digital printer
Roll up, sticker, reflective, transparent...
Heat press machines
Cap, Mug, Mask, Plate
And exhibition stand & event stage construction
Fast and Quality Service
+251 911 253 076 / +251 984 872 919
maldivespromotion@gmail.com
Shola, on the Main Road to British Embassy



EFDA
የኢትዮጵያ ምግብ መድኃኒት ባለስልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY



አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ጋይልብ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


ገጽ 4

## «ዓባይ አሁን ላይ ለኢትዮጵያ ወሳኝ የልማት አቅም ሆኗል»

- አቶ ደመቀ መኮንን
የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር



# አራት ባንኮች ከወለድ ነጻ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው ተገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አራት ባንኮች ፈቃድ ወስደው ከወለድ ነጻ የሆነ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው ተገለጸ።

አገር አቀፍ ከወለድ ነጻ የፋይናስና ኢኮኖሚ ጉባኤ "አካታች የፋይናንስ አገልግሎት በኢትዮጵያ ውስጥ ተደራሽ ማድረግ" በሚል መሪ ቃል ከትናንት በስቲያ በሸራተን አዲስ ሆቴል በተካሄደበት ወቅት የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሽዴ እንደገለጹት፤ በፋይናንሱ ዘርፍ የተደረጉ የማሻሻያ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሙስሊሙን ማሕበረሰብ ያማከለ የፋይናንስ አገልግሎት ለማስፋፋት የባንክ ስራ አዋጅ ከወለድ ነጻ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጎ መሻሻሉ፣ የመድን ስራ አዋጅ የተካተተበት አገልግሎት እንዲሰጥ መፈቀዱ፤ ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ አነስተኛ የማክሮ ፋይናንስ እንዲቋቋሙ መሰረታዊ የሆኑ ሶስት የሕግ ማሻሻዎች ተደርገዋል ብለዋል።

ለማሻሻያ ስራው አንዱ ማሳያ የሆነው የሙስሊሙን ማሕበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ አሰራር መዘርጋት ነው ያሉት አቶ አሕመድ፤ ለዚህም ባለፉት አራት ዓመታት በተሰራው ተግባር አራት ባንኮች ፈቃድ ወስደው ከወለድ ነጻ የሆነ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። 11 ባንኮች ደግሞ ከወለድ ነጻ የመስኮት አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

በፋይናንስ ዘርፉ ለውጡን ተከትሎ የተሰሩ ተግባራት ለአገር ብልጽግና፣ ለፋይናንስ ዘርፉ መስፋፋትና እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ የሸሪያ



አቶ አሕመድ ሽዴ

መርህን በመከተል አካታች የሆነ የፋይናንስ ሥርዓትን ለመዘርጋት በጥናትና ምርምር የተደገፈ ስራ መሰራት እንዳበት ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ከወለድ ነጻ አገልግሎቱ አንድ መቶ 17 ቢሊዮን ብር በላይ ብር ተቀማጭ ሆኗል ብለዋል። ከወለድ ነጻ አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ 3 ተቋማት ያሉ ሲሆን ሶስት የሚሆኑት ደግሞ ወደ ስራ ለመግባት በሂደት ላይ ናቸው። እስካለፈው ሰኔ 30 ድረስም 4842 ከወለድ ነጻ የሆኑ ሂሳቦችን በመክፈት የሰጡት ብድር 35 ቢሊዮን ብር ደርሷል።

የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ሰለሞን ደስታ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በዓለም ላይ ነጻ የፋይናንስ አገልግሎት የሚንቀሳቀሰው የገንዘብ መጠን ሁለት ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር ደርሷል። በዚህም ተጠቃሽ የሆኑት እንግሊዝና ኬንያ ናቸው። በኢትዮጵያም ባለፉት አራት ዓመታት በተሰራው የሪፎረም ስራ ነጻ የወለድ አገልግሎት ለመስጠት በአራት ባንኮች መደበኛ አገልግሎት የተጀመረ ሲሆን በ11 ባንኮች ደግሞ የመስኮት አገልግሎት እየሰጡ ነው። ከወለድ ነጻ አገልግሎት ላይ ለሚከናወነው ስራ ባንኩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር መሐመድ እድሪስ፤ ነጻ የፋይናንስ አገልግሎት የዳያስፖራው የረጅም ዓመታት ጥያቄ መልስ ያገኘበት ነው። የፋይናንስና የኢኮኖሚ ጉባኤ በተለያዩ ዓለማት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በአገራቸው የኢኮኖሚ ተጠቃሚ በሚያደርጉ መስኮች ተሳታፊ እንዲሆኑ ትልቅ እድል ነው። በተለያዩ የዓለም አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በአገር እድገትና ብልፅግና ላይ አሻራቸውን ማሳረፍ አለባቸው። በተለይም የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግ ገንዘባቸውን በአገር ውስጥ ተቀማጭ ማድረግና በዘርፉ ተሳታፊ እንዲሆኑ አሳስበዋል።

ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ በበኩላቸው እንደተናገሩት፣ በጋራና በቅንጅት ለአገር መስራት በሚያስፈልግበት ወቅት ይህ ነጻ የፋይናንስ የኢኮኖሚ ጉባኤ አስፈላጊ ነው። ጉባኤው ከኢድ እስከ ኢድ መርሃ ግብር ላይ ተሳታፊ የሆኑ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም በውጭ አገር ያሉ ሙስሊም ማሕበረሰብ በኢትዮጵያ ያለውን የፋይናንስና የኢኮኖሚ አማራጮች ማስተዋወቅና የሥርዓቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑና በአገር ልማት ላይ የበኩላቸውን እንዲወጡ ያለመ ነው።

# በአንጋፋው ፕሬስ የተጣደው የእውቀት ማዕድ

**ጌትነት ምህረቴ**

የሚዲያ ሚና እውነት ላይ ተመስርቶ ትክክለኛ፣ ተዓማኒና ወቅታዊ መረጃዎችን በማቅረብ ሕብረተሰቡ በቂ መረጃ እንዲኖረው ማስቻልና ሕዝቡ የሚያነሳቸውን ማናቸውንም ጥያቄዎችና ሃሳቦች መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት አውቀው ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ነው። ለዚህ ደግሞ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችን አቅም በየጊዜው እያሳደጉ መሄድ ይጠይቃል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ላለፉት ሰማንያ ሁለት ዓመታት በህትመት ዘርፍ ለሕብረተሰቡ መረጃ በማቀበል የኖረ እና በርካታ ታላላቅ ደራስያንን ጭምር ያፈራ የሀገሪቱ አንጋፋ የሚዲያ ተቋም ነው።

ተቋሙ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ ደግሞ አጠቃላይ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ዘርፈ ብዙ ለውጦችን በማድረግና በሕብረተሰቡም ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ የሚዲያ ተቋም ነው። በአሁኑ ወቅትም ከሕትመት ውጤቶች ባሻገር ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በኦንላይን ሚዲያው አማካኝነት ለሕብረተሰቡ ትክክለኛና ፈጣን መረጃዎችን በመስጠት ላይ ይገኛል።

ተቋሙ ይህንን ስኬት ይበልጥ ለማጎልበት እና የተቋቋመለትን ዓላማ በስኬት ለመፈፀም ሙያዊ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት እየሰራ ይገኛል። ከነዚህ ሙያዊ የውይይት መድረኮችም ውስጥ አንዱ የአርታኢያን መድረክ ነው።

ሀሙስ ነሀሴ 5 ቀን 2014ዓ.ም በተቋሙ የመሰብሰብያ አዳራሽ በተካሄደው የአርታኢያን መድረክ በኢፕድ ስር በሚታተሙ የጋዜጦች ዜና ላይ ያሉ ጠንካራ፣ ደካማ ጎኖችና የመፍትሄ ሃሳቦች ፤ የተቋሙ የሪፎርም ስራዎችና ያስገኛቸው ውጤቶች፣ እንዲሁም የፊቸር ስራዎች ያሉበት ደረጃ የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ሶስት የጥናት ጽሁፎች ቀርበው በተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል።

በኢፕድ የጋዜጦች ዜና ላይ ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የተዳሰሱበትን የጥናት ጽሁፍ ያቀረቡት በድርጅቱ የኦንላይ ሚዲያ ዋና አዘጋጅ አቶ አርአያ ጌታቸው ናቸው። የኢፕድ ጋዜጦች በተዓማኒነት፣ በተደራሽነት፣ በተጽእኖ ፈጣሪነትና በሌሎች ሚዲያዎች በምንጭነት ከመጠቀስ አንጻር በተጨባጭ የሚጠቀሱ አመርቂ ውጤቶች መገኘታቸውን ገልጸዋል።

አሁንም ተነባቢ የሆኑ የዜና ትንታኔዎች፣ ሀተታዎችና


ፎቶ - ዳኜ አበራ
የአርታኢያን መድረክ

የዕቅድ ስራዎችን በመስራት ረገድ ብዙ ስራ የሚጠይቅ በመሆኑ ሊተኮርበት ይገባል። ለዚህም አቅሙ እንዳለ ከዚህ በፊት በተሰሩ ጠንካራ የዘገባ ስራዎች በተጨባጭ ታይቷል። ይህን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል ብለዋል።

የተቋሙ የሪፎርም ስራዎችና ያስገኛቸው ውጤቶች በተመለከተ ጥናት ያቀረቡት የዘኢትዮጵያን ሔራልድ ዋና አዘጋጅ አቶ ወርቁ በላቸው በበኩላቸው እንዳሉት፤ በይዘት ዘርፍ በተለይም በጋዜጦች ላይ ከአሰራር ጀምሮ የተደረገው የማሻሻያ ሥራ በተለይ ተጽእኖ በመፍጠር ረገድ ትልቅ ለውጥ ማምጣት አስችሏል።

ይህንን ለውጥ ተከትሎ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስር በሚታተሙ ጋዜጦች ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ጨምሮ፣ አምባሳደሮች፣ ታዋቂና ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ ምሁራን እና ሌሎች ጸሀፍት ሃሳባቸውን የሚጽፉባቸው የሃሳብ ማንሸራሸሪያ መድረክ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ጋዜጦች ላይ ያሉ ጥንካሬዎቻችንን አጠናክረን በድክመቶቻችን ላይ አተኩረን ከሰራን አሁን ካለው በላይ በይዘት ሥራዎቻችን ተጽዕኖ መፍጠር እንችላለን ያሉት አቶ ወርቁ፤ የለውጥ ስራዎችን በየጊዜው እየፈተሹ ችግሮችን ማረምና ጥንካሬን በማስቀጠል ተጸእኖ ፈጣሪነትን ይበልጥ ማሳደግና ማስፋት ይገባል ነው ያሉት።

በጋዜጦች ላይ የወጡ የፊቸር ሥራዎች የተዳሰሱበትን የጥናት ጹሁፍ ያቀረቡት ደግሞ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ አቶ እስማኤል አረቦ ናቸው።

አቶ እስማኤል እንደገለጹት፤ ከዘርፉ የፊቸር አጻጻፍ መርህ አንጻር የፊቸር ስራዎች ያሉበት ደረጃ ጥሩ የሚባል ነው። በተለይም በሕግ ማስከበርና በህልውና ዘመቻው ወቅት ይሠሩ የነበሩ የፊቸር ሥራዎች በምሳሌነት የሚጠቀሱና በጥንካሬ የሚታወሱ ናቸው። ከዚህ አኳያ የአንባቢያንን ቀልብ የሚስቡ ታሪኮችን እየፈለጉ ብዛት ያላቸው የዜና ፊቸር ዘገባዎችን በመስራት ተጽእኖ ፈጣሪነትና ተነባቢነትን ማሳደግ ይገባል።

መድረኩን የመሩት የኢፕድ የይዘት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ በበኩላቸው፤ የይዘት ሥራዎች በጋዜጦቻችን ከመውጣቸው በፊት በቀን ሁለት ጊዜ በሚካሄደው የኤዲቶሪያል መድረክ ለይዘት ስራዎች የጥንካሬ ምንጭ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ይህ የአርታኢያን መድረክ ደግሞ ሥራዎች ታትመው ከወጡ በኋላ ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን የምንፈትሽበት በመሆኑ ይበልጥ የይዘት ስራዎች ተነባቢ፣ ተደራሽና ተጽእኖ ፈጣሪ ለመሆን ያስችላል ብለዋል።

ይህ የአርታኢያን መድረክ የርስ በርስ መማማሪያ በመሆኑ በቀጣይ በሁሉም የይዘት ሥራዎች ላይ የሚቀጥል መሆኑን አቶ ፍቃዱ ጠቁመዋል።

በመድረኩ ማጠቃለያ መልዕክት ያስተላለፉት የኢፕድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሠ በበኩላቸው የአርታኢያን መድረክ የይዘት ጥራትን ለማሻሻል የልምድ ልውውጥ መድረክ መሆኑን ገልጸዋል።

የጋዜጦችን ይዘት የሚያሳድጉ ትችቶች አስፈላጊ ናቸው ያሉት አቶ ጌትነት፤ እንደ ተቋም የጀመርናቸው ሠፋፊ የለውጥ ሥራዎችን ይዘን ወደፊት ስንቀጥል በፊት የነበሩ ጠንካራ ተሞክሮዎችንም ይዘን ነው። ከዚህ አንጻር የአርታኢያን መድረኩ ተቋርጦ የቆየ ቢሆንም አስፈላጊ ተሞክሮ ስለሆነ አስጀምረነዋል ብለዋል።

ወደፊትም መድረኩ በወር አልያም በሁለት ወር አንድ ጊዜ በቋሚነት የሚካሄድ ይሆናል ያሉት አቶ ጌትነት፤ መድረኩ መልካም ተሞክሮዎችን ለማጎልበትና ለታዩ ድክመቶች የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለመቀየስ ያስችለናል ነው ያሉት።

ይህ መድረክ የመማማሪያና የይዘት ማሻሻያ ግብዓታችንም ስለሆነ፤ አገራዊና ተቋማዊ አንድምታ በሚያጎላ መልኩ በቀጣይ የውስጥም ብቻ ሳይሆን የውጭ ባለሙያዎች ጭምር የሚሳተፉበትና በጋዜጦቹ ይዘት ስራዎች ላይም ጹሁፍ የሚያቀርቡበት ትልቅ የባለሙያዎች መድረክ እናደርገዋለን፤ ለዚህም ተቋሙ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደርጋል ብለዋል።

በመድረኩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ የሌሎች የሚዲያ ተቋማት ባለሙያዎች እና የድርጅቱ አርታኢያን ተሳትፈዋል።



## «የህዳሴው ስኬት መከራ የማይበግረን፣ ፕሮፖጋንዳ የማይረታን ጠንካራ ሕዝቦች መሆናችንን ያሳየንበት ነው»

**- ወጣት ሱሌይማን አብደላ የማሕበረሰብ አንቂ**

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ሁለተኛ ዩኒት ሃይል እንዲያመነጭ ማድረግ መቻላችንና ሶስተኛውን ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት ማጠናቀቃችን መከራ የማይበግረን ፕሮፖጋንዳ የማይረታን ጠንካራ ሕዝቦች መሆናችንን ያሳየንበት ነው ሲል የማሕበረሰብ አንቂው ወጣት ሱሌይማን አብደላ ገለጸ።

የማሕበረሰብ አንቂው ወጣት ሱሌይማን አብደላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ የግድቡ መሰረት ድንጋይ ከተጣለበት እለት ጀምሮ ኢትዮጵያ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች።

ኢትዮጵያ አገር፣ አህጉርና ዓለም አቀፍ ፈተናዎች ተቋቁማ እዚህ መድረሷ፤ ኢትዮጵያውያን መከራ የማይበግራቸው የሐሰት ፕሮፖጋንዳ የማይረታቸው ጠንካራ ሕዝቦች መሆናቸውን ለወዳጅና ጠላቶቻቸው ያስመሰከሩበት አጋጣሚ እንደሆነም ተናግሯል።

ኢትዮጵያ ይሄን ቀን ለማየት ብዙ ፈተናዎችን አሳልፋለች ያለው ወጣት ሱሌይማን፤ የገጠሟትን ፈተናዎች ተቋቁማ ለሁለተኛ ጊዜ ሃይል ማመንጨት መጀመሯና ለሶስተኛ ጊዜ የውሃ ሙሌቱን በስኬት ማጠናቀቋ፣ ለዜጎቿ በራስ መተማመንን የሚጨምር ነው ብሏል።

በግድቡ ግንባታ ወቅት ሥነ ልቦናዊ ማበረታቻ ያደረጉ፣ በገንዘብ የደገፉ፣ በሕይወታቸው ተደራድረው ግድቡን የሚጠብቁ የጸጥታ አካላት፣ በግንባታ ስራ የተሰማሩ ሰራተኞች፣ ከአገራቸው ጎን ለቆሙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የደስታና የመመስገኛ ወቅታቸው መሆኑንም ወጣት ሱሌይማን ተናግሯል።

እንደ ወጣት ሱሌይማን ገለጻ፤ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ተነሳሽነት ግድቡን መገንባት መቻላቸውና የግድቡ ኤሌክትሪክ ማመንጨት መጀመር ራስን ችሎ በራስ ወጪና እውቀት ትልልቅ ፕሮጀክቶችን የመገንባት አቅምና ጉልበት ያላት አገር መሆኗን ያሳየ ነው።

በተጨማሪም ስኬቱ ኢትዮጵያ ከምዕራባውያን እርዳታና ምፅዋት ነፃ ሆነው የቱን ያሕል መጓዝ እንደሚችሉ ትልቅ ማሳያ ነው ሲል ወጣት ተናግሯል።

ወጣት ሱሌይማን ለአገሩ ጥብቅና ቆሞ በታላቁ የሕዳሴ ግድብ ላይ አስተዋፅኦ በማበርከቱና የዚህ ታሪክ አካል መሆኑ እንደሚያኮራው የገለጸ ሲሆን ሌሎች ወጣቶችም እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን ሳይቆጥቡ አገራቸውን ሊያገለግሉ እንደሚገባቸው ጠቁሟል።

መንግሥት የሕዝብን አንድነት አስጠብቆ በምስራቅ አፍሪካ ብሎም በመላው ዓለም ጠንካራ ኢኮኖሚን ለመገንባት ፊቱን ወደ ልማት ስራዎች ማዞር እንደሚጠበቅበት የጠቆመው ወጣት ሱሌይማን ሕብረተሰቡም የሚመራውን መንግሥት የልማት ጥያቄዎች በመጠየቅ ለዚያ ምላሽ የራሱን አስተዋፅኦ ሊያበረክት እንደሚገባው ተናግሯል።

የግድቡ ኤሌክትሪክ ማመንጨት ኢትዮጵያን ወደ ኢኮኖሚዊ ከፍታ እንደሚያሸጋግራት የገለጸው ወጣት ሱሌይማን ኢኮኖሚዋን በተሻለ መንገድ ለመገንባት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነም ጠቁሟል።

## «ግብጻውያንና ሱዳናውያን እህት ወንድሞቻችን ኢትዮጵያ እንኳንም የህዳሴ ግድብን ገነባችልን የሚሉበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም»


**- አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ከኢትዮጵያ አልፎ ለሱዳንና ለግብጽ ሕዝቦች እጅግ ጠቃሚ የሆነውን ታላቁን የህዳሴ ግድብ ኢትዮጵያ እንኳንም ገነባችልን ሲሉ ግብጻውያንና ሱዳናውያን እህት ወንድሞቻችን የሚገልጹበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ሲል ጀግናው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ ገለጸ።

የህዳሴው ግድብ ሁለተኛ ተርባይን ሥራ መጀመርንና ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቅን አስመልክቶ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ በተለይም ለኢ.ፕ.ድ እንደገለጸው የፍትሃዊነት መገለጫና እንደ ዓድዋው ድል ሁሉ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ነጻነት ለአፍሪካ ቀንዲል የሆነችበት ታላቁ የህዳሴ ግድብ በመላ ኢትዮጵያውያን ርብርብ ለዚህ ደረጃ መብቃቱ የኢትዮጵያውያንን አሸናፊነት ከፍ አድርጎ ለዓለም ያሳየ ነው ብሏል።

በአትሌቲክሱ፣ በልማት ሥራዎችና በፀጥታው ዘርፍ ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ያለው ድል ከዚህ በፊት



ተደርጎ የማያውቅና እኛ ኢትዮጵያውያን በእውነትም እንደምንችል ያሳየንባቸው ህያው ምስክሮች ናችው ያለው አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ በዚሁ ሁሉ ድላችን ፊጣሪ ፊቱን አዙሮልናል ብዬ አምናለሁ፤ ለዚህም ትልቅ ምስጋና ይገባዋል ሲል አክሎ ገልጿል።

በታላቁ የህዳሴ ግድብ መተጋገዝና መተባበር ምን ያህል ለድል እንደሚያበቃና አንዱ መሪ የጀመረውን ሌላው በማስቀጠል የኢትዮጵያን ልዕልና ማረጋገጥ እንደሚቻል በተጨባጭ አይተንበታል ብሏል።

ኢትዮጵያ መርፌ እንኳን መስራት አትችልም ስንል ራሳችንን ስንሰድብ ቆይተናል ያለው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ፤ ይሁንና ይህ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያን እንደማይገልጽና ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከሰራን ተአምር መፈጸም እንደምንችል ሰሞኑን ባገኘናቸው ድሎች ተመስክሯል ብሏል።

አትሌት ኃይሌ በማጠቃለያ መልዕክቱ ኢትዮጵያውያን አውቀንም ይሁን ሳናውቀው የጠላት አጀንዳ ተሸካሚና የጥፋት ተላላኪ እንዳንሆን መጠንቀቅ ይገባናል። ብንችል ለኢትዮጵያ ሰላምና ዕድገት የራሳችንን አሻራ ማስቀመጥ ይሄን ማድረግ ያቃተው ቢኖር ግን ቢያንስ የልማት ጉዞ እንቅፋት ባለመሆን ከታሪክ ተጠያቂነት ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል ብሏል።



ዶክተር ጫኔ ከበደ



አቶ ቶሴራ አደባ



አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ

## ግድቡ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ የኢትዮጵያውያንን የመልማት ጥያቄ የመለሰ መሆኑን የፖለቲካ ፓርቲዎች አስታወቁ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቁና ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩ የኢትዮጵያውያንን ፍትሃዊ የሆነ የመልማት ጥያቄ የመለሰ መሆኑን ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ገለጹ። የኢዜማ፣ የኦነግና ትዴፓ ፓርቲ አመራሮች ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቁና ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩን አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማሕበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሊቀመንበር ዶክተር ጫኔ ከበደ እንደተናገሩት፤ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጉዳይ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ኢዜማ ልዩ ክትትል ከሚያደርግባቸው አገራዊ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው። ግድቡ ኢትዮጵያዊነትን ያስተሳሰረ፣ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው አቅምና ሀብት የሰሩትና ጠቀሜታው ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ ሁሉም በተስፋ የሚጠብቀውና የሚጠባበቀው ትልቅ አገራዊ ፕሮጀክት ነው። ኢዜማም እንደ ዜግነት አስተሳሰባችን ውጤቱን ስኬቱን ሲናፍቅና ሲጠባበቀው የነበረ ፕሮጀክት ነው።

ኢትዮጵያ ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለመሸጋገርና ብዙ ስራ ዕድል ለመፍጠር በምታደርገው ጥረት ውስጥ የግድቡ ስኬት ወሳኝ ትርጉም አለው ያሉት ዶክተር ጫኔ፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሶስተኛው ዙር ሙሌት መጠናቀቅና ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመር ለኢኮኖሚያዊ እድገታችን ትርጉም ያለው ለውጥ እንደሚያመጣ ጠቁመዋል። ይህም ለኢትዮጵያውያን ትልቅ ኩራት እንደሆነ ተናግረዋል።

የህዳሴው ግድብ ይዞት የሚመጣው ኃይል ኢትዮጵያን ወደ አንድ ምዕራፍ ያሻግራታል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ ኢትዮጵያ ያለችበትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ደረጃዎችን በሙሉ ለዓለም ማሳየት የምትችልበት ትልቅ ፕሮጀክት ነውም ብለዋል።

ጠላት የውስጥ ልዩነቶችን በመጠቀም ግድቡ እንዲቆም ጥረት ቢያደርግም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድህነት መውጣት ስላለበት ውስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮችን በጋራ ተቋቁሞ ግድቡን ለመጨረስ «ግድቡ የእኔ ነው» የሚል መሪ ቃል ይዞ ሀብቱን በማዋጣት እየሰራ በመሆኑ ህብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ያሳየ መሆኑን የዓለም ሕዝብ ያወቀበት መሆኑን ዶክተር ጫኔ ተናግረዋል።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር(ኦነግ) ቃል አቀባይ አቶ ቶሴራ አደባ፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቅና ሁለተኛው ዙር ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብስራት መነገሩ ግድቡ በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እየተገነባ እንዳለ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ምን እንደሆነ ለዓለም ሕዝብ ያስገነዘበ ነው ብለዋል።

አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለትውልድ የሚተላለፍ ስራ ተሰርቶ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ሁሉንም ያስደሰተ ነው ያሉት አቶ ቶሴራ፤ ኦነግ እንደ ፓርቲ በታላቅ ደስታ ተቀብሎታል ሲሉም ተናግረዋል።

አቶ ቶሴራ፤ ይህ ኢትዮጵያን ወደፊት ትልቅ እርምጃ እንድትራመድ ያደረገ በመሆኑ ለአገር እድገትና ብልጽግና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለውጭ ጫና ሳይበገር ለዚህ ድል መብቃቱ ትልቅ ኩራት በመሆኑ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል።

በቀጣይ የኢትዮጵያን ፍትሃዊ የመልማት ፍላጎት ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ለማስገንዘብ ጠንክሮ መስራት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ቶሴራ፤ ኦነግም እንደ ፖለቲካ ድርጅትነቱ ለአባላቱና ደጋፊዎቹ ግንዛቤ በመፍጠር ድጋፍ ማድረጉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ በተናጥል ፉክክርና እልህ የሚገነባ አገርና የሚመጣ ብልጽግና የለም። ስለዚህ በታላቁ የህዳሴ ግድብ የታዩ አንድነቶችን ማጠናከር ይገባል። በብሔር፣ በፖለቲካ ልዩነት ፣ በተለያዩ አመለካከቶች ሳይለያይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ግድቡ የእኔ ነው በማለቱ የተገነባ በመሆኑ በሌሎች ጉዳዮች ላይ በትብብር ሊሰራ ይገባል።

የትግራይ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ በበኩላቸው፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቅና ሁለተኛው ዙር ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩ እንደ ፓርቲ ትልቅ ደስታ ሰጥቶናል ብለዋል። አባይን መገደብ ከጀመርን ጊዜ ጀምሮ በጂኦ ፖለቲካው ብዙ ተግዳሮቶችን አልፎ ከዚህ ደረጃ መድረሱ ልዩ ትርጉም እንዳለውም ጠቁመዋል።

ዓባይ ማለት የአንድነታችን ማስተሳሰሪያ ገመድ ነው ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ ለአባይ ገንዘቡን፣ ጉልበቱን ያላዋጣ ሕዝብ የለም። ስለዚህ ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ፍሬ አፍርቶ መታየቱ እንደ አገር ትልቅ ስኬት ነው ሲሉም ገልጸዋል።

አገራችን የጀመረችው የለውጥ ጉዞ የተሳካ እንዲሆንና ከድህነት ወጥተን ራሳችንን እንድንችል ከዚህ የበለጠ መተጋገዝ፣ መደጋገፍና አንድነታችን ማጠንከር አለብን። ኢትዮጵያ በገጠማት ፈተና ሳትደናቀፍ ችግሮችን በመሻገር በርካታ ድሎችን እያስመዘገበች ያለች አገር ናት። ታላቁ የህዳሴ ግድብም ከጀመረችው የለውጥ ጉዞ ማንም እንደማያስቆማት ትምህርት የሰጠ በመሆኑ ለመላ ኢትዮጵያውያን እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል።

አዲስ ዘመን | ቅዳሜ ነሐሴ 7 ቀን 2014 ዓ.ም

ዜና

# «ዓባይ አሁን ላይ ለኢትዮጵያ ወሳኝ የልማት አቅም ሆኗል»

- አቶ ደመቀ መኮንን

የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ዓባይ አሁን ላይ ኢኮኖሚያችንን የምናሳድግበትና ከድህነት የምንወጣበት ወሳኝ የልማት አቅም ሆኗል ሲሉ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ተናገሩ።

አቶ ደመቀ መኮንን የሕዳሴ ግድብ ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁን ተከትሎ ትናንትና በጉባ ተገኝተው እንደተናገሩት፤ የአባይ ተፈጥሮ ጸጋ ለሺህ ዓመታት ከኢትዮጵያ ማህፀን እየፈሰሰ ተጉዟል። አሁን ላይ ደግሞ የተፈጥሮ ጸጋው የኢኮኖሚ አቅማችንን ለማሳደግ የሚረዳ ብሎም ድህነትን የማሸነፊያ መሳሪያ ሆኗል።

ዓባይ አሁን ለኢትዮጵያውያን ወሳኝ የልማት አቅም ሆኖ ኃይል ያመነጫል፤ ከዚህም አልፎ ወደታችኞቹ ተፋሰስ አገራት ጉዞውን ቀጥሏል ሲሉ ተናግረዋል።

የተፈጥሮ ጸጋችን ዓባይ ከኢትዮጵያ ማሕጸን እየፈሰሰ ለሺሕ ዓመታት ተጉዟል፤ ዛሬ ግን በጋራ ጥረታችንም ለኢትዮጵያ ብልጽግና ሊሆን ከመጀመሪያው ምዕራፍ ደርሷል። በአንድ ድምጽ በአንድ የተባበረ ክንድ ብዙ ፈተናዎችን ተሻግረን በግድቡ ስራ ለስኬት በቅተናል። በዚህ ልንኮራና ለላቀ ስኬት ልንነሳሳ ይገባል ብለዋል።

በሕዳሴው ግድብ ውጤት ኢትዮጵያውያን ተባብረን ያገኘነው ታሪካዊ ድል ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ ኢትዮጵያውያን ስንተባበር እንዴት እንደሚያምርብንና በተለያዩ ትንንሽ አጀንዳዎች ስንጣላ ደግሞ እንዴት እንደምንጎዳዳ ከታሪካችን ማየት ችለናል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ገለጻ፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት በማንኛውም ሰው ሰራሽ ጫናዎች ሳይበገር ለዚህ ታላቅ ውጤት መብቃቱ የትውልዱ ጽናት እና ትብብር ማሳያ ነው።

የአንድነታችን መገለጫ የህብረታችን ማረጋገጫ የሆነው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት በሂደት ወደ ማጠናቀቂያ ምዕራፍ መሸጋገሩን ቀጥሏል ብለዋል።

ባለፉት ዓመታት እንደጎነገር ከገጠሙን የሰላምና የፀጥታ ችግሮች አኳያ የግድቡ ግንባታ ሳይስተጓጎል በተቀመጠለት የጊዜ ማዕቀፍ ማስቀጠል መቻላችን ፈተና ይበልጥ ያፀናን እንደሆን እንጂ ከቶውኑ እንደማይጥለን በተግባር ያረጋገጥንበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያን የፍትህ መንገድ በመጫን ለማዛባት ወደ ቀድሞ የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ ለመመለስ የሚደረጉ ጥረቶች አሉ፤ ጥረቶቹ ግን ከዕውነት ያፈነገጡና የኢትዮጵያውያንን መብት የሚጋፉ በመሆናቸው ተቀባይነት አይኖራቸውም ብለዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ጊዜያት ከዕኁነት ጋር ቆማ በዲፕሎማው መድረክ ብዙ መስራቷን ጠቁመው፤ ለኔ ብቻ የሚል አስተሳሰብ ከኢትዮጵያ እውነታ ያፈነገጠ ነው። ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ በፍትሃዊነት መጠቀም እንደሚቻል በፍትሃዊነት በዓለም አደባባይ አቋሟን እያሳወቀች እዚህ ደርሳለች ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የግድቡ ተጠቃሚነት ሳይንሳዊም፣ ፍትሃዊም ይዘት ያለው እውነት በመሆኑ ለስኬት በቅተናል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ስለግድቡ የተለያዩ ጉዳዮች ሲነሱበትና ጥርጣሬዎች ቀርበውበት ብዙ ፈተናዎችን አልፈናል ብለዋል።

የዓባይ የተፈጥሮ ጸጋ ሁላችንንም ያስተሳሰረ እንደመሆኑ ተባብረንና ተከባብረን የየድርሻችንን መጠቀም እንችላለን ያሉት አቶ ደመቀ፤ 21ኛው ክፍለ ዘመንም የሚጠይቀው አስተሳሰብና አሰላለፍ ጸጋውን በጋራ የመጠቀምንና የማልማት እሳቤ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

አቶ ደመቀ እንደገለጹት፤ በተፈጥሮ ጸጋዎች የበለጠ ለመጠቀም አንድ መሆንና መተባበር ያስፈልጋል። ሰላምና አንድነትን በማረጋገጥ የኢትዮጵያን ልማት ማፋጠን ይገባል።

በቀሪ የማጠናቀቂያ ምዕራፍ ስራዎች በተለመደው አግባብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድነቱን ይበልጥ እንዲጠብቅ እና ሕብረቱን እንዲያፀና መልዕክት አስተላልፈዋል።

ለግድብ ግንባታ ሂደቶች መሳካት ጉልህ አስትዋጽኦ ላበረከቱ ለፕሮጀክቱ አመራሮችና ባለሙያዎች፣ ለግድቡ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት አባላት፣ ለፀጥታ አካላት፣ ለባለሀብቶች፣ ለዳያስፖራው ማሕበረሰብ አባላትና ለመላው ኢትዮጵያውያን ምስጋና አቅርበዋል።

## ከዓባይ ውሃ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እያመነጨች ለዘመናት ሳትጠቀም መቆየቷ የሚያስቆጭ ቢሆንም፤ አሁን የሚገባንን ተጠቅመን የሚገባቸውን ለወንድሞቻችን ሰጥን በጋራ ለማደግ ዝግጁ ነን ብለዋል።

የዓባይ ውሃ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም የተሰጠ ወንዝ መሆኑን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ውሃው በተለይ ለኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብፅ ብሎም ለአፍሪካና ለዓለም እንዲጠቀሙበት ከፈጣሪ የተሰጠ ነፃ ስጦታ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን የዓባይ ውሃ በነፃ የተሰጣቸው ሀገራት ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ሦስቱ ሀገራት ይህን ውሃ በነፃ የመጠቀም ዕድል የተሰጣቸው በመሆኑ የሚገባቸውን ድርሻ በአግባቡ መጠቀም ከቻሉ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የአፍሪካ ወንድም እና እህቶችም ጭምር መጥቀም የሚችሉ በርካታ ሥራዎች መሥራት ይችላሉ ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ ከኢትዮጵያ፣ ከሱዳንና ከግብፅ የተሰጣቸውን ሀብት መገንዘብ፤ በተሰጣቸው ልክ መተባበር እና በጋራ መቆም ይጠበቃል። ነገር ግን ዓባይ ለሦስቱ ሀገራት እንደተሰጠና ሀገራቱ በሚገባቸው ድርሻ መጠቀም እንዳለባቸው የማያምኑ ኃይሎች ካሉ የተፈጥሮን ሕግ ያዛባሉ። ዓባይ ወንዝም በተፈጥሮ ይህን መፋሰሻ ሲይዝ ኢትዮጵያ የሚገባትን ተጠቅማ ሱዳንና ግብፅ ወንድሞችም እንዲጠቀሙበት በነፃ የተሰጠ ስጦታ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

አፍሪካም የዓባይ ውሃ ተጠቃሚ እንደምትሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቁመዋል። የአፍሪካን ኢኮኖሚ ለማስተሳሰር የተጀመሩ ሥራዎች መኖራቸውን በማንሳት አህጉሯን በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር አንዱ መንገድ ኢነርጂ መሆኑን አንስተዋል። የህዳሴው ግድብ ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ሲያመነጭ ለጎረቤት ሀገራት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ተሻግሮ የሚጠቅም በመሆኑ ለአፍሪካ ሀገራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር የራሱ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

የዓባይ ውሃ ከኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብፅ ባለፈ የአፍረካ ሀገራትን መጥቀም የሚችል መሆኑን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በተመሳሳይ ለዓለምም ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ተናግረዋል። የዓለም ሕዝቦች ወደ አካባቢው በመምጣት እንዲዝናኑና ጊዜያቸውን በደስታ እንዲያሳልፉ የሚያስችል ከፍተኛ ብቃት አለውም ብለዋል። በታላቁ ህዳሴ ግድብ 70 የሚሆኑ ከፍተኛ ቦታዎችና ደሴቶች መኖራቸውን አንስተው ዓለም አካባቢው ምቹ መሆኑን ተገንዝቦ ለመጠቀምና ኢንቨስት ለማድረግ ዝግጁ መሆን እንደሚጠበቅበት አሳስበዋል።

በተጨማሪም የህዳሴው ግድብ ከሚያመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል በተጨማሪ ሥነምህዳራዊ ጥቅሞች እንዳሉት ለዓሣ ርባታ ተስማሚ መሆኑንና በዓሳ ማስገር ለሚዝናኑ ቱሪስቶች ተዝናኖት እንዲሁም ለተራራ ላይ ጉዞ ለሚያዘወትሩ እና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ዘርፎች ምቹ መሆኑን ጠቁመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ዓባይ የኢትዮጵያ ኩራት፤ የብልፅግናዋ ጅማሮ መነሻ፤ ኢትዮጵያዊነት እና የኢትዮጵያ ከፍታ የሚለመልምበት ቦታ መሆኑን ተገንዝበን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጋራ በመደመርና አንድ ላይ በመቆም ብልፅግናችንን ዕውን እናድርግ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ለተሳተፉ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና በዕውቀትና በጉልበት የተሳተፉ እንዲሁም በገንዘብ ድጋፍና በዲፕሎማሲ መስክ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ላበረከቱ ምሥጋና ያቀረቡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ለግድቡ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቅ መላው ኢትዮጵያውያንና አፍሪካውያን ወንድሞች እንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ግድቡ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 575 ሜትር ይፈስበት የነበረው ከፍታ በዘንድሮው ዓመት በ25 ሜትር ከፍ ብሎ 600 ሜትር ላይ የውሃው ፍሰት ይታያል። በግራና በቀኝ በኩልም ያለው ርዝመት 585 ሜትር የነበረ ሲሆን ዘንድሮ 611 ሜትር በመድረስ ውሃ የመያዝና ኃይል የማመንጨት አቅሙ ከፍ ብሏል።

ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታው የተጀመረው በ2003 ዓ.ም ሲሆን ከትናንትና በስቲያ የሁለተኛው ተርባይን ኃይል የማመንጨት መርሃግብር ተበስሯል። በትናንትናው ዕለት ደግሞ የግድቡ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት ተጠናቆ ውሃው በግድቡ አናት ላይ መፍሰስ ጀምሯል።

## አንጸባራቂው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ገልጸዋል። ወጣቶቹ አትሌቶች ዛሬ በተለያዩ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች በክፍት ተሽከርካሪዎች እየተዟዟሩ ደስታቸውን ከሕዝብ ጋር እንደሚካፈሉ ይጠበቃል። በስካይ ላይት ሆቴልም የእውቅናና የሽልማት መርሃግብር እንደተዘጋጀላቸው ታውቋል።

የወጣት አትሌቲክስ ቡድኑ በውድድሩ ታሪክ 6 ወርቅ ፣5 ብርና 1 የነሐስ ሜዳሊያ በማስመዝገብም ከዓለም ሶስተኛ ከአፍሪካ ደግሞ ቀዳሚ ሆኖ ማጠናቀቅ ችሏል። በ19 አትሌቶች በሁለቱም ፆታ በ10 የውድድር ተግባራት ብቻ የተሳተፈው የአትሌቲክስ ቡድን በድምሩ በ12 ሜዳልያዎች ከዓለም ሀገራት አሜሪካንን እና ጃማይካን ተከትሎ 3ኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል። ይህም ውጤት እስከ ዛሬ ከተካሄዱት የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች ከፍተኛው ሲሆን ከተሳተፉበት ውስን ውድድሮች አንፃር ውጤቱ በርካቶችን ያስደሰተ ሆኗል።

በውድድሩ ኢትዮጵያ ይዛ ካጠናቀቀችው ደረጃ ባሻገር አራት ወርቆችና ሁለት የብር ሜዳሊያዎች ቻምፒዮናው በተጠናቀቀበት ሌሊት የተመዘገቡበት መንገድ በርካቶችን አስደስቷል። እነዚህ ሜዳሊያዎች በአንድ ሌሊት አንድ ሰአት ባልሞላ ሰአት ውስጥ ሲመዘገቡ በወንዶች ስምንት መቶ ሜትር ወርቅ፣ በወንዶች 3ሺ ሜትር መሰናክል ወርቅና ብር፣ በሴቶች 1500 ሜትር ወርቅና በሴቶች አምስት ሺ ሜትር ወርቅና ብር የኢትዮጵያ ሆኗል።

በዚሁ ቻምፒዮና በ1500 ሜትር የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ የቻለው ወጣቱ አትሌት ኤርሚያስ ግርማ በ800 ሜትር ተጨማሪ ወርቅ በማጥለቅ በቻምፒዮናው የጎላ ኢትዮጵያዊ አትሌት ሆኗል። በ3ሺ ሜትር መሰናክል ወንዶች ሳሙኤል ዱጉና የወርቅ ሜዳሊያውን ሲያጠልቅ ሌላኛው ኢትዮጵያዊ ወጣት አትሌት ሳሙኤል ፍሬው በድንቅ ብቃት የብር ሜዳሊያውን ወስዷል። ከባድ ፉክክር ባስተናገደው በ5ሺ ሜትር ሴቶች ውድድር መዲና ኢሳ እና መልክናት ውዱ በተመሳሳይ ወርቅ እና ብር ሜዳሊያ ሲያጠልቁ፣ በ1500ሜ ሴቶች ደግሞ በአትሌት ብርቄ ሀየሎም (4:04.27) የቻምፒዮናውን ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር የወርቅ ሜዳሊያ ማሸነፍ ችላለች።

ከፍጻሜው ቀን አስቀድሞ በነበሩ ሌሎች ውድድሮች ኢትዮጵያ በ5 እና 3ሺ ሜትር ወንዶች በአዲሱ ይሁኔ እና መልኬነህ አዘዝ የወርቅ፣ በ3ሺ ሜ መሠናክል ሴቶች በሲምቦ አለማየሁ፣ በ1500 ሜትር ወንዶች በኤርሚያስ ግርማ እና በ3ሺ ሜትር ሴቶች በፅዮን አበበ የብር ሜዳሊያወችን ያሸነፈች ሲሆን፣ በተጨማሪም በሴቶች 3ሺ ሜትር መሰናክል በአትሌት መሰረት የሻነህ የነሀስ ሜዳልያ ማግኘቷ ይታወቃል።

ይህንን ውጤት ተከትሎም ኢትዮጵያ በሜዳሊያ ሰንጠረዡ በ ስድስት ወርቅ፣ አምስት ብር እና አንድ የነሀስ በድምሩ በ12 ሜዳሊያዎች ከአሜሪካ እና ጃማይካ በመቀጠል ከዓለም ሶስተኛ ከአፍሪካ ደግሞ በቀዳሚነት ውድድሯን ፈጽማለች። በ19 ወጣት አትሌቶች እና በ10 የውድድር አይነቶች ተሳትፎ ብቻ የተገኘው ይህ አስደናቂ ውጤት በቻምፒዮናው ብቻ ሳይሆን በታላላቅ ውድድሮች ታሪክ የኢትዮጵያ የምንጊዜም ከፍተኛው ሆኖ ተመዝግቧል።

## «የግድቡ ትርጉም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ።

የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት ትናንት በስኬት መጠናቀቁን አስመልክቶ በጉባ በተዘጋጀው መርሃግብር ላይ የተገኙት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፤ የግድቡ ትርጉም ሃይል ከማመንጨት በላይ ኢትዮጵያውያን እንችላለን የሚለውን የሚያሳይ ነው፤ ኢትዮጵያውያን ከተባበርን ብዙ መስራት እንችላለን፤ ዛሬ ያየነው የአሸናፊዋን ኢትዮጵያ ገጽታ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ይህ ፕሮጀክት ከግድብነት ያለፈ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ግድቡ የሙብራት ሃይል ከማመንጨት ያለፈ ትርጉም እንዳለው፤ ከጭለማ ወደ ብርሃን ከማሸጋገር ያለፈ እንደሆነ፤ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ ዘር እንዲሁም የተለየ ቀለም የሌለው ይልቁንም ኢትዮጵያዊ ግድብ መሆኑን ጠቅሰዋል። ኢትዮጵያውያን ከተባበርን ለዚህ መድረስ እንችላለን ብሎ የሚያሳይ እንደሆነም ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቷ፤ "ኢትዮጵያውያን ከተባበርን ብዙ መስራት እንችላለን፤ ዛሬ ያየነው የአሸናፊዋን ኢትዮጵያ ገጽታ ነው። ኢትዮጵያ እንደዚህ ነች፤ ኢትዮጵያን እንደዚህ ነው ማድረግ ያለብን። ኢትዮጵያን ዛሬ የደስታ እንባ እንድታፈስ እናደርጋታለን። ነገር ግን የኀዘን እንባ እንድታፈስ አድርገናታል። ይህንን ማወቅ አለብን ፤ ማመን አለብን" በማለት ከዚህ ለመውጣት መስራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖች ይህንን ግድብ ለዚህ ያበቁት በሀሩር ውስጥ እንደሆነና፤ የውጭ ድርጅቶችም በዚህ ግንባታ መሳተፋቸውን በመጥቀስ፤ "ነገር ግን ከሁሉም በላይ እናንተ ኢትዮጵያውያን በልታችሁ ሳትጠግቡ ፣ ነገ ያልፍልናል ብላችሁ ገንዘብ ያዋጣችሁ፣ እናንተ ኢትዮጵያውያን ለዚህ ግድብ የተረባረባችሁ፤ ሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ያላችሁ በእጅጉ ልትመሰገኑ ይገባል" ብለዋል።

ግድቡ አሁን ወደ ልማት ለማተኮር የሚጋብዝ በመሆኑ ይህ ሃይል መንጭቶ ለሕዝቡ በፍትሃዊነትና በዘላቂነት የሚደርስበትን ሁኔታ በማመቻቸት ኢትዮጵያ ወደፊት እንድትራመድ ማድረግ እንደሚገባም አሳስበዋል።

ፕሬዚዳንቷ፤ ላም አለኝ በሰማይ ከሚለው እንድንወጣ እያደረገን ነው በማለት፤ "የኛ ስራ ውይይትን፣ ምክክርን የሚከለክል አይደለም። እንዳውም የዚህ ግንባታ እዚህ መድረስ ለጎረቤት ሀገሮች ከናይል ተፋሰስ ሀገሮች ጋር የበለጠ ትብብር ምክክር እንዲኖረን ከሀገር አልፎ አካባቢውን፣ ከአካባቢ አልፎ አህጉራችንን ለማሳደግ ነው መነሳት ያለብን" ሲሉ ገልጸዋል።

ግድቡ በጋራ ለመስራት የዲፕሎማሲውን በር በሰፊው የሚከፍት እንደሆነ በመግለጽ፤ በርትቶ መሥራት እንደሚገባና የሕዝቡ ድጋፍም ቀጣይነት እንዲኖረው ጥሪ አቅርበዋል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሄት

ከጆብሉ
ንግድ ወደ
ፋብሪካዎች
ባለቤትነት



ገጽ 13



«ያየነው የአሸናፊዋን
ኢትዮጵያ
ገጽታ ነው»

- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

ገጽ 14



«የትልልቅ ህንፃዎች መሰራት ከከተማ ውበት ባሻገር
እድገት እንዲመጣ አስተዋፅኦ አበርክቷል»

- ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል ዋተሮ

ገጽ 6



ጎዳናን ከመለመኛነት ወደ
ስራ ማከናወኛነት እየለወጡ
ያሉ ባለሙያ

ገጽ 16

## በውስጥ ገጾች

«የሚገባንን ተጠቅመን፣ የሚገባቸውን
ለወንድሞቻችን ሰጥተን በጋራ ለማደግ በእኛ
በኩል ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ አገልጻለሁ»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣

ገጽ 9

የግል ትምህርት ቤቶችና «የግል
ሥርዓተ ትምህርቶች»

ገጽ 11

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹የትልልቅ ህንፃዎች መሰራት ከከተማ ውበት ባሻገር እድገት እንዲመጣ አስተዋፅኦ አበርክቷል››

- ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል ዋተሮ

ማህሌት አብዱል



የዛሬው የዘመን እንግዳችን በፖሊስ ተቋም ውስጥ በርካታ ስትራቴጂክ ዲዛይን በመስራትና በመቆጣጠር ከፌደራል እስከ ክልሎች ድረስ ስራዎች ያበረከቱ የምህንድስና ባለሙያ ናቸው:: በቀድሞ አጠራር በሸዋ ክፍለ አገር ደቡብ ሸዋ ከምባታ አውራጃ አንጋጫ ወረዳ ዋሰራ ቀበሌ ውስጥ ነው የተወለዱት:: የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ዋሰራ ቅድስት ትሬዛ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል:: በቀድሞ ስያሜ ልጅ አበባ ወልደሰማያት ትምህርት ቤት ደግሞ ዘጠነኛ አስረኛ ክፍልን ተምረዋል:: ወደ 11ኛ ክፍል በከፍተኛ ውጤት ቢያልፉም ወቅቱ የደርግ መንግስት ሥርዓቱን ተረክቦ የእድገት በህብረት ዘመቻ አዋጅ ታወጀና ትምህርታቸውን አቋርጠው በዘመቻው ላይ እንዲሳተፉ ተጠሩ:: በዚህም ምክንያት ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ::

በወቅቱ የዘመቻው ተልዕኮ አንድ አካል የነበረው የመሠረተ ትምህርት ማስተማር፣ ገበሬዎችን የማደራጀት፣ የድልድይ ግንባታና የመንገድ ሥራ እንዲሁም መሬት የማከፋፈሉን ሥራ ሰርተዋል:: ዘመቻውን እንዳጠናቀቁም 11ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ወደ ቀድሞው ትምህርት ቤታቸው ተመልሰው የቀጠሉ ሲሆን 12ኛ ክፍልን ግን የጨረሱት አዲስ አበባ ከሚገኘው ዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት በማለፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለመማር ተመዘገቡ:: ምዝገባውን ካከናወኑ በኋላ በእግራቸው ወደ አሳት አደጋ አካባቢ እየተጓዙ ሳለ የኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሌጅ ያወጣውን የትምህርት ማስታወቂያ ተመለከቱ:: ወትሮውንም ቢሆን ለፖሊስ ሙያ ትልቅ ክብር የነበራቸው እንግዳችን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲውን ትምህርት ትተው በፖሊስ ኮሌጅ ለመማር አመለከቱ። እዛም በምክትል መቶ አለቅነት በከፍተኛ ማዕረግ በፖሊስ ሳይንስ ዲፕሎማቸውን አገኙ::

እንደተመረቁ በቀጥታ አዲስ አበባ ፖሊስ ትራፊክ መምሪያ የትራፊክ አደጋ ምርመራ፣ ሴፍቲ ጥናትና ምርምር ኃላፊ ሆነው ተመደቡ:: ስድስት ወር እንደሰሩ ደግሞ የትራፊክ አደጋ ምርመራ ኃላፊ ሆነው ተሾሙ:: አንድ አመት ያህል እንደሰሩ አምስት ኪሎ በሚገኘው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምህንድስና ትምህርት ክፍል በማታው ክፍለ ጊዜ ገብተው መማር ጀምረውም ነበርና ጎን ለጎን በፖሊስ ኮሌጅ ተመድበውም በትራፊክ ደህንነት መምህርነት ሙያ ለአንድ ዓመት ተኩል አገልግለዋል:: በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ነፃ የውጭ ትምህርት እድል በማግኘታቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲውን ትምህርት አቋርጠው በራሺያ በኢንደስትሪያል ሲቪል ኢንጂነሪንግ የመጀመሪያ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሰሩ::

ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አገራቸው ሲመለሱ ሲሉ የመንግስት ለውጥ በመምጣቱ የራሺያ መንግስት በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ጥሩ ባለመሆኑ እዚያው እንዲቆዩ ይጠይቋቸዋል:: ሆኖም እንግዳችን የራሺያን መንግስት ጥያቄና የሚቀጓውን አማራጭ ‹‹አሻፈረኝ›› ብለው ወደ እናት አገራቸው መጡ:: እንደመጡም ባስተማራቸው የፖሊስ ተቋምም መምሪያ ኃላፊ በመሆንም ተመደቡ:: በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ የኪነ-ህንፃ ሙያቸውን በተግባር የማሳየት እድሉን ያገኙት:: ቦሌ መንገድ ላይ የለንደን ካፌን ዲዛይን ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን አወጡ፤ በወቅቱ ትልቅ የመነጋገሪያ ርዕስ በፈጠረው በዚህ የኪነ ህንፃ ዲዛይን እንዲሁም ግንባታው በሚከናወንበት ጊዜ በአማካሪነት ሰርተዋል::

የፖሊስ ሰራዊት ተቋም ውስጥ በርካታ ስትራክቸራል ዲዛይን በመስራትና በመቆጣጠር ከፌደራል እስከ ክልሎች ድረስ ሰፊ ተግባራት አከናውነዋል:: በተለይም እሳቸው የሚታወቁበት የኪነ-ህንፃ ዲዛይን መሀል ሜክሲኮ ላይ የፌደራል ፖሊስ ዋና መስሪያ ቤትን ከአስር በላይ ዲዛይኖችን ሰርተው ካስረከቡ በኋላ አሁን የሚታየው ዲዛይን ተመርጦ እንዲገነባ የተደረገ ሲሆን ግንባታውንም በበላይ ተቆጣጣሪነት መርተዋል:: የኦሮሚያ ክልል መስሪያ ቤትንም በግንባታ ተቆጣጣሪነት ሰርተዋል:: የአፋር ርዕሰ ከተማ ሰመራ ላይ ምንም አይነት ህንፃ ባልነበረበት ጊዜ ለከተማዋ የመጀመሪያ የፖሊስ ህንፃ ዲዛይን ሰርተዋል:: አለቆቻቸው ‹‹ሻለቃ እንደልቡ›› እያሉ የሚጠሯቸው የዛሬው የዘመን እንግዳችን ሻለቃ ኢንጂነር ወልደሚካኤል ዋተሮ ናቸው:: ከእንግዳችን ጋር በሕይወት ተሞክሯቸውና በሌሎች አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያደረግነው ቃለ-ምልልስ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል::

**አዲስ ዘመን፡- ለውይይታችን መነሻ ይሆነን ዘንድ ‹‹ሻለቃ እንደልቡ›› የሚል ቅፅል ስም እንዴት ሊወጣሎት እንደቻለ ሊነግሩን ይችላሉ?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** እኔ በሕይወቴ የምኖረው በእውነትና እንደፍላጎቴ ነው:: ሥራዬን እንደልቤ መስራት ያስደስተኛል:: በሃቅ ላይ ተመስርቼ ብቻ የምናገርና የምቃወማቸው ስለሆነ ነው አንዳንድ ሰዎች ይህንን ስያሜ ያወጡልኝ:: የማላምንበትን ነገር በገሃድ እናገራለሁ፤ ሥራዬን ግን ጠንቅቄ ነው የምሰራው:: ሆኖም እነዚህ ሰዎች ባወጡልኝ ቅፅል ስም ምንም ቅሬታ የለኝም፤ ደግሞም እንዳሉትም እንድልቤ የምኖር ሰው ነኝ:: ለዚህም ነው ወያኔ ከመጣ በኋላ 12 ዓመት አገልግዬ በኋላም ሁኔታዎች እየተበላሹ ሲመጡ በገዛ ፍቃዴ ለቅቄ የወጣሁት:: በወቅቱ ኃላፊ የነበሩት ሰዎች ማዕረጉ ስላላቸው ብቻ የማላምንበትን ነገር እንዳደርግ ሊያዙኝ እንዳማይችሉ፤ እኔን ለማዘዝ አስቀድመው እኔ የደረስኩበት የእውቀት ደረጃ ላይ መድረስ እንዳለባቸው በድፍረት ነግሪያቸው ነው የወጣሁት:: በመሰረቱ የፖሊስ ተቋም እየከፈለ ያስተማረኝ ባለውለታዬ በመሆኑ ነው የተሻሉ እድሎች እያሉኝ ለዚህ ሁሉ ዓመት ሳገለግል የቆየሁት::

**አዲስ ዘመን፡- የሁለተኛ ደረጃ እድገት በህብረት ዘመቻን የተቀላቀሉበትን አጋጣሚ ያስታውሱን?**

**ሻለቃ ኢንጅነር ወ/ሚካኤል፡-** የ10ኛ ክፍልን እንደጨረስኩኝ የእድገት በህብረት የስራ አዋጅ ታወጀ፤ ከ10ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አራተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በዘመቻው ላይ እንዲሳተፉ በሬዲዮ ተነገረና እኔን ጨምሮ 150 ተማሪዎች ከምባታ አውራጃ ውስጥ ቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ አሁን ዱራሜ የሚባለውና የከንባታ ዋና ከተማ ተመድበን ሄድን:: ሸሪፋ በሚባል ሜዳ ላይ ድንኳን ተጥሎ ህዝቡ ድግስ ደግሶ ፤ ‹‹መሄዴ ነው ዘመቻ››፣ ‹‹ተነሳ ተራመድ፤ ክንድህን አበርታ›› የሚሉ ጥዕመ-ዜማዎችን እያዜሙም ነው የተቀበሉን::

በዚያ ሁኔታ እነዚያ ተማሪዎች በአምስት የተለያዩ ቦታዎች ተመድበን ቀኑን ሙሉ ስንፈጋ ነው የምንውለው:: መንገድ፣ ድልድይ እንሰራለን። ገበሬዎቹም ባህር ዛፍ ቆርጠው ተሸክመው እየመጡ ያግዙን ነበር:: ከዚሁ ጎን ለጎን የአካባቢውን ሰው ሰብስበን መሰረተ ትምህርት እናስተምራለን፤ ሴት፣ ወንድ፣ ህፃን ሽማግሌ ሳይባል ሁሉም ፊደል እንዲቆጥር ይደረግም ነበር:: በዚህም ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ችለን ነበር:: በወቅቱ በዘመቻው የተሳተፍነው ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ተመርጠን የመጣን ተማሪዎች ብንሆንም ያለማንም ልዩነት ተቀራርበን ነበር የምንሰራው:: እኔ እንዳውም በየሳምንቱ ዘመዶቼ ቤት እየወሰድኳቸው ከፍተኛ ግብዣ ይደረግላቸው ነበር:: ይህም አብሮነታችንን ይበልጥ አጠናክሮታል:: በነገራችን ላይ የእኔን ሕይወት የቀረፀው የእድገት በህብረት ዘመቻ ነው:: ልዩ ትዝታ ነው ያለኝ:: የሚገርምሽ ‹‹ሴቶች አይችሉም›› የሚለው አስተሳሰብ የተሰበረው እዚያ እድገት በህብረት ዘመቻ ላይ ነው:: አብረውን የዘመቱ በርካታ ሴት ተማሪዎች አምበርቾ የሚባለውን ትልቁን ተራራ ሳይቀር እየወጡና እየወረዱ ከእኛ እኩል ይሰሩ ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- የመሬት ላራሹ አዋጅን ተከትሎ መሬት ለጭሰኛው እንድታከፋፍሉ በዘመቻው የተሳተፋችሁ ሰዎች ኃላፊነት ተሰጥቷችውም ነበር:: እስቲ ስለዚህ ሥራ ደግሞ በጥቂቱ ያጫውቱን?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** አዋጁ እንደታወጀ የምናስፈፅመው እኛ መሆናችን በይፋ ነበር የተነገረው:: መሬት ወርሰን የምናከፋፍለው እኛው ነበርን:: በወቅቱ በጣም የማረሳው አርሾና ሃላባ አካባቢዎች ሁለት ሰዎች የአካባቢውን መሬት በሙሉ ተቆጣጥረው ነበር:: በአካባቢው የነበሩ በርካታ አርሶ አደሮች የሁለቱ ባላባቶች ጪሰኞች ነበሩ:: እነዚህ ባላባቶች መሬታቸውና ንብረታቸው ሲወረስባቸው አካባቢውን ጥለው ወጥተዋል:: በዘመቻው ውስጥ የተሳተፉ አንዳንድ የባላባት ልጆችም ዘመቻ ጣቢያውን ለቀው የወጡበት አጋጣሚም ነበር:: በተቃራኒው ደግሞ ጭሰኞቹ የመሬት ባለቤት በመሆናቸው ከፍተኛ ደስታ ነበር የተፈጠረባቸው:: ከዚህ ቀደም ግን አመቱን ሙሉ ለፍተው ሲያበቁ የባላባቱን ኪስና ጎተራ ነበር የሚደልቡ የነበረው:: እኛም በተሰጠን ትዕዛዝ መሰረት ለእያንዳንዱ ገበሬ በስም ለይተን መሬት መትረን እንዲሰጥ አድርገናል:: በዚህም ጥሩ ሥራ እንደተሰራ አምናለሁ:: በነገራችን ላይ ባላባቶቹ የነበራቸውን የጦር መሳሪያ ጭምር እንወርስ ነበር::

በመጨረሻ ላይ ግን በዘመቻው ከተሳተፉ ሰዎች ከፊሎቹ ጥለው ጠፍተው ነበር፤ ደግሞ የኢህአፓን በራሪ ወረቀቶች በሽልኩታ እየመጡ እናነብ ስለነበር አንዳንዶቹ ስርዓቱን ወደመቃወም ገቡ:: ከእኛ ጋር የነበሩ የአራተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም፣ ዲሞክራሲ መብቶችና አስተምሮዎችን ያስተምሩናል:: እኛም አጠና አልጋ ላይ ማታ ተኝተን በቃል እየነገሩን እንፅፍ ነበር:: በተለይ ‹‹ዲሞክራሲያ›› ትባል የነበረችው የኢህአፓን መፅሔት ከመንግስት ሰዎች ተደብቀን እንደምንም ተራ ጠብቀን እናነብ ነበር:: በአጠቃላይ ፍልስፍናን ዘመቻ ላይ ሆነን ነው አጥንተን የጨረስነው:: ካነበብን በኋላ ደግሞ ጫካ ውስጥ ተደብቀን እንወያይም ነበር:: በመካከላችን ዘመቻውን እናቋርጥና እንጥፋ፤ አንጥፋ የሚል ውዝግብም ተነስቶ ነበር:: በነገራችን ላይ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አብሮን ከዘመቱ ወጣቶች አንዱ ነበር:: እሱ ግን የዘመተው እዛው ትውልድ ሥፍራው አካባቢ ነበር:: እኩል ብንዘምትም ግን እሱ እንደሄደ ሸፍቶ ደደቢት ነው የገባው::

**አዲስ ዘመን፡- ለመሆኑ የፖሊስ ሰራዊትን የተቀላቀሉበት የተለየ ምክንያት ነበርዎት?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** ፖሊስ ሰራዊትን የተቀላቀልኩት በአጋጣሚ ነው:: ነገር ግን የፖሊስ መኮንኖች ኮፍያ እና ገበርዲን ልብሳቸውን ከልጅነቴ ጀምሮ ነበር እወደው የነበረው፤ ሳየው ገና ደስ ይለኛል:: እንዳልኩሽ ከልጅነቴ ጀምሮ የፖሊስ ፍቅር ቢኖረኝም ሁለተኛ ደረጃ እንዳጠናቀኩኝ በቀጥታ ለመማር የተመዘገብኩት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነበር:: ሆኖም ስድስት ኪሎ ካምፓስ ተመዝግቤ በአፍንጮ በር አድርጌ በእግሬ ወደ ፒያሳ እየሄድኩ ሳለ እሳት አደጋ ጋር ስደርስ አጥሩ ላይ በርካታ ወረቀት ተለጥፎ 200 የሚሆኑ ወጣቶች ትከሻ ለትከሻ እየተጋፉ ወረቀቱ

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

ላይ የተፃፈውን ለማንበብ ሲንጠራሩ ተመለከትኩኝ። እኔም ተሽሎክልኬ የፖሊስ ኮሌጅ ማስታወቂያውን አነበብኩት። እንደአጋጣሚ ሆኖ ደግሞ የትምህርት ማስረጃዬን ይዤ ስለነበር በዚያው ውስጥ ገብቼ እንደሌሎቹ ልጆች ተመዘገብኩኝ። በመሰረቱ መመዝገብ የሚችለው የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪ ነበር፤ እኔ ደግሞ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ ስለነበርኩኝ መዝጋቢዎቹ እኔን ለመመዝገብ አቅማምተው ነበር። ሆኖም ውጤቴ ጥሩ ስለነበር መዘገቡኝ። እናም በዚያ መሰረት ፈተናውን አልፌ ሰንዳፋ ፖሊስ ኮሌጅ ገባሁና ለሶስት ዓመታት የተለያዩ የቀለም ትምህርቶችን ተከታትያለሁ፤ ሶስት ወር ደግሞ በርሃ ተልከን ወታደራዊ ስልጠና ወስደናል። እናም በዚህ መሰረት ነው ሰልጥኜ ወደ ሰራዊቱ የተቀላቀልኩት።

በነገራችን ላይ በኢላማ ተኩስ ከፍተኛ ውጤት በማምጣት በማዕረግ ነው የተመረቅሁት። እንደተመረቅሁኝም በቀጥታ አዲስ አበባ ፖሊስ ትራፊክ መምሪያ የትራፊክ አደጋ ምርመራ፣ ሴፍቲ ጥናትና ምርምር ኃላፊ ሆኜ ነው የተመደብኩት። ስድስት ወር እንደሰራሁ የትራፊክ አደጋ ምርመራ ኃላፊ ሆንኩ። የሚገርመው ያ ቦታ በሙሉ መቶ አለቃ ነው የሚመራው የነበረው፤ እኔ ግን ገና ምክትል መቶ አለቃ ሆኜ ቦታው የተሰጠኝ። ሥራው ግን ውጥረት የተሞላበትና ከባድ ነበር። ያም ቢሆን በብቃት ነው ኃላፊነቴን ስወጣ የነበረው።

**አዲስ ዘመን፡- እንግዲህ የትራፊክ አደጋ ከተነሳ አይቀር በኢትዮጵያ በየቀኑ ከፍተኛ የትራፊክ አደጋ የሚመዘገብበት ምክንያት ምን ይሆናል ብለው ያስባሉ?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** እውነቱን ለመናገር እኔ በሰራሁበት ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ የነበረው ተሽከርካሪ መጠን በጣም ትንሽ የሚባል ነው። መንገዶቹም ብዙ አልነበሩም። የነበረው አደጋ ብዛት ግን ከፍተኛ የሚባል ነበር። አሁንም ቢሆን አደጋው እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይደለም። እኔ በነበርኩበት ጊዜ በተለይ ትምህርት ቤቶች አካባቢ ያለውን አደጋ ለመቀነስ የተማሪ ትራፊክ ፖሊስ ማሰልጠን የሚያስችል ጥናት በማጥናት እንዲጀመር አድርጊያለሁ። በዚያ መሰረትም ከየሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ተመልምለው እንዲሰለጥኑ ተደርጓል። ይህም አደጋውን ለመቀነስ ለምንሰራው ሥራ ከፍተኛ እገዛ አድርጎልናል ብዬ አምናለሁ።

ከዚህ ቀደምም ሆነ አሁን አደጋው እየሰፋ የመጣው በአሽከርካሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ግዴለሽነት ያለ በመሆኑ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን የእውቀት ማነስም አለባቸው። ሹፌር የተባለ ሁሉ እኩል ሹፌር አይደለም፤ ሁሉም ደንብና ስርዓትን ጠብቆ የሚያሽከረክር አይደለም። ብዙዎቹ በትንሽ ቦታ ላይ ፍጥነት መቆጣጠር አይችሉም። አሁንም ድረስ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ያለው የፍጥነት ወሰን ያለመጠበቅ ችግር ነው። ሁልጊዜም ቢሆን ፍጥነት ካለ አሽከርካሪው ሊያድነው የሚችለውን ሰው ይገጨዋል። አሁንም እንደምናየው ብዙ አደጋ ነው በየቀኑ እየደረሰ ያለው። ስለዚህ ይህንን ችግር መፍታት የሚቻለው ለማንኛውም አሽከርካሪ መንጃ ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት በቂ እውቀትና ግንዛቤ መስጠት ስንችል ነው የሚል ሃሳብ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ራሺያ ለትምህርት ሄደው እዚያው እንዲቀሩ ጥያቄ ቀርቦሎት ሳይቀበሉ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱበት ምክንያት ምን ነበር?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** ልክ ነሽ፤ ትምህርቴን በጨረስኩበት ወቅት ደርግ ወድቆ ወያኔ በትረ-ስልጣኑን ሲረከብ የራሺያ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፖለቲካ ጥሩ ባለመሆኑ እዚያው እንድንቀርና ሥራም ሆነ አስፈላጊው ሁኔታ እንደሚመቻችልን ነግረውን ነበር። ሆኖም ያስተማረን አገርና ህዝብ እንደመክዳት ስለቆጠርኩት አሻፈረኝ ብዬ ለመመለስ ወሰንኩኝ። እኔ ብቻ ሳልሆን ሌሎች ከእኔ ጋር የነበሩ ኢትዮጵያኖችንም ሳይቀር አስተባብሬ ነው ይዤያቸው የመጣሁት። እንደመጣሁም ያስተማረኝ ተቋም አላሰፈረኝም፤ አስራ አምስት ቀናት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የፖሊስ ምህንድስና ዋና መምሪያ ኃላፊ አድርጎ መደበኝ።

በዚያ ኃላፊነት ላይ መስራት እንደጀመርኩ ደግሞ የአገሪቱ አጠቃላይ ችግር ወደ እኔ መምጣት ጀመረ። ምክንያቱም በየክልሉ ያሉ በርካታ የፖሊስ ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ ቢሮ የላቸውም ነበር። በወቅቱ አንድ ለእናቱ በሚባል ደረጃ እኔ ብቻ ነበርኩኝ በፖሊስ ሰራዊት



ውስጥ ዋና መሃንዲስ የነበርኩትና የግንባታ ሥራዎች ጉዳይ ሁሉ ወደ እኔ ቢሮ ነበር የሚመጣው። በየክልሉ እየዞርኩኝ ከቦታ መረጣ ጀምሮ የፖሊስ ተቋሞችን ህንፃ እስከመስራትና ግንባታውን እስከመቆጣጠር ድረስ ኃላፊነት ተጥሎብኝ ነበር።

ከሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ደግሞ ከባድ የህንፃ ዲዛይን ስራዎች ይመጡ ጀመር። የየክልሎቹን፤ የአዲስ አበባና የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ዘመናዊ ህንፃ ዲዛይኖችን እንዲሰሩ ጥያቄ ቀረበልኝ። በዚያ ወቅት የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ራሱ የራሱ ህንፃ አልነበረውም፤ ዝም ብሎ የጣሊያን ዳሳሳ ቤት ውስጥ ነበር ይሰሩ የነበሩት። እናም አሁንም ድረስ የምኮራበትና ደስ የሚለኝ ነገር አሁን የምናየውን ትልቁን የፌደራል ፖሊስ ህንፃ ዲዛይን መስራቴ ነው። የሚገርምሽ ይህ ዲዛይን የተመረጠው አስር ዲዛይን ሰርቼ ከእነዚያ ውስጥ ነው።

ሰመራ ከተማ ያለው የአፋር ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ህንፃ ዲዛይንም እኔ የሰራሁት ነው። የዚያ ዲዛይን መሰራት ተከትሎ ነው ከተማዋ እየተስፋፋችና እያደገች የመጣችው። በተመሳሳይ የሱማሌ ክልል ፖሊስ ህንፃን፤ የአዲግራት ፖሊስ ማሰልጠኛን፤ የሐረር ፖሊስ ማስፋፊያ ህንፃና በርካታ ተቋማትን ህንፃ ሰርቻለሁ። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ በሙያዬ ምክንያት አካልያለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- እንደፌደራል ፖሊስ ያሉ ትልልቅ ህንፃዎች መሰራት በተለይ ለከተሞች እድገትና መስፋፋት ምን አበርክቶ አምጥቷል ብለው ያምናሉ?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** ይሄ ምንም ጥርጥር በሌለው መልኩ ትልልቅ ህንፃዎች መሰራት ከከተማ ውበት ባሻገር እድገት እንዲመጣ፤ ዘመናዊ ከተማ እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል ባይ ነኝ። በተለይም እንደ ፖሊስ ያሉ ህዝባዊ ተቋማት ደረጃውን በጠበቀና እንዲህ ባማረ መልኩ ህንፃ መሰራቱ አሰራራቸውንም በዚያው ልክ እንዲያዘምኑ፤ ደህንነታቸውና ሚስጢራዊነታቸውም የተጠበቀ እንዲሆን አስችሏል። እኔም እንደአንድ ባለሙያ ይህንን የፌደራል ፖሊስን ከነበረበት ዳሳሳ ጎጆ ወጥቶ በዚህ ያማረ ህንፃ ባለቤት እንዲሆን በማድረጌ በጣም ደስተኛ ነኝ። በነገራችን ላይ ይህ ህንፃ ከመሬት ውስጥ ጀምሮ እስከ ሂሊኮፍተር ማረፊያ ድረስ ያለው ግዙፍ ህንፃ በመሆኑ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፖሊስ ተቋም እንዲሆን የላቀ ሚና አለው። አሁን ቢሆን እንደጊዜው እየታየ ዘመናዊ ህንፃዎችን መገንባት አለበት። ይህ ሲሆን ነው ከተሞችንም ሆነ አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ የምንችለው።

> **በእኔ እምነት አሁን ያለው ትውልድ ከትምህርት ስርዓቱ ጀምሮ አገሩን እንዲወድና በአንድነት አገሩን እንዲያሳድግ ተደርጎ አልተቀረፀም። ይህም በመሆኑ ነው አሁን ላይ የምናየው የመከፋፈል ችግር እየተፈጠረ ያለው።**

**አዲስ ዘመን፡- በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ከተሞች የሚገነቡ ህንፃዎች ለህዝቡ የሚመቹና ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን እንዲገነቡ በማድረግ ረገድ ያለው ክፍተት ምንድን ነው?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** አንድ ከተማ አደገ የሚባለው በርካታ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ስለተገነቡ አይደለም። በተለይም በህንፃው የሚገለገለውንም ሌላውንም ማህበረሰብ ያማከለ፤ ከአጠቃላይ የከተማዋ ማስተር ፕላን ጋር የተናበበ ሊሆን ነው የሚገባው። ከዚህ አንፃር አንቺም እንዳልሽው በተለይም በአዲስ አበባ ብዙ የሚታዩ ችግሮች አሉ። የሚገነቡት ህንፃዎች አሁን ያለውን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱንም ትውልድ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ህንፃው በተገናባበት አካባቢ የሚሰራውን ስራ ማጤን የግድ ይላል። ህንፃ ብቻ መስራት እድገት አያመጣም፤ ጠቢባንም አያደርገንም። ይልቁንም የሰው አስተሳሰብ መቀየርና ከዘመኑ ጋር የሚሄድ አድርጎ መቅረፅ ያስፈልጋል። ደግሞም የትኛውም መሰረተ ልማት የሚገነባው ለህዝብ ጥቅም እንደመሆኑ ከግባታው ጎን ለጎን የህዝቡን ኑሮ መለወጥ ያሻል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያዊነትን እንዴት ይገልፁታል?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** ኢትዮጵያዊነት ለእኔ ሁሉም ነገሬ ነው። አገሬን ከምንምና ከማንም በላይ ነው የምወዳት። አስቀድሜ እንዳልኩሽም ውጭ የመኖር አማራጭ እያለኝ ጥዬ የመጣሁት አገሬን ስለምወዳትና ለአገሬና ለህዝቤ የበኩሌን ድጋፍ ማድረግ አለብኝ ብዬ ስለማምን ነው። ከልጅነቴ ጀምሮ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እንድወድ ተደርጌ በመቀረፄ አገሬን ሲነኩብኝ አልወድም። በሌላ በኩል ካለፉት 30 ዓመት ወዲህ ኢትዮጵያዊነትን የሚከፋፍል ስርዓት በመምጣቱና ትውልዱም እኔ ብቻ ብሎ እንዲቀረፅ መደረጉ ያሳዝነኛል። በግሌ አንዱን ብሔር ከሌላው የሚለያይ አስተሳሰብን አልቀበለውም። ለእኔ ሁሉም የሰው ልጅ እኩል ነው። ደግሞም ከምን በፊት ሰው መሆን ይቀድማል ብዬ ነው የማምነው።

በእኔ እምነት አሁን ያለው ትውልድ ከትምህርት ስርዓቱ ጀምሮ አገሩን እንዲወድና በአንድነት አገሩን እንዲያሳድግ ተደርጎ አልተቀረፀም። ይህም በመሆኑ ነው አሁን ላይ የምናየው የመከፋፈል ችግር እየተፈጠረ ያለው። ለዚህ ሁሉ ችግር ተጠያቂ የሚሆነው ግን የፖለቲካ ስርዓቱ ነው። በወታደራዊ ቋንቋ «ተመልከት አላማህን፤ ተከተል አለቃህን» እንደሚባለው ሁሉ ትውልዱም እንዲህ አገር ጠልና ራስን ብቻ አፍቃሪ የሆነበት ምክንያት በፖለቲካው ስርዓትና በነበሩን መሪዎች ምክንያት ነው ባይ ነኝ። አሁንም ቢሆን አገር ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት የፖለቲካም ሆነ የትምህርት ስርዓቱ መፈተሽና መስተካከል አለበት ብዬ አምናለሁ። ትውልዱንም በኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ መቅረፅ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ እስቲ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ምን ሲሰራ እንደሚገባ ይግለፁልንና ውይይታችን በዚሁ እናብቃ?**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** ልክ ነው፤ ከምንም በፊት የአገር ሰላምን ማረጋገጡ ቀዳሚ ሥራ ሊሆን ይገባል። እንዳልኩሽ አሁን የምናየው መከፋፋል ቀርቶ ወደ አንድነት መምጣትና አገራችን ከገባችበት ችግር ለማውጣት መረባረብ አለብን። ከምንም በላይ በፖለቲከኞች አለመግባባት ምክንያት እየሞተ ያለውን ንፁህ ሕይወት ዜጋ ሕይወት መታደግ አለብን። በእውነቱ በሰሜን ኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች በተፈጠረው ግጭት በግፍ እያለቀ ያለው ዜጋ በጣም ነው የሚያሳዝነኝ።

በእኔ እምነት ይህ ጦርነት መቋጫ ሊበጅለት ይገባል። ፖለቲከኞች ተቀራርበው መነጋገርና ለአገር ዘላቂ ሰላም ዋጋ መክፈል አለባቸው ባይ ነኝ። አሁን ላይ በመንግስትና በወያኔ ሰዎች መካከል እየተደረገ ስላለው ድርድር መረጃ ባይኖረኝም ግን ድርድሩ የሁሉንም ህዝብ ጥቅም የማከለ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ። በነገራችን ላይ በዚህ ጦርነት ምክንያት ህዝብ ሳይሆን እየጠፋ ያለው ተፈጥሮም ጭምር ነው። እንዳየነውም ከሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳቱ ባሻገር ብዙ ሃብት ሊሰጠን የሚችል መሬት ሳይቀር ነው ጉዳት የደረሰበት።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ሻለቃ ኢንጂነር ወ/ሚካኤል፡-** እኔም ለሰጣችሁኝ እድል ከልብ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ቅድመ ስኳር በሽታ (Pre-diabetes)



አካንቶሲስ ናይግሪካንስ (Acanthosis nigricans): አንዳንድ የስኳር እና የቅድመ-ስኳር በሽታ ህመምተኞች ላይ የሚታይ ምልክት።

**የቅደመ ስኳር በሽታ (Pre-Diabetes) ምንድነው?**

**በደም ውስጥ ያስ ግሉኮስ መጠን ሲጨምር ነገር ግን የስኳር በሽታን ያህል ከፍተኛ ካልሆነ ቅድመ ስኳር በሽታ ወይም ፕሪ ዳያቤቲስ (pre-diabetes) ይባላል።** በደም ጉሉኮስ (በባዶ ሆድ) ምርመራ ላይ 100 እስከ 125 ሚሊግራም በዴሲሊትር ወይም በኤዋንሲ(A1C) ምርመራ ከ 5.7% – 6.4% ያሳያል።።

**በጤና ላይ የሚያስከትለው ችግር**

የደም ግሉኮሱን ካልተቆጣጠረ ቅድመ ስኳር በሽታ ያለበት ሰው ለስኳር በሽታ በከፍተኛ ደረጀ የተጋለጠ ነው። በተለይ ከ60 አመት እድሜ በታች ከሆነ፣ ውፍረት ካለ፤ በእርግዝና ጊዜ የደም ግሉኮስ ከፍተኛ ከነበረ ወደስኳር በሽታ የመለወጥ እድሉ ከፍተኛ ነው።

በምርመራ ይህ የታወቀለት ሰው እራሱን እንደ እድለኛ መቁጠር ይችላል። ምክንያቱም ህመሙ ከፍቶ በስኳር በሽታ ሰበብ የሚመጡ በሽታዎች ሳይከሰቱ በፊት የጤናውን ሁኔታ ማወቅ ችሏል። ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ፤ አመጋገቡን በማስተካከል፤ የአካል እንቅስቃሴ በማድረግ፣ የሃኪሙን ምክር በመከተል ቅድመ ስኳር በሽታ ወደ ስኳር በሽታ እንዳይሄድ ለማድረግ እድል አለው።

**ምልክቶች**

በዚህ ደረጃ ላይ እያለ ህመምተኛው ምንም ምልክት ላያሳይ ይችላል። አንዳንድ ሰዎች አንገታቸው፣ ብብታቸው፣ ጉልበታቸው፣ ክርናቸው፣ ወይም የጣታቸው መተጣጠፊያ ላይ የሚገኝ ቆዳቸው በተለየ መልኩ ይጠቁራል። ይህ ጥቁረት አንዳንዴ እድፍ ይመስላል። ነገር ግን እንደእድፍ በመታጠብ አይለቅም። ከዚህ ውጭ የማይረካ የውሃ ጥም፣ ቶሎ ቶሎ የረሃብ ስሜት ሲሰማዎ፣ እና አሁንም አሁንም የውሃ ሽንት የሚለው ከሆነ ህመሙ ወደስኳር በሽታ መለወጡን ጠርጥረው ለሃኪም ማማከር ተገቢ ነው።

**ህክምና**

የቅድመ ስኳር በሽታ ያለበት ሰው፤ እንደዶክተሩ ምክር የደም ግሉኮሱን በየግዜው መታየት አለበት። የደም ግፊት ወይም እና ኮሌስትሮል ካለ በቂ ህክምና ማድረግ ለህመምተኛው ጤና ይመከራል። አንዳንድ ዶክተሮች የህመምተኛውን አጠቃላይ ጤና በማየት ሜትፎርሚን የተባለ ክኒን ያዛሉ። ይህ መድሃኒት የስኳር በሽታን ለማዘግየት እንዲሁም የደም ግሉኮስን ለመቀነስ ለብዙ ስኳር በሽተኞች ይታዘዛል። ምንም መድሃኒት ባይታዘዝ እንኳን አመጋገብ መለወጥ እና የሰውነት እንቅስቃሴ ማድረግ ለወደፊቱ ጤንነትዎ አስፈላጊ መሆኑን አይዘንጉ።

**ሜትፎርሚን ስምን በሽታ ይታዘዛል?**

ሜትፎርሚን አይነት 2 ስኳር በሽታ (Type II diabetes mellitus) ያለባቸው ሰዎች፤ በደማቸው ያለውን የግሉኮስ መጠን ለማስተካከል የሚታዘዝ መድሃኒት ነው።

በተጨማሪ፤ ሜትፎርሚን ለሌሎች ህመሞች ሊታዘዝ ይችላል። ቅድመ ስኳር በሽታ(Pre-diabetes)፣ በእርግዝና ጊዜ ለሚከሰት የስኳር በሽታ(Gestational Diabetes)፣ ፓሊሲስቲክ ኦቫሪ ሲንድሮም(Polycystic ovary syndrome) ለተባለ የሴቶች የማህጸን ህመምን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

**ሜትፎርሚን እንዴት ነው የሚሰራው?**

ሜትፎርሚን በደም ውስጥ ያለውን ግሉኮስ በተለያየ መንገድ ይቀንሳል።

- ኢንሱሊንን በመርዳት ከደም ውስጥ ወደጡንቻ ህዋስ የሚገባውን ግሉኮስ መጠን ይጨምራል።
- ጉበት ውስጥ የተከማቸውን ግላይኮጅን(glycogen) ወደግሉኮስ እንዳይለወጥ ይረዳል። ይህም ከጉበት ወደ ደም የሚገባውን የግሉኮስ መጠን እንዲቀንስ ያደርገዋል።
- በምግብ ልማት ከትንሿ አንጀት የተገኘውን ግሉኮስ ወደ ደም ስርአት ሲገባ እንዲቀነስ ያደርገዋል።

እነዚህን መንገዶች ተጠቅሞ በደም ውስጥ ያለውን የግሉኮስ መጠን እንዲቀንስ ያደርጋል። ሜትፎርሚን፤ የስኳር በሽታን ይቆጣጠራል እንጂ አያድንም። የደም ግሉኮስ መጠን ቢስተካከል እንኳን፤ መድሃኒትዎን መውሰድ እንዳያቋርጡ። አመጋገብን መቆጣጠር እንዲሁም የሰውነት እንቅስቃሴ ማዘውተር፤ የስኳር በሽታ ህክምና አካል መሆኑን አይዘንጉ።

**ሜትፎርሚን በምን መልኩ ታሽጎ ይመረታል?**

በአፍ የሚወሰድ ክኒን(tablet) ወይም በብጥብጥ ፈሳሽ (solution) መልክ ይዘጋጃል። የሜትፎርሚን ክኒን ቶሎ የሚሰራ(immediate release) ወይም ዘግይቶ የሚሰራ(long acting or extended release) ሊሆን ይችላል። ከተዋጡ በኋላ ዘግይተው የሚሰሩ (long acting or extended release) መድሃኒቶችን መስበር፣ ማኘክ፣ ወይም መዳመጥ የለብዎትም።

**ከመጠቀምዎ በፊት ማወቅ ያስብዎት ምንድነው?**

- እርጉዝ ሴት ከሆኑ፦ ሜትፎርሚን በጽንስም ሆነ በነፍሰጡር ሴት ጤና ላይ ችግር አያስከትልም።
- የሚያጠቡ እናት ከሆኑ፦ ሜትፎርሚን በጡት ወተት ውስጥ ስለሚኖር አማራጭ መንገድ ለመፈለግ ዶክተርዎን ያማክሩ።
- ሜትፎርሚንን በሚወስዱበት ጊዜ አልኮል መጠጣት አይመከርም።
- ለረጅም ጊዜ ሜትፎርሚን የሚወስዱ ሰዎች የቫይታሚን ቢ12 ማነስ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ይህ ቫይታሚን የአእምሮ እና የደም ጤንነት ላይ አሉታዊ ሚና አለው። ብዙ ጊዜ ቫይታሚን ቢ12 ከአሳ፣ ከእንቁላል፣ እና ከስጋ ምግቦች ይገኛል። ነገር ግን ሜትፎርሚን የሚወስዱ ሰዎች፤ ቫይታሚኑ ከአንጀታቸው ወደሰውነታቸው በሚገባ መልኩ አይሰርግላቸውም። ዶክተርዎ የምርመራ ውጤትዎን አይቶ ካስፈለገ ይህን ቫይታሚን በክኒን መልክ ሊያዝልዎት ይችላል።

**የሜትፎርሚን ትክክለኛ አወሳሰድ**

የሀኪምዎን ትእዛዝ በጥንቃቄ ይከተሉ። የሚወስዱበት ሰአት፦ ዘግይቶ የሚሰራ (Extended Release, Long Acting) ሜትፎርሚን ከሆነ በእራት ሰአት ይውሰዱ። የተቀሩት የሜትፎርሚን አይነቶች ቀንም ሆነ ማታ መውሰድ ይቻላል። በየእለቱ በተመሳሳይ ሰአት መዋጥ መድሃኒትዎን ሳይረሱ እንዲወስዱ ይረዳዎታል።ሜትፎርሚንን ከምግብ ጋር መውሰድ ይመከራል።

**መድሃኒቴን መዋጥ ከረሳሁ ምን ማድረግ አስብኝ?**

ወዲያው እንዳስታወሱ ይውሰዱ። ብዙ ሰአት ካለፈ ይተውት እና በሚቀጥለው የመድሃኒት መውሰጃ ጊዜዎ የተለመደውን መጠን ይዋጡ። የረሱትን ጨምረው ለመዋጥ እንዳይሞክሩ።

**በዚህ መድሃኒት ምክንያት ሲከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮች**

ሜትፎርሚን የሚወስዱ ሰዎች ብዙ ጊዜ ይስማማቸዋል። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ሜትፎርሚን ሲወስዱ የሆድ ህመም ሊያጋጥማቸው ይችላል። ለምሳሌ ያህል ተቅማጥ/ድርቀት፣ የምግብ አለመንሸራሸር፣ ፈስ(flatulence/gas ) እና ሆድ መጮህ፣ አፍ ላይ የብረት ጣእም እንዲሁም ሆድን የመጭነቅ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ይህ ምልክት ከጊዜ በኋላ ይጠፋል። ከምግብ ጋር መውሰድ እነዚህን ምልክቶችን ለመቀነስ ይረዳል። ከሚችሉት በላይ ከሆነ ግን ሃኪምዎን ያማክሩ።

አንዳንድ ዘግይቶ የሚሰራ (ግሉኮፌጅ ኤክስ-አር (Glucophage XR)፣ ፎርታሜት (Fortamet) ወይም ግሉሜትዛ (Glumetza)) የተባሉት የሜትፎርሚን መድሀኒቶች የሚወስዱ ሰዎች በሰገራ ውስጥ ክኒን የሚመስል ነገር ሊያዩ ይችላሉ። ይህ ምንም ችግር የለውም። እነዚህ መድሃኒቶች በ24 ሰአት ውስጥ መድሃኒቱን ቀስ በቀስ እንዲለቁ የሚያደርጋቸው የሚጠቀለሉበት ነው። ይህ ለየት ያለ መጠቅለያ በጨጓራም ሆነ በአንጀት ላይብላላ ይችላል። መድሃኒቱን ግን እንደማጥለያ ቀስ እያለ ማሳለፍ ይችላል። ስለዚህ በሰገራ ውስጥ ክኒኑ እንዳለ የወጣ ይመስላል። ውስጡ መድሃኒት የለም፤ ባዶ ቀፎ ነው።

**ለዚህ መድሃኒት የሃኪም ክትትል ያስፈልገኛል?**

እንደዶክተርዎ ምክር፣ በአመት አንድ ጊዜ ወይም በየመንፈቁ፣ አንዳንዴ በየሶስት ወሩ ሀኪምዎ ጋር መሄድ ያስፈልጋል። የኩላሊትዎን ጤንነት እና በደምዎ ያለውን ቫይታሚን ቢ12 በየጊዜው መመርመር ሜትፎርሚንን ለጤናዎ ጥቅም እንጂ ጉዳት እያስከተለ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ይረዳል። በተጨማሪ የደም ግሉኮስ እና ኤዋንሲ(A1C) በየጊዜው መለካት ያስፈልጋል።

**መድሃኒቱ መቀመጥ ያለበት ቦታ**

መድሃኒትዎን፤ ሙቀት እና ቅዝቃዜ የማይበዛበት፤ ደረቅ ቦታ ያስቀምጡ። መድሃኒትን መታጠቢያ ቤት ማስቀመጥ አግባብ አይደለም። ህጻናት እና የቤት እንስሳት የማይደርሱበት ቦታ ያስቀምጡ።

**የላክቲክ አሲዶሲስ(Lactic Acidosis) ማስጠንቀቂያ**

የኩላሊት ህመም ያለባቸው ሰዎች፤ ሜትፎርሚንን ከሰውነታቸው በሚገባ መልኩ አያስወግዱም። ሜትፎርሚን በሰውነት ሲከማች ለጤና አስጊ የሆነ ላክቲክ አሲዶሲስ የተባለ ህመም ሊከሰት ይችላል። ይህ የሚከሰተው እጅግ አልፎ አልፎ ቢሆንም፤ ምልክቶቹን እና ቢከሰት ምን ማድረግ እንዳለብዎ ማወቅ አይከፋም።

የላክቲክ አሲዶሲስ ምልክቶች የጡንቻ ህመም፣ የመተንፈሻ አካላት መጨናነቅ፣ በጭንቅ መተንፈስ፣ ቶሎ ቶሎ አየር መሳብ፣ ጥልቅ ድካም መሰማት፣ማንቀላፋት፣ እና የሆድ መጨነቅ ናቸው።

**ስመከላከል**

ቅድመ ስኳር በሽታን ለመከላከል የሚረዱ እርምጃዎች ቅድመ ስኳር በሽታ ወደ ስኳር በሽታ እንዳይሄድ ከሚረዱት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። እነዚህም፣ የተመጣጠነ ጤናማ ምግብ መመገብ፣ በሳምንት ቢያንስ 150 ደቂቃ (በየእለቱ ቢያንስ ሃያ ደቂቃ) እንደሩጫ ያለ ስፖርት መስራት፣ ውፍረት መቀነስ፣ የሚያጨሱ ከሆነ መተው፣ እንዲሁም ከፍተኛ የደም ግፊት ወይም ኮሌስትሮል ካለብዎ ህክምና መከታተል ናቸው።

# ነፃ ሃሳብ

## የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛው ዙር ውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቅን አስመልክቶ ትናንት ያስተላለፉት የእንኳን ደስ አለን መልዕክት!

## "የሚገባንን ተጠቅመን፣ የሚገባቸውን ለወንድሞቻችን ሰጥተን በጋራ ለማደግ በእኛ በኩል ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ እገልጻለሁ"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣



ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ እንዲሁም በዚህ ስፍራ በዚህ ታሪካዊ ፕሮጀክት ውስጥ በእውቀት፣ በጉልበት የተሳተፋችሁ የኢትዮጵያ ድንቅ ልጆች፤ ከዚህም ባሻገር የዚህን ፕሮጀክት ጠቃሚነት ተገንዝባችሁ ኢትዮጵያን በሀሳብና በተለያየ መንገድ ስትረዱ የቆያችሁ የኢትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ፤ ዛሬ በዚህ ስፍራ ሦስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቁን ሳበስርላችሁ በታላቅ ደስታ ነው:: ዛሬ ከጀርባዬ የምትመለከቱት (የውሃው ፍሰት ከጀርባቸው እያስመለከቱ ስለሚናገሩ የተጠቀሙት ቃል ነው) የሦስተኛው ሙሌት የውሃ በላይ መፍሰስ (ኦቨር ቶፕ ማድረግ) እየተከናወነ ይገኛል::

ይህ ክንውን አምና ከነበረው ጋር ለማነጻጸር ብንሞክር፤ አምና በመሃከል ውሃ የሚፈስስበት ቦታ 575 ሜትር ነበር:: ዘንድሮ ተጨማሪ 25 ሜትር ከፍ በማድረግ 600 ሜትር ላይ የውሃው ፍሰት ይታያል:: ግራና ቀኝ አምና 585 ሜትር ነበር:: ዘንድሮ 611 ሜትር በመድረስ በከፍተኛ ደረጃ ውሃ የመያዝ አቅምችንንና ኃይል የማመንጨት(ኢነርጂ ጀነሬት የማድረግ) አቅማችንን ከፍ አድርጎታል:: ይህ በዚህ ስራ ለተሳተፉ ሰዎች ሁሉ እና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ደስታን የሚፈጥር ታላቅ ድል ስለሆነ እንኳን ደስ ያላችሁ፤ እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ::

ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት፣ ዓባይ የእኛ የፈጠራ ውጤት አይደለም:: ዓባይ የፈጣሪ ስጦታ ነው:: ይህ የፈጣሪ ስጦታ በአግባቡ እንድንጠቀምበት፣ በአግባቡ እንድንገለገልበት ታስቦ የተሰጠን ነው:: ፈጣሪ እጅ ሰጥቶናል፤ እጃችንን በአግባቡ መጠቀም ማረስ፣ መዝራት፣ መነገድ፣ መገንባት፣ የእያንዳንዱ በነጻ እጅ የተሰጠው ሰው ኃላፊነት ይሆናል:: ዓይን በነጻ ተሰጥቶናል:: ዓይናችንን በአግባቡ መጠቀምና መገልገል የእያንዳንዱ በነጻ የተሰጠው ሰው ኃላፊነት ይሆናል:: ከተሰጠው በኋላ የማይጠቀም ሰው ቢኖር ተወቃሹ እሱ እንጂ ሰጪው ሊሆን አይችልም:: በዚሁ አግባብ ዓባይ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ተሰጥቷል::

ለዓለም የተሰጠበት መንገድ የዓለም ሕዝቦች አስፈላጊ ነው ብለው በሚያምኑበት በማንኛውም ጊዜ በዚህ ስፍራ መጥተው ሊዝናኑ፣ ሊያዩ፣ ጊዜያቸውን በደስታ እንዲያሳልፉ የሚያስችል ከፍተኛ ብቃት አለው:: በዚህ ግድብ ምክንያት ከኋላ በምናየው ቦታ(ውሃው የተኛበትን ቦታ) 70 ገደማ ደሴቶች (ሃይ ላንዶች) አሉ:: እነዚህ ደሴቶች ከ40 በላይ የሚሆነው ደሴት እያንዳንዱ ከ10 ሄክታር በላይ ቦታ ይዟል:: አንዳንዶቹ 800 ሄክታር፣ ከ2ሺህ ሄክታር በላይም ደሴት የሆነ ቦታ ይገኛል:: ዝቅተኛው ደሴት(ሃይ ላንድ) አምስት ሄክታር የሚይዝ ነው:: እያንዳንዱን ሃይላንድ(ደሴት) አንዳንድ ሪዞርት ብናደርግ፣ በመሃል ከውሃ ጋር የሚደረጉ ጫወታዎችን ብንጨምር ከፍተኛ የሆነ የዓሣ ምርት በዚህ ቦታ አለ:: እስከ 70ና 80 ኪሎ የሚመዝኑ ዓሣዎች አሉ:: እናም ዓሣን በማጥመድ ደስታን የሚያገኙ ሰዎች ቢኖሩ መጥተው ሊዝናኑበት ይችላሉ::

አካባቢውን እንደምታዩት እጅግ ተራራማ እና በጣም ሲበዛ አረንጓዴ(ግሬን) ቦታ ነው:: ተራራውን ለሃይ ኪንግ፣ እንዲሁም አረንጓዴ ስፍራውን ለተለያየ መዝናኛ መጠቀም ይቻላል:: ከዚህ አንጻር ዓለም መጥቶ በዚህ ቦታ ላይ ለመዝናናት የሚያስችለው ትልቅ ስጦታ ነው:: ነገር ግን ግድቡ ከመገደቡ በፊት እንደዚህ አይነት ደስታ በዚህ ቦታ ማግኘት አይቻልም ነበረ:: ሙቀቱ ብቻ ሳይሆን የውሃው መቆየት በራሱ ደሴት ፈጥሯል፤ ዓሣ ፈጥሯል፤ በጣም በርካታ የተፈጥሮ ሃብቶቻችንን አጉልተን የምናይበትን እድል ፈጥሮልናል:: እናም ዓለም ከዚህ አንጻር መገልገል የሚችልበት ቦታ መሆኑን ተገንዝቦ ለመጠቀም ዝግጁ መሆን፤ ኢንቨስት ለማድረግ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል::

ሁለተኛው በነጻ ተቀባይ አፍሪካ ነው:: አፍሪካ የኢኮኖሚ ትስስር ብሎ ካፀደቀ ዓመታት ተቆጥረዋል:: እናም የኢኮኖሚያዊ ትስስር አንዱ መንገድ ኢነርጂ(ኃይል)ን ለጎረቤት አገሮች መሸጥ ነው:: ይህ ኃይል ሙሉ በሙሉ ሲመነጭ ለእኛ ጎረቤቶች ብቻም ሳይሆን ከዛም ተሻግሮ ሊጠቅም የሚችል ነው:: ለዜጎቻችን ይጠቅማል፤ እኛም ለጎረቤት ሕዝቦች ኃይል በመሸጥ እንዲገለገሉ ለማድረግ ያስችላል:: ያስተሳስራል፤ በጋራ እንድንለማ፤ በጋራ እንድናድግ እድል ይከፍታል::

ሦስተኛው በነጻ የተሰጣቸው አገራት፣ ሦስቱ አገራት ናቸው፤ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን እና ግብጽ:: እነዚህ ሶስቱ በነጻ ይሄን ውሃ የመጠቀም እድል የተሰጣቸው አገራት፤ የሚገባቸውን ድርሻ በአግባቡ መጠቀም ከቻሉ ለእነሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የአፍሪካ ወንድምና እህቶችም ጭምር መጥቀም የሚችሉ በርካታ ስራዎች ሊሰሩ ይችላሉ:: እነዚህ ሶስት አገሮች የተሰጣቸውን መገንዘብ፣ በተሰጣቸው ልክ መተባበር እና በጋራ መቆም ከእነሱ ይጠበቃል:: ነገር ግን ዓባይ ለሶስቱ አገራት እንደተሰጠ፣ ሶስቱም በሚገባቸው ድርሻ መጠቀም እንዳለባቸው የማያምኑ ኃይሎች ካሉ የተፈጥሮን ሕግ ያዛባሉ::

ዓባይ ለእኛ ብቻ የተሰጠ ቢሆን ኖሮ ልክ እንደ አዋሽ እዚሁ በቀረ ነበር:: ወይም ወደ ደቡብ፣ ወደ ምስራቅ በፈሰሰ ነበር:: ዓባይ በተፈጥሮ ይሄንን ኮርስ(የፍሰት መስመር) ሲይዝ እኛ የሚገባንን ተጠቅመን የሱዳንና የግብጽ ወንድሞቻችንም እንዲጠቀሙበት ሰጪው በነጻ የሰጠን ስፍራ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ለዚህም ኢትዮጵያ ለሺህ ዓመታት ዓባይን ሳትጠቀም በመቆየቷ ከፍተኛ ቁጭትና ሃዘን ይሰማታል:: ለሺህ ዓመታት የተሰጣትን ዓይን አላየችበትም ማለት ነው:: የተሰጣትን እጅ አልሰራችበትም ማለት ነው:: ዛሬ ግን እጅግ ደስታ የሚሰጥ ኩልል ያለ ውሃ በዚህ ስፍራ ማየት ይቻላል:: በርካታ ዓሣዎች እያጠመዱ መመገብ ይቻላል:: አጠቃላይ አካባቢውን ለቱሪዝም ምቹ አድርጎ መጠቀም የሚያስችል እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሃብት፤ ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት ብሉ ጎልድ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

ሰው እና አገር የሚመሳሰል ባህሪ አላቸው:: አንድ ሰው ምንም እንኳን በተፈጥሮው የሚያምር ቁመና ቢኖረውም በቂ ምግብ ካላገኘ፣ ቆንጆ ልብስ ካልለበሰ፣ ካልታጠበ ያ ሰው የቆሸሸ ነውና መልካም ስፍራ ላይ የማይኖር ስለሆነ ሰዎች በቀላሉ ደሃ መሆኑን፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖር ሰው መሆኑን ተገንዝበው ናቅ አድርገው ሊያዩት ይችላሉ:: ሰው በተፈጥሮ የተሰጠው ቁመና ብቻ ሳይሆን በምግብ፣ በንጽህና፣ በአለባበስም ጭምር የሚቀየር ስለሆነ:: አገርም እንደዚሁ ናት:: ምንም እንኳን በተፈጥሮ እጅግ ያማረ ፀጋ የተሰጣት አገር ብትሆንም፤ ያንን አልምታ ተጠቅማ፣ ከልመና ወጥታ ለሌሎች ማሳየት ካልቻለች፤ ልክ በጎዳና በቆሸሸ ባደፈ ልብስ እንደሚታየው ሰው ዝቅ ተደርጋ ልትታይ ትችላለች::

ኢትዮጵያን ደሃ ያሰኛት፣ ኢትዮጵያን ለማኝ ያሰኛት ስላልተሰጣት አይደለም:: እጅግ አስደማሚ የሆኑ የተፈጥሮ ፀጋዎች አሏት:: ነገር ግን ወንድ እና ሴት ልጆቿ በተባበረ መንፈስ በጋራ ቆመው፣ የአገርን ጥቅም አስቀድመው ለልማት ቅድሚያ ሰጥተው መስራት ባለመቻላቸው ነው እንጂ፤ በአንድ ግድብ 70 ደሴት(አይላንድ) አለን ማለት ቀላል ሃብት አይደለም:: ግራና ቀኝ ያለውን መልክዓ ምድር ብታዩት እጅግ አስደማሚ የሆነ ተራራማ፣ ከተራራም በላይ በጣም ግሪን ቦታ ይታያል:: ሁላችሁም እንደምታውቁት፣ በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ተራራዎች ከግማሽ በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ ይባላል:: ይሄንን መጠቀም ብንችል ኖሮ ምን ያክል ተለውጠን በጽዱ ልብስ፣ በጽዱ ቁመና፣ በጽዱ ሁኔታ ደሃ ከመባል የተላቀቅን መሆን እንደምንችል መገንዘብ ይቻላል::

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ 85 በመቶውን የዓባይ ውሃ ስናበረክት ቆይተን ላለፉት ዘመናት አለመጠቀማችን የሚያስቆጭ ቢሆንም፤ አሁን መልካም ጅምር በመታየቱ የሚገባንን ተጠቅመን፣ የሚገባቸውን ለወንድሞቻችን ሰጥተን በጋራ ለማደግ በእኛ በኩል ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ እየገለጽኩ፤ ዓባይ የኢትዮጵያ ኩራት፣ ዓባይ የኢትዮጵያ የብልጽግና ጅማሮ መነሻ፣ ዓባይ ኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ ከፍታ የሚለመልምበት ቦታ መሆኑን ተገንዝበን፤ እስላም ክርስቲያን፣ ጉራጌ ስልጤ፣ ኦሮሞ አማራ፣ ሶማሌ አፋር፣... ሳንል ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጋራ በመደመር አንድ ላይ በመቆም ብልጽግናችንን እውን እንድናደርግ እና ከእርዳታ ከልመና ራሳችንን እንድንገላግል በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ::

መላው የአፍሪካ ወንድሞቻችን እንኳን ደስ ያላችሁ፤ ዓባይ እንደተለመደው በድል የሚገባውን አስቀርቶ የሚገባቸውን እየሰጠ መጓዝ ጀምሯል:: መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በዚህ የተሳተፋችሁ፣ ገንዘብ ያዋጣችሁ፣ በሙያ የደገፋችሁ፣ በዲፕሎማሲው መስክ የጮኻችሁ ሁሉ ልፋታችሁ ፍሬ ስላፈራ እንኳን ደስ ያላችሁ ልል እፈልጋለሁ:: ከሁሉ በላይ የጀመርነው የእጅ ስራ እንዲከናወን የረዳን፤ የተናገርነው እንዲፈጸም ያገዘን፤ በድካም በፈተና ሁሉ በጥንካሬና በስኬት እንድንወጣ ያደረገን መልካሙ አምላክ፣ የኢትዮጵያ ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን::

አሁንም ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ፤ ብልጽግናችንን እውን ያድርግ፤ የእጃችንን ስራ ይባርክ፤ የተጀመረው ድል ይቀጥላል፤ የተጀመረው የብልጽግና ጉዞ ይቀጥላል፤ እያንዳንዱ ፈተና ግን የሚያጠነክረን ይሆናልና የምንሸማቀቅበት ሳይሆን የምንማርበት እንዲሆን አደራ እያልኩ፤ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ፤ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ::

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

## በክህደት የተቋጨው ትዳር

አስመረት ብስራት

ጋብቻ ማለት በስነ ልቦና፣ በስነ አእምሮ እና አካላዊ ጥምረት ቤተሰብ ለማስተዳደር ወይም ለመምራት አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ባልና ሚስት ሆነው ወደውና ፈቅደው በፍቅር የሚጣመሩበት ትልቅ የቤተሰብ መመስረቻ ነው። በሂደቱም ያዳበሯቸውን ማህበራዊ ዕሴቶች በህግ አግባብ የሚተገብሩበት ነው።

አንዳንድ ፀሀፍት ጋብቻ "አንድ ወንድና አንድ ሴት ባልና ሚስት ሆነው ለመኖርና የህግ፣ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመውሰድ ተስማምተው የሚመሰርቱት ግንኙነት ነው።" የሚል ጠባብ ትርጉም ሲሰጡት በሌላ በኩል "ጋብቻ በተለያየ የስርዓት አይነት፣ ቤተሰባዊ ትስስር ለመፍጠር፣ የሚመሰረት በህግ እውቅና የተሰጠውና የጋራ ጥቅም፣ ኃላፊነትና ግዴታ የሚያስከትል እንዲሁም የዝምድና ትስስር የሚመሰረት ግንኙነት ነው።" ሲሉ የሚገልፁትም አልታጡም።

በአጠቃላይ ግን ‹‹ ጋብቻ ›› በአንድ ወንድ እና በአንዲት ሴት ቤተሰብ የመመስረት ወይም የመፍጠር ነጻ ፍላጎት ባልና ሚስት የመሆን ፍቃደኝነት ላይ የሚመሰረትና በሁለቱ መካከል የሚገኙ ሰዎችን በዝምድና የሚያስተሳስር በባልና ሚስቱ እንዲሁም በማህበረሰቡ መካከል ትስስር የሚፈጥር ህጋዊ፣ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ኃላፊነት እና ግዴታን የሚያስከትል ግንኙነት ነው የሚል ጠቅላላ ግንዛቤን (ትርጓሜ) ይሰጠዋል።

የተለያዩ ፀሃፍት የተለያየ ትርጓሜ የሰጡት ትዳር ባልተፃፈ ህግ ማህበረሰቡ በልቡ በከተባቸው በተለያዩ ስርአቶች ይመራል። መከባበሩ፣ መዋደዱ፣ መተማመኑ ትዳርን ከሚያጠብቁት ገመዶች አንዱ ነው። አብሮ በመኖር መንገድ ውስጥ ፍሬ ማፍራቱ አብሮ ማርጀቱ የእድሜ ልክ ትስስሩ ለጋብቻ የተለየ ትርጉም እንዲኖረን ቢያደርግም ሁሉም ትዳር ግን እንቅፋት ሳይመታው ቀጥ ብሎ የተጓዘ ነው ለማለት አያስደፍርም። እንኳን ሰው እግር እና እግር እንኳን ይጋጫልና በትዳር መካከል ግጭቶች ፣አለመግባባቶችና ጭቅጭቆች ያጋጥማሉ። ይህም ግጭት በቀላሉ በእርቅ በይቅርታ የሚደመደም ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ ደግሞ ግጭቱ የከረረ ይሆንና ጉዳዩ የፍትህ አካላት ደጅ ይደርሳል። አንቺ ትብሽ አንተ ትብስ ተባብሎ የተመሰረተው የተከበረው ትዳርም እንዲሁ ይበተናል።


በትዳር መካከል የሚያስቀና ትዳር ልክ እንደነእከሌና እከሊት የሚያስብል ደግሞ ያጋጥማል።ሚስት ቀኑን ሙሉ ደፋ ቀና እያለች አጣፍጣ ሰርታ ያቀረበቸውን ምግብ ባል ካንቺ በፊት አልጎርስም ሲል በመጀመሪያ ጉርሻው ፍቅሩን ሲገለጥላት፤ አረፍ በይ በሚል ቃል መተሳሰባቸውን የሚያሳዩበት፤ ከሁሉ በላይ ለብሳ ደምቃ እንድትታይ አዲስ አዲሱን መግዛት ማልበሱ ፍቅርን የሚያደረጁ የመተሳሰብ ምልክቶች ናቸው። ስለ ልጆቻቸው የጋራ ጉዳይ በጋራ መወሰናቸው ብቻ ሳይፃፍ መመሪያ ሳይወጣ በፍቅር መስመር ውስጥ የሚሰመር የህይወት ረጅም መንገድ ነው ። ይህ መስመር ደግሞ ከትናንሽ ግጭቶች አንስቶ እስከ ትላልቆቹ ጸብና ግጭት በመካከሉ በመፈጠሩ ትዳሩ ሰምሮ እንዳይሄድ መሰናከል ይሆናል። ለምን ግን በትዳር መካከል አባጣ ጎርባጣ ይበዛዋል፤ተዋደውና ተፋቅረው የተጋቡ ባልና ሚስት ለምን አይንሽን ላፈር ይባባላሉ?

### የትዳር መንገድ

የዛሬዎቹ ባለታሪኮቻችን ገና በጠዋቱ የአፍላነት እድሜ ላይ ተጣምረው ለአመታት በትዳር ህይወት ቆይተዋል። በልጅነት እድሜያቸው ልጅህን ለልጄ በሚለው የአካባቢው ባህል መሰረት ተጣምረው መኖር ከጀመሩ ከራርመዋል። ለወትሮው እርስ በእርስ በፍቅር ከመተያየት ያለፈ ፀብ በቅጡም ታይቶባቸው አያውቅም ነበር፤ ከተራ የእለት ግጭት አልፎ አሳልፎ እስከመሰጣጠት የደረሰ ጥልም አልነበራቸውም ይላሉ የሚያውቋቸው።

በዚህ ልክ በባለቤቷ ላይ ያላትን እምነት አሳጥቶ ለበላንጣዎቹ አሳልፎ እስከመስጠት ያደረሳት ጉዳይ በውል አልታወቀም፤ እምነቷን የሸረሸረው ምንም ይሁን ምን ባለቤቷን አሳልፎ እስከመስጠት የደረሰ ጥላቻ ውስጥ ገብተዋል።

‹‹ከአንተ በፊት ያድረገኝ ፤ ካንቺ በፊት ያደርገኝ›› ሲባባሉ የኖሩት ባልና ሚስት ለወዳጅ ጎረቤት የሚያስቀናው ፍቅራቸው ወደ ጥላቻ ተቀይሮ



በጥርጣሬ መተያየት ከተጀመረ እሷማ እኔን ለማጥፋት ታስባለች፤ እሱማ ቢገለኝ ደስታው ነው መባባልም ጀምረው እንደነበር አንዳንድ ወዳጆቻቸው ይናገራሉ። እንዲህ አንዲህ እያለ በቂምና ጥላቻ የተቋረጠው የፍቅር መንገድ ነው የትዳር አጋሯን ለጠላቶቹ አሳልፋ እንድትሰጥ ያደረጋት።

በቀላሉ በመነጋገር ሊፈቱ የሚችሉ ግጭቶች ተጠራቅመው በሆድ ውስጥ ውለው ሲያድሩ ቁርሾ ይሆናሉ። ያ ቁርሾ ደግሞ በበቀል ሊገለጥ ሲያስብ ‹‹ሰይጣን ምን ሰርቶ ይብላ›› እንዲሉ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮ የራስን ግማሽ አካል አሳልፎ እስከመስጠት የሚያደርስ ቂም ያሳድራል።

### የሞት ድግስ

ቂም የወለደው የሞት ድግስ ታህሳስ ሀያ ሁለት 2013 ዓ.ም ነው የሆነው። ወይዘሮ ሀና አዘዘና ባለቤቷ አደራው ከቤ በአንድ ቤት በፍቅር በመከባበር ይኖሩ ነበር። ሀና የሀያ ሁለት አመት ወጣት ናት። ጥንዶቹ በታዳጊ የእድሜ ክልል ላይ ሆነው ነው ትዳር የመሰረቱት። ነዋሪነታቸው በአማራ ክልል በጎጃም ክፍለ ሀገር አነደድ የተባለ ወረዳ ሻፎ በተባለ ቀበሌ ውስጥ ነበር። ጥንዶቹ ድርጊቱ በተፈፀመ እለት ማለትም ታህሳስ ሀያ ሁለት 2013 ዓ.ም ጁቤ ከተማ ሰፈር ሁለት በሚባለው አካባቢ አደራው ከቤና ሀና አዘዘ እንደ ሁልጊዜያቸው እራታቸውን በልተው ቤት ያፈራውን መጠጥ እየተጎነጩ ነበር። አደራው በደስታ የምታስተናግደው ሚስቱን እየተመለከተ እያሳለፉት ስላለው የፍቅር ምሽት ያስባል፤ እሷ ደግሞ የቧላን መስከርና በልቧ ያሰበችውን እኩይ ተግባር ለመፈፀም በጉጉት ትጠባበቃለች።

በእለቱ ከባል ማለትም ከአደራው ጋር ፀብ የነበራቸው ሁለት ግለሰቦች ጋር የሸረበቻት ሴራ ነበረች። እነዚህ ላቄ ጫኔና ቢያድግ ሉሌ የተባሉ ሁለት ግለሰቦች በአርባዎቹ እድሜ ክልል ላይ የሚገኙት ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ጠላታችን ነው ወዳሉት ወደ አደራው ቤት በመምጣት ሚስቱን ያግቧቧት ጀመር።

ባልሽን መጠጥ አጠጥተሽ አስክሪልን ሲሉ ካግባቧት በኋላ ከአካባቢው ዞር ይላሉ። ወትሮም ሆዷ ጎሾ የነበረችው ሀና ባሏን አሳልፋ ለመስጠት አላንገራገረችም። እሷም የተባለችውን ለማድረግ ከወትሮው በተለየ ፍቅር ተንከባክባ ባለቤቷን ራቱን አብልታ ቤት ባፈራው መጠጥ በአናት በአናቱ እየደጋገመ እንዲጠጣ በመገፋፋት ታሰክረዋለች። በአናት በአናቱ የተቀዳለትን አረቄ መቋቋም ያቃተው ባል በስካር አቅሉን ሲስት ቀስ ብሎ አልጋው ላይ ጋደም ይላል። ያን ጊዜ ደመኞቹን ወደ ቤት ታስገባለች።

በሚገርም ሁኔታ ወይዘሮዋ ባሏ ከእነዚህ ሁለት ሰዎች ጋር በምን እንደተጋጨ ሳትጠይቅ ነበር ባሏን አስክራ ለበላንጣዎቹ አሳልፋ የሰጠችው። ፖሊስ ባጠናቀረው መረጃ ላይ ይች ሴት ባሏን እንዲህ በማድረጓ ምን እንደምትጠቀም አልተገለፀም።

### የባላንጣዎቹ ክፉ እጅ

ከባላንጣቸው ቤት አቅራቢያ ተደብቀው እስኪጠሩ የሚጠባበቁት በቀል ያረገዙት ጓደኛሞች በስካር ደንዝዞ እንቅልፍ የወሰደው ግለሰብን ቤቱ ድረስ በመግባት በብረት አንገቱንና የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን በአሰቃቂ ሁኔታ ቀጥቅጠው ህይወቱ እንዲያልፍ አድርገውታል። ይህንንም ያደረጉት ቀን ገበያ ደርሰው ሲመለሱ ጎራ ካሉበት መጠጥ ቤት አንድ ሁለት ሲባባሉ በተወራወሩት ቃል የተነሳ በያዙት ቂም ነበር። በይቅርታ መተላለፍ ወይም ወደ ህግ መሄድ ሲገባ ባልተገባ ሁኔታ በበቀል በመነሳሳት ክቡሩ የሰው ልጅ ህይወት እንዲጠፋ ሆነ። ቀጥቅጠው መግደላቸው ሳያንስ አስከሬኑን በኬሻ ጠቅልለው በአካባቢያቸው በሚገኘው ማሩ በተባለ ወንዝ ጥለውት ከአካባቢው ይሰወራሉ።

### የፖሊስ ምርመራ

ይህ ድርጊት ከተከሰተበት ከታህሳስ ሀያ ሁለት እስከ ጥር አስራ ስድስት ድረስ ለአንድ ወር ጥቂት ቀን እስኪቀረው ድረስ የሟች መድረሻ ሳይታወቅ እምን ይግባ ሰማሁ አየሁ የሚል ጠፍቶ ቆየ። ሚስቲቱም ከባሏ መጥፋት በላይ የሰራችው ወንጀል ውስጥ ውስጧን እየበላት ጠፋ የተባለውን ባሏን በመፈለግና ባለመፈለግ መካከል ቆማ ትናውዝ ነበር። ከአንድ ወር በኋላ ግን ወደ ገበያ ሲሄዱ የነበሩ መንገደኞች አስከሬኑን አግኝተው ለፖሊስ ጥቆማቸውን ይሰጣሉ። የሟች አስክሬን ከተገኘ በኋላ ፖሊስ ምርመራውን ይጀምራል።

ፖሊስ ምርመራውን የጀመረው ከቤተሰብ ወይም ከሟች ጋር ቅርበት ካላቸው ሰዎች አካባቢ ነበር። የሟች የቅርብ ጓደኞችን ወዳጅ ዘመዱን ሟች ከማን ጋር ፀብ እንደነበረው ያጠያይቃሉ። ሟች አመለሸጋ መሬት እየገመሰ እልፍ ምርት የሚዝቅ ጠንካራ ገበሬ እንደነበረ እንብዛም ከሰው ጋር የማይጋጭ ሲነኩት የማይወድ አይነት ሰው እንደ ነበረ ብዙዎች ይመሰክራሉ።

ባለቤቱም ባሏ ከጠፋ በኋላ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ሆኖባት ብዙም የተረጋጋ መንፈስ ስላልታየባት የምርመራ አቅጣጫው ወደሷ መዞር ጀመረ። በምርመራውም የዚህ አሰቃቂ ወንጀል ተባባሪ ባለቤቱ ሀና አዘዘ መሆኗን ፖሊስ ይረዳል። ፖሊስ የምስክሮችን ቃል የታክቲክና የቴክኒክ ማስረጃዎችን በማጠናከር ተጠርጣሪዎቹን ለምስራቅ ጎጃም የወንጀል አቃቤ ህግ በማድረስ ጉዳዩን ወደ ፍርድ እንዲቀርብ ያደርጋል።

አቃቤ ህግም የምርመራውን ውጤት በመያዝ ክስ የመሰረተ ሲሆን፤ በፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪዎች ቀርበው የእምነት ክህደት ቃላቸውን በመስጠት ጉዳዩ ሲታይ ቆይቶ ውሳኔ አስተላልፏል።

### ውሳኔ

አቃቤ ህግ ከአይን እማኞችና ከተለያዩ ምርመራዎች የተገኙ ማስረጃዎችና መረጃዎች ተጠናክሮ የቀረበለትን ማስረጃ በመያዝ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል። ፍርድ ቤቱ መረጃዎችን ሲመረምር ቆይቶ በተከሳሾቹ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለማሳለፍ በቀነ ቀጠሮ ተገኝቷል። ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል ተከሳሾች በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ መሆናቸውን አረጋግጦ የክስ መከላከያቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል ሰጥቷል። ተከሳሾቹም ወንጀሉን ፈጽመው አላስተባበሉም።

ሰኔ አስራ ሰባት ቀን 2013 ዓ.ም የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋለው ችሎት ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት አንደኛ ተከሳሽ ሃና አዘዘ እጇ ከተያዘበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር በአስራ ስድስት አመት ፅኑ እስራት እንድትቀጣ ውሳኔ ተላልፎባታል። ሁለተኛ ተከሳሽ ሟችን በብረት በመደብደብ ህይወቱ እንዲያልፍ ያደረገው ላቄ ጫኔ በአስራ ሰባት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል። እንዲሁም ሶስተኛ ተከሳሽ ቢያድግ ሉሌ በአስራ ስድስት አመት ፅኑ እስራት እጃቸው ከተያዘ ጀምሮ በሚቆጠር ‹‹ይቀጡልኝ›› ሲል ውሳኔውን በማሳለፍ መዝገቡን ዘግቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የግል ትምህርት ቤቶችና "የግል ሥርዓተ ትምህርቶች"

ደበል ካሳ

ታላቁ የነጻነት ታጋይና የፖለቲካ መሪ የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላ ለትምህርት የተለየ ፍቅር እንደነበራቸው ይነገራል። ብዙ ጊዜ ስለእርሳቸው ሲነሳ "ዓለምን መለወጥ የሚያስችል ብቸኛው መሳሪያ ትምህርት ነው" የሚለው አባባላቸው ሳይጠቀስ የማይታለፈውም ለዚሁ ነው። በእርግጥም ትምህርት ራስን፣ አካባቢን፣ አገርንና ወገንን ከፍ ሲልም ዓለምን የመለወጥ ኃይል አለው። ይህንን የሚያደርገው ደግሞ የሰውን ልጅ የአስተሳሰብ አድማሱን በማስፋት፣ ዓለምን የሚመለከትበት ዕይታውን ወይንም አመለካከቱን በማስተካከልና ነገሮችን የመከወን ክህሎቱን በማሳደግ ነው።

ትምህርት የሰው ልጅ አዕምሮ ችግር ፈች በሆነ አስተሳሰብ እንዲሞላ ስለሚያደርገው አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር ብቃትን ያላብሰዋል። ዓለም በየጊዜው ያለፈችበት የለውጥ ሂደትና አሁን ላይ የደረሰችበት አጠቃላይ የስልጣኔና የዕድገት ደረጃም የሰው ልጅ በትምህርት አማካኝነት በየጊዜው የሚገጥሙትን ችግሮች እየፈታና አዳዲስ ነገሮችን እየፈጠረ በአሸናፊነት ወደፊት መጓዝ የመቻሉ ውጤት ነው።

ለዚህ ደግሞ ትምህርት የሚጠበቅበትን ዓላማ ማሳካት እንዲችልና በትክክል የለውጥ መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የዜጎችን አካላዊና አዕምሯዊ የእድገት ደረጃ ያማከለና ሁሉንም እንደየፍላጎቱና አቅሙ ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችል ተገቢ ሥርዓተ ትምህርት ሊመራ ይገባዋል። ይሁን እንጂ በሃገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በመዲናችን አዲስ አበባ ከመደበኛው የአገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት ውጭ የሆነ የራሳቸውን ማስተማሪያ መጽሃፍ አዘጋጅተው የሚያስተምሩ አንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች መኖራቸውን በተለያየ አጋጣሚ ሕብረተሰቡ በስፋት ሲያነሳው የሚሰማ ጉዳይ ነው።

ወቅቱ ልጆቻችን ለአዲሱ ዓመት ትምህርት ለማዘጋጀት እየተሰናዳን የምንገኝበት ነውና ከሰሞኑ በአንድ አጋጣሚ በዚሁ ጉዳይ ላይ የታዘብኩትና እንደአንድ ኃላፊነት የሚሰማው ኢትዮጵያዊ በጉዳዩ ላይ አሳሳቢ ሆኖ ያገኘሁትን ችግርና ጉዳዩ የሚመለከተው አካል መፍትሔ ይፈልግለት ዘንድ ሃሳቤን ላካፍላችሁ ወደድኩ።

ከሰሞኑ ወደአንድ ጓደኛዬ ቤት ጎራ ብዬ ነበር። አዲስ አበባ ውስጥ በአንድ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ አስተማሪ ነው። ታዲያ ቤት ውስጥ ተቀምጠን ስለሥራ፣ ኑሮ... የተለያዩ ጉዳዮችን እያነሳን እየተጨዋወትን እያለ በመሃል "አንተ እኮ እንግሊዝኛ ነው ያጠናኸው፤ እስኪ እነዚህን መጽሐፎች እያቸው" አለና ከኋላው ካለው ጠረጴዛ ላይ አራት የሚሆኑ የ"ኤ4" መጠን ያላቸው ትልልቅ ሞጁል መሳይ መጽሃፍቶችን አንስቶ ሰጠኝ። እርሱ በሌላ የትምህርት መስክ ተመርቆ ነው በትምህርት ቤቱ ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተማሪ የሆነው። ይህንንም ያዙልኝና ወደዋናው ጉዳዩ ልለፍ።

ከዚያም በጥያቄው መሠረት መጽሐፍቱን ተቀብዬ በጉጉት ማገላበጥ ጀመርኩ። ሁሉም የአራተኛ ክፍል ማስተማሪያዎች ናቸው። በእያንዳንዱ ሞጁል ላይ የተጻፈው የትምህርት ዓይነት ስም እንደ ወረደ አንደኛው "ኢንግሊሽ"፣ ሁለተኛው "ስፖክን"፣ ሦስተኛው "ሪዲንግ ስኪል" አራተኛው ደግሞ "ጀኔራል ሳይንስ" ይላል። እርሱ እንዳለው የተመረኩበት የትምህርት ዘርፍ እንግሊዝኛ ቋንቋ በመሆኑ ትኩረቴን እንግሊዝኛ ሞጁሎቹ ላይ አድርጌ ምልከታዬን ቀጠልኩ። "ኢንግሊሽ" የሚለውን ሞጁል አንስቼ የመጀመሪያውን ገፅ ገልበጥ አድርጌ ማውጫውን ስመለከት በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ "ፕሩፍ ሪዲንግ" የሚል ርዕስ ሳይ ክው ብዬ ደነገጥኩ።

ራሴን ማመን ስላቃተኝ በፍጥነት ሞጁሉን ዘጋሁትና እንደገና ጀርባውን አፍጥጬ ሳይ መጽሃፉ እውነትም ለአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው። ቀና ብዬ ጓደኛዬን በግርምት ተመለከትኩትና "እውነት ይሄን ለአራተኛ ክፍሎች ነው የምታስተምሯቸው?" በማለት ስጠይቀው "እኔን ግራ የገባኝና አንተ እንድታየው የፈለኩትም እኮ ለዚህ ነው" አለኝ። የአራተኛ ክፍል ጨቅላ ህጻናትን "ፕሩፍ ሪዲንግ" የሚያስተምር ትምህርት ቤት እንደ እውነታው "የዕውቀት ቤት" ሳይሆን "የውድቀት ቤት" በመሆኑ እዚያ አስተማሪ መሆን የሚጎዳው ትውልድን ብቻ ሳይሆን የአስተማሪውንም ህሊና ጭምር ነውና በእርግጥም ነገሩ ግራ ከማጋባት አልፎ የሚያሳዝንም ሆኖ ነው ያገኘሁት።

"ፕሩፍ ሪዲንግ" ማለት እኮ የንባብ የመጨረሻው ደረጃ ሲሆን ከፍተኛ የአዕምሮ ብስለትንና የማሰብ ችሎታን የሚጠይቅ ለአዋቂዎች ሳይቀር የሚከብድ ክህሎት ነው። ለአዋቂዎችም የሚከብድ ነው የሚባልበት ምክንያትም ትምህርቱ በእጅጉ አስተዋይነትንና ጥንቃቄ የሚፈልግ በመሆኑ ነው። ለአብነትም "kill him not, leave him" በሚለው ለቅጣት አስፈጻሚ ፖሊስ የተጻፈ የእንግሊዝኛ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ኮማ የምትባለውን ሥርዓተ ነጥብ "not" ከሚለው ቃል በፊት ተሳስቶ ቢያስቀምጣት እንደማንኛውም ስህተት በይቅርታ ወይም በእርማት የሚታለፍ አይደለም፣ በመሳሳታችን ምክንያት ክቡር የሆነውን የሰው ህይወት አጥፍተናልና! እንግዲህ እንዲህ ዓይነት ስህተቶችን የማስቀረት ክህሎት ነው "ፕሩፍ ሪዲንግ" የሚባለው።

ታዲያ ማንበብ በደንብ የማይችል አንድ የአራተኛ ክፍል ህጻን ማንበብ እንኳን ሳይችል በምን ተዓምር ነው ከማንኛውም ዓይነት ስህተት በፀዳ መንገድ ማንበብን እንዲማር የሚደረገው? እኔው ራሴ ተምሬ የተመረኩት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሲሆን እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ "ፕሩፍ ሪዲንግ" የሚባል ነገር አላውቅም። ፕሩፍ ሪዲንግን የተማርኩት ዩኒቨርሲቲ ከገባሁ በኋላ ያውም መጨረሻ ዓመት ላይ ነው። እዚህ ግን ማንበብና መጻፍ እንኳን በደንብ ያለመዱ የአራተኛ ክፍል ህጻናት ያለ አቅማችሁ ተማሩ ተብለው ሲጨነቁ ይውላሉ።

ይህን በማሳያነት አነሳን እንጂ ሌላም ብዙ ብዙ ነገር አለ። ከላይ እንደቀረበው አንዱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የትምህርት ዓይነት "ኢንግሊሽ"፣ "ስፖክን" "ሪዲንግ ስኪል" አንዳንዶቹ የግል ትምህርት ቤቶች አካባቢ ደግሞ "ራይቲንግ" ተብሎ አንዱን አራት ጊዜ ያስተምሯቸዋል። ተመልከቱ እንግዲህ ስፖክን፣ ሪዲንግና ራይቲንግ በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ ክህሎቶች ሆነው እያለ የተለያየ የትምህርት ዓይነት ሆነው ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾላቸው መጽሐፍ ተዘጋጅቶላቸው ተማሪዎች እንዲማሩ ሲደረግ። እናማ እንግዲህ በእንግሊዝኛ ጻፍ ስትለው "በራይቲንግ ነው እንጂ በእንግሊዝኛ መጻፍ ይቻላል እንዴ? የሚል ትውልድን ቀርጸው እስከሚያስረክቡን በትዕግስት መጠበቅ ነው እንጂ ምን እንላለን።

ሌላም አለ። "ጀኔራል ሳይንስ" የትምህርት ዓይነታቸው ደግሞ እነዚህን የአራተኛ ክፍል ህጻናት ልጆቻችንን ማወቅ ስለሚገባቸው ስለ አምስቱ የስሜት ህዋሳትና ስለ ዋና ዋና የአካል ክፍሎቻችን አገልግሎት ትተው ለሕጻናቱ ቀርቶ ስፔሻሊስት ሃኪሞች እንኳን በስንት ድካም የሚረዱትን ውስብስቡን የሥርዓተ ነርቭ ሳይንስ ያስተምሯቸዋል ማለቴ ያሰፍሩባቸዋል። ሥለ ሥርዓተ ነርቭ የተማርኩት አስረኛ ክፍል ላይ መሆኑን በሚገባ አስታውሳለሁ፣ ከሥነ ህይወት ትምህርት ብዙዎቻችን የሚከብደንም ይኼ እንደነበርም ትዝ ይለኛል።

እናም የተማሪዎችን ዕድሜ፣ የአዕምሮ ዕድገት ደረጃና አቅም ያላገናዘበ በአንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው የትምህርት ሥርዓት ችግር የሚፈታ ሳይሆን ትውልድን ለችግር የሚያጋልጥ አካሄድ ነው። ከዚህም ባሻገር በአንድ ሃገር ውስጥ የግል ትምህርት ቤት እንጂ የግል ሥርዓተ ትምህርት ሊኖር ስለማይችል ሁኔታው መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባል።

# ዓለም አቀፍ



## አሜሪካ ከሰሃራ በታች ላሉ የአፍሪካ ሃገሮች የነደፈችው አዲሱ ስትራቴጂ

አሜሪካ ከሰሃራ በታች ላሉ የአፍሪካ ሃገሮች የነደፈችው አዲስ ስትራቴጂ ከኢትዮጵያ ሁኔታ አኳያ ከፍተኛ አንደምታ እንዳለው በአትላንቲክ ካውንስል ከፍተኛ ተመራማሪ ገለጹ።

ከፍተኛ ተመራማሪው አቶ ገብርኤል ንጋቱ፣ለዶይቸ ቨለ እንደገለጹት፤ አዲሱ የአሜሪካ ስትራቴጂ በአፍሪካውያን ፍላጎትና ፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆኑ፣በራሷ መንገድና አስተሳሰብ ለምትሄደው ኢትዮጵያ ትልቅ ትርጉም አለው ተብሏል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን፣በአፍሪካ ሃገሮች በቀጠለው ጉብኝታቸው ያስተዋወቁት የዩናይትድ ስቴትስ ከሰሃራ በታች ለሚገኙ ሃገሮች ያዘጋጀችው አዲስ ስትራቴጂ፣ቅድሚያ የሚሰጣቸው ብሎ በአራት የከፈላቸው የጋራ ጉዳዮች ግልጽነት፣ዴሞክራሲ፣ኮቪድ 19 እና የአየር ንብረት ለውጥ ናቸው።

ስትራቴጂውን ይፋ ባደረጉበት ንግግራቸው፣ዩናይትድ ስቴትስ የአፍሪካን ምርጫዎች አትወስንም ያሉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣እነዚህን ምርጫዎች የማድረግ መብት ሌላ የማንም ሳይሆን የአፍሪካውያንና የአፍሪካውያን ብቻ ነው ብለዋል።

ይኸው አዲሱ ስትራቴጂ፣በአፍሪካውያን ፍላጎትና ፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ለኢትዮጵያ ትርጉም እንዳለው በአሜሪካ የጥናትና ምርምር ማዕከል የሆነው የአትላንቲክ ካውንስል ከፍተኛ ባልደረባ አቶ ገብርኤል ንጋቱ ገልጸዋል። "ኢትዮጵያ በራሷ መንገድና በራሷ አስተሳሰብ የምትሄድ ሃገር ነች። እና ከምሥራቁም ከምዕራቡም ሳይሆን ከሁለቱም የሚጠቅማትን የምትወስድ ሃገር ናት፤ ለኢትዮጵያ ትልቅ አንደምታ መኖሩን ተናግረዋል።

ብሊንከን፣ዴሞክራሲና ዲፕሎማሲ ላይ ባተኮረው ገለጻቸው፣ሁከትን ለማስቆምና የሠላም ጎዳና ለመክፈት አሜሪካ ከአፍሪካ መሪዎች፣ቀጣናዊ ድርጅቶችና ዜጎች ጋር መስራቷን ትቀጥላለች። የአሜሪካው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣አፍሪካ ለምን ተፈላጊ አህጉር እንደሆነች ባመላከተው የስትራቴጂ ሰነዱ ክፍል፣በ2050 በዓለም ላይ ከአራቱ ሰዎች አንዱ፣አፍሪካዊ እንደሚሆን ጠቁመዋል። እነዚህም የዓለምን ዕጣ ፈንታም ይቀርጻሉ ማለታቸውን ፣ለዶይቼ ቨለ ዘግቧል።

## የዶናልድ ትራምፕ መኖሪያ ቤት በኤፍቢአይ የተበረበረበት ምክንያት ይፋ ሊደረግ ነው



የኤፍቢአይ ወኪሎች የቀድሞውን የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕን ቤት የበረበሩበት የፍተሻ ማዘዣ ይፋ እንዲደረግ የአገሪቱ ፍትህ ቢሮ የፍሎሪዳውን ፍርድ ቤት ጠየቀ።ያልተለመደ ነው የተባለለት ጥያቄ ፈቃድ ካገኘ የትራምፕ መኖሪያ ቤት እንዲፈተሽ የተደረገበት ምክንያት ለሕዝብ ይፋ ይሆናሉ ተብሏል።

ዶናልድ ትራምፕ በተመሳሳይ የብርበራ ፍቃዱ ሰነድ ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን ፍላጎታቸው እንደሆነ ገልጸዋል። የፍትህ ቢሮ ፍተሻው ለምን እንደተካሄደ እስካሁን ይፋ አላደረገም። የአሁኑ ጥያቄ ግን ለዚህ ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል። ሰኞ ዕለት በኤፍቢአይ ወኪሎች የተደረገው ብርበራ የቀድሞው ፕሬዝዳንት ጥብቅ እና ሚስጢራዊ ሰነዶች አያያዝ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ስማቸው ያልተገለጸ አንድ ምንጭን ጠቅሶ ዋሽንግተን ፖስት እንዳስነበበው የኤፍቢአይ ወኪሎች ከኒውክለር መሣሪያዎች ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ጭምር በትራምፕ መኖሪያ ቤት ሲፈልጉ ነበር።

ወኪሎቹ የቀድሞዋ ቀዳማዊት እመቤት ሜላኒያ ትራምፕን ቁም ሳጥን እና የግል ቁሳቁሶቻቸውን መበርበራቸውን ትራምፕ ገልጸዋል። ቀደም ሲል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ሜሪክ ጋርላንድ በትራምፕ መኖሪያ ቤት ላይ ፍተሻው እንዲካሄድ መፍቀዳቸውን ገልጸዋል።

ከፍርድ ቤት ፍተሻ ማዘዣ ጋር የተገናኙ ሰነዶች ለሕዝብ ጥቅም ሲባሉ ይፋ እንዲሆኑ እየጠየቁ መሆኑን ጋርላንድ ተናግረዋል። የፍትህ ቢሮ ሁሌም መደበኛ ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ እንደሚያደርገው ዝምታ የመምረጥ ልምዱን እየተከተለ ነው። የፍትህ ቢሮ ጠበቆች ሐሙስ ዕለት በፌዴራል ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ "በዚህ ሁኔታ የተከሰተውን ነገር ለመረዳት የሕዝቡ ግልጽ እና ከፍተኛ ፍላጎት ስላለው ይፋ መሆኑ ይጠቅማል" ብለዋል።

የቀድሞ ፕሬዝዳንት መኖሪያ ቤት ከወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ ሲፈተሽ የሰኞው በአሜሪካ ታሪክ የመጀመሪያው ነው። ትራምፕ እና ሌሎች ሪፐብሊካኖች እርምጃውን ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ሲሉ አውግዘዋል። ሐሙስ ዕለት በጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት ጋርላንድ የኤፍቢአይ ወኪሎችን እና የፍትህ ክፍል ኃላፊዎችን ተከላክለዋል።

ጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ "ታማኝነታቸው ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ሲጠቃ በዝምታ አላይም" ብለዋል። የፍተሻ ማዘዣውን ለማስፈጸም መወሰኑም ቀላል እንዳልነበር ተናግረዋል። የትራምፕ ጠበቃ የሆኑት ሊንሴይ ሃሊጋን ፍርድ ቤት ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት የህግ ቡድናቸው ማዘዣውን በመልቀቅ ጉዳይ ላይ እየተወያየ ነው።

የብርበራውን ፎቶ እና ቪዲዮ ይፋ ለማድረግም እያሰቡ ነው። የኤፍቢአይ ወኪሎች የማር-አ-ላጎ የሲሲቲቪ ካሜራዎች እንዲጠፉ ጠይቀው ነበር። የትራምፕ ሠራተኞች ግን ይህንን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም መባሉን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# የእይታ ልክ!

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

ቦታው የአይን ህክምና አገልግሎት መስጫ ቦታ ነው። አገልግሎት ፈልገው የተሰበሰቡት ሰዎች ወረፋቸውን እየጠበቁ ነው። በወረፋቸው መሰረት ወደ ህክምና ክፍል የገቡ እናት ከሀኪሙ ጋር ናቸው። ሀኪሙ እንደተለመደው "ይህቺ ፊደል አቅጣጫዋ ወዴት ነው?" እያለ ይጠይቃል፤ እርሳቸውም ይመልሳሉ። አሁንም ሌላ አቅጣጫ ጥያቄ፤ እርሳቸውም ሌላ ምላሽ። ከትልቁም፤ ከመካከለኛውም፤ ከትንሹም ፊደል እያደረገ አቅጣጫውን እየፈተነ ዘለቀ። እማማ "ህክምና ነው የመጣሁት ወይንስ ምን?" እያሉ በውስጣቸው እያጉረመረሙ፤ ማሽን ላይ እንዲቀመጡ ታዘዙና ወደ ማሽን ሄዱ። በማሽን ወደሚደረግ ምርመራ።

ህክመናውን ጨርሰው ከቤታቸው ሲደርሱ ውሏቸውን ለቤተሰባቸው አባል ሲናገሩ የመጨረሻው ልጃቸው በጥሞና ታደምጣለች። እንደተለመደው ከቤተሰቡ ውሎ ተነስታ ጽሁፍ ልትጽፍ። ሁሉም የቤተሰብ አባል ስለ እይታ፤ ስለ አይን ምርመራ፤ ስለ ህክምና የየራሳቸውን ሃሳብ እየሰጡ አመሻሹ፤ ታዳጊዋም ስለምትጽፈው ጽሁፍ እያሰበች።

በነገታው ልጃቸው "የእይታ ልክ" ብላ የሰየመችውን አጭር ልብወለድ አዘጋጀች። ጽሁፉንም ለቤተሰቡ አባላት አነበበች። አባት በልጃቸው የስነጽሁፍ አቅም ተገረሙ። የእይታ ልክ ትልቅ ቦታ ለመድረስ አስባ ተነስታ በየጊዜው የሚገጥማትን ተግዳሮት አልፋ መዳረሻዋ ላይ ደርሳ ታሪኳን ለልጆቿ የምትተርክ እናት ታሪክ ነው።

ልጅቱ በሥነ-ጽሁፍ ነገሮችን የምታይበትን ፍልስፍናዊ መንገድ ታሳያለች። በማህበረሰብ ውስጥ እየሆነ ያለውን ነገር በጥበብ አድርገን ማቅረብ መቻል እንደ ማህበረሰብ ልንቀርጽ የሚገባውን እሴት ለመቅረጽ ይረዳል ብላም ታምናለች። እይታው ትልቅ የሆነ ማህበረሰብ በመደበኛ ትምህርትም፤ በኪነጥበብም እንዲሁም በሚዲያ ይዘቶች ይቀረጻል የሚልም እምነት ይዛለች።

አባትም እንደወትሮው ለልጃቸው "ልጄ እውነትሽን ነው የእይታ አቅም ብዙ ነገር ማለት ነው። በአይናችን አማካኝነት ብዙ መረጃዎችን ወደ ውስጣችን አስገብተን አብላልተን ለውሳኔ ሰጪነት እንደምንጠቀምበት እንዲሁ ህይወትን የምናይበት መንገድም ለአጠቃላይ ለህይወት ጉዞችን ወሳኝ ነው።" በማለት ተናገሩ። አባት ንግግራቸውን በመቀጠል "ልጄ የአድዋ ድልን በእይታ ውስጥ ስታይው ብዙ ያስተምረናል። አድዋ ተራሮች አናት ላይ ስለ እይታ የተጻፈ ታላቅ ገድል አለ። ይህን ታላቅ ክስተት ከተለያየ አቅጣጫ ተመልክተሽ በብእርሽ አድርገሽ የምታቀርቢው መልእክት የአድዋን መንፈስ በሰዎች ውስጥ ይፈጥራል። ጣሊያን በቂም ዳግም የወረረችን ታሪክንም እንዲሁ በተለያየ አቅጣጫ ልታይው ትችያለሽ። በመጀመሪያው የተሸነፈች በኋለኛው ያሸነፈች አድርገሽ ልታቀርቢው ትችያለሽ። ነገር ግን መሸነፍ ማለት እጅ ሰጥቶ መቀመጥ ከነበረ ደግሞ እንዳልተሸነፍን ይገባሻል። አየሽ ልጄ የእናትሽን አይን ጤንነት ለማወቅ የአይን ሀኪሙ ከተለያየ አቅጣጫ እንደመረመረ እንዲሁ ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ በመመልከት እይታን ማስተካከል ይቻላል። ሰዎች ስለ እኛ በተለያየ አቅጣጫ የሚሉትን ሰምተን ምናልባትም በተሳሳተ ሳጥን ውስጥ ራሳችንን እንዳንጨምር የእይታ ጥራት የግድ ነው።" እያሉ የተለመደውን ማበረታቻቸውን ቀጠሉ።

"ልጄ ብርጨቆውን ተመልከቺው፤ ግማሽ ብርጭቆ ውሃን ይዞ ይታያል። በብርጭቆ ውስጥ ያለውን ውሃ የምታይበት አተያይ ግን እንደ እይታሽ ልክ ነው። አንዳንዱ ግማሽ ብርጭቆ ውሃ ሲታየው ሌላው ግማሽ ባዶ ብርጭቆ ሊታየው ይችላል። ሁሉም እንደ እይታው የሚለው ይኖረዋል። እይታ የህይወት አቅጣጫን የመወሰን እድሉ ከፍተኛም የሆነው ለእዚህ ነው። ሰዎች የልቦናቸው አይኖች በርተው ምርቱን ከገለባው ለይተው ማየት ካልቻሉ ኪሳራ ውስጥ ዘመናቸውን ይጨርሳሉ። የመጣው ነገር ሁሉ የሚወስዳቸውም ይሆናሉ። የሚመጣው ነገር ሁሉ ራሱን አሳምሮ እንደሚመጣ መሆኑን ይረሳሉ።

አንቺን ለፍቅር ህይወት የሚፈልግ ሁሉ ሲመጣ ራሱን መልአክ አድርጎ፤ አንደበቱን አስተካክሎ ወዘተ ነው የሚመጣው። ነገርግን በጠራ እይታ ነገሮችን መርምረሽ ውሳኔ ማሳለፍ የአንቺ ኃላፊነት ነው። ዛሬ በተንሸዋረረ እይታ የህይወትን መስመር የሳቱ ብዙ ሰዎች አሉ። ህይወትን በገንዘብ ውስጥ ብቻ አይተው ስለ ገንዘብ በማይሆን መንገድ ውስጥ ገብተው ከዓላማ መስመር የወጡ። ህይወትን በዝና ውስጥ ፈልገው ዝናው እጃቸው ሲገባ ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ የሆኑም አሉ። ሁሉም እንደ እይታሽ ነው፤ እይታሽ የጠራ ካልሆነ ግን ህይወትሽ በጨለማ ውስጥ ይዳክራል። ህይወትን እንዲህ ግለጪያት። ፈጽሞውኑ ህይወትን በደፈረሰ እይታ ውስጥ የመምራትን አደገኛነት አስተምሪ።" አሉ።

በዚህ ጽሁፍ ስለ እይታ ልክ እናነሳለን። ትልቅ እይታን የያዙ ሰዎች የሄዱበት እርቀትን ተመልክተን በትንንሽ እይታ በቆሙበት ቦታ ላይ ስለቀሩትም በማስታወስ። ትልልቅ እይታ ከትልልቅ ስፍራዎች ሳይሆን ከራስ ልብ የሚነሳ መሆኑን ልብ በማለት።

### ኮሌጅ ያልተገኘው

ወደ ኮሊጅ የገባ ተማሪ እውቀትን ይዞ ሊወጣ የወሰነ መሆኑ ጥርጥር የለውም። እውቀትን ሸምቶ፤ እውቀትን የራሱ አድርጎ መፍትሔን ፍለጋ በሥራው አለም የሚሰማራ። ሊያሳኩ የፈለጉትን ነገር ኢላማ አድርገው፤ ትኩረታቸውን በልባቸው ይዘው ዳር ለማድረስ የተጉ አያሌ አንቱታን ያተረፉ ሰዎች በኮሌጅ በር ላይ አልፈዋል። እነህ በስራቸው አንቱታን ያተረፉ ሰዎች የሚያዩትን በተግባር ለማየት በብዙ የደከሙ መሆኑን የተራመዱት እያንዳንዱ ቀን ምስክር ነው። በኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አያሌ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው መመረቃቸው ጸድቆላቸው ይወጣሉ። ከተመራቂዎቹም መካከል ከፍተኛውን ነጥብ ያመጡት ኮሌጁ ያዘጋጀውን ሽልማት ተሸልመውም ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ለማመን የሚከብድ ውጤት ይዘው ሲወጡ ሚዲያዎች የገጾቻቸው ማድመቂያ አድርገዋቸውም እናነባለን። ለትምህርት ቦታ መስጠት ለነገ የሚባል አለመሆኑንም እንረዳለን፤ እንዲህ በመሰለ መንገድ ጎበዝ ተማሪዎች መሸለማቸውንም እንዲሁ እናነሳለን። ነገርግን የዓለማችንን ተጽእኖ ፈጣሪዎች ዝርዝር ውስጥ ኮኮብ ተማሪዎች ግንባር ቀደም ሆነው የመታየታቸው ነገር የጠበበ የሆነበትን እድልም ጎን ለጎን እንፈትሻለን።

በተለምዶ ውጤታማ ተማሪዎች መገለጫ አድርገን በምንመዝንበት መመዘኛቸው መሰረት በትክክል ተጽእኖ መፍጠር መቻል ወይንም ውጤታማ መሪ ሆኖ መመዘን አስቸጋሪ ሆኖ ይገኛል። ለምሳሌ በ500 ትልልቅ ድርጅቶች ላይ በተሰራ ጥናት ከ 50% በላይ የሚሆኑት የድርጅት ስራ-አስፈጻሚዎች የኮሌጅ ውጤታቸው በ C የሚገለጽ ሆኖ የተገኘ ነው። 75% የሚሆኑ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች የትምህርት ቤት ውጤታቸው በመካከለኛ ተማሪነት የሚገለጹ እንጂ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ (በተለምዶ ሰቃይ ተማሪዎች) ከሚባሉት መካከል አይደሉም። ከግማሽ የማያንሱ በጥናቱ የተካተቱ ሚሊዬነር ስራ ፈጣሪዎች ኮሌጅ የጨረሱ ሆነው አልተገኙም። እነህ ተራ የሚባሉ ሰዎች ሀገር ለመምራት እንዲሁም ሚሊዬነር እንዲሆን ያደረጋቸው የእይታ ልካቸው ነው፤ ትልቅ አይተው ትልቅ ቦታ ደርሶ፤ ትልቅ በማየታቸው በውስጣቸው የተፈጠረው መቀጣጠል ያዩትን እንዲጨብጡ አደረጋቸው። እይታ ጤናማ ሲሆን፤ እግር በአግባቡ ሲራመድ፤ እጅም ሊሰራ የሚገባውን ሲሰራ ግብ ካደረጉት ተራራ ላይ መድረስ ይቻላል።

### በምን አወቅናቸው?

በዓለማችን ውስጥ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አድርገው ያለፉ ሰዎችን በምን አወቅናቸው ብለን እንጠይቅ። እከሌን በእዚህ አወቅኩት፤ እከሊትን በእዚህ አወቅናት ስንል የምናነሳው ተጨባጭ ውጤት አለ። ጋንዲን በሰብዓዊ መብት አወቅነው ዊንስተን ቸርችልን ስለ ነጻነት በሄዱበት እርቀት፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ ስለ እኩልነት በጉልህ የፊትለፊት ሰው ሆኖ በከፈለው ታላቅ መስዋእትነት፤ ቢልጌት በቴክኖሎጂ አብዮተኛነቱ አወቅነው። እንዲህ እያልን ሌሎችንም መጥቀስ እንችላለን። እነህ ግለሰቦች አንድ ግለሰብ ሆነው ሳለ ለዓለም ባበረከቱት አስተዋጽኦ የታወቁ ሆነው አገኘናቸው። እይታቸው ይዟቸው ከወጣበት ከፍታ ላይ ቆመው ዓለም አያቸው፤ ወደ ከፍታው ለመድረስ ያለፉበት መንገድ ትልልቅ መጽሐፍ ይወጣዋል።

ዛሬ ሰዎች እንዲያውቁን ከመድከም የጠራ እይታ ኖሮን፤ ተፈጽሞ ልናይ የምንወደው ሆኖ እንድናይ እንመላለስ። ዛሬ በማህበራዊ ሚዲያ ዘመን የሚከተሏቸውን ሰዎች ለማብዛት ትኩረት ሳቢ በሆነ እንቅስቃሴ የተጠመዱ ሰዎችን እናገኛለን። እኛም ከእነርሱ አንዱ ሆነን እንደሆነ በፍጹም አንድከም፤ ስራችን ስለ እኛ መናገር ሲጀምር ሰዎች እንዲከተሉን ሳንጠይቃቸው የሚከተሉን ሆነው እናገኛቸዋለን።

የጠራ እይታ በያዝን፤ በያዝነው እይታ መሰረት በግለት ለመልካም ስራ በተጋን ቁጥር ለውጥ እናመጣለን። የምናመጣው ለውጥ ውስጣችን በተቀጣጠለው እሳት ልክ በተሰማራንበት ዘርፍ ውስጥ ወደ ፊትለፊት ይዞን ይወጣል።የተቀጣጠለው እሳትም ነዳጅ ሆኖን ልንሆን ያሰብነው ጋር እንድንደርስ ያግዘናል። ወደ ውስጣችን ብንመለከት በአንዳች ጎልቶ በወጣ ነገር ውስጣችን ሲቀጣጠል ልናገኘውም እንችላለን።

በታሪክ መዝገብ ውስጥ ስለ ሰው ልጆች መልካም ይሆን ዘንድ በብዙ የተጋደሉ ሰዎች መደበኛ ህይወት ኖረው ካለፉ ሰዎች በተጨባጭ የሚለዩ ናቸው። ይህ በሁሉም ዘርፍ ተመሳሳይ ነው። ጠንካራ የውስጥ ፍላጎት የጠራ እይታን ሰጥቷቸው በጠራ እይታ ወደ ተራራው የደረሱ። ደካማ ፍላጎት ደካማ ውጤት ነው የሚያመጣው። ትንሽ እሳት ትንሽ ሙቀት እንደሚፈጥር ማለት ነው። ትልቁ የውስጥ እሳት ግን አንዳንዴ በትንሽ ነገር እንዳይጋረድ ጥንቃቄን በሚሻ አካሄድ።

ትንሽዋ ሳንቲምና የተራራው ምሳሌ

ወደ ትልቁ ተራራ የሚደረገውን ጉዞ መገዳደር በተመለከተ የትንሿ ሳንቲምና የተራራው ምሳሌ በአስተውሎት እንመልከት። ተራራው ገዝፎ የሚታይ እሩቅ ሆኖ እይታ ውስጥ መግባት የሚችል ነው። ከእርቀት የሚታየውን ተራራ ግን ትንሿ ሳንቲም ወደ አይናችን ባስጠጋን ቁጥር እየጋረደችው ትመጣለች። ሳንቲሙ ወደ አይናችን አብዝቶ ከተጠጋ አብዝቶ የተራራው ምስል እየደበዘዘ ይመጣል።

እይታ በትንሽ ነገር ከተጋረደ ትልቁን ምስል ማየት የማንችልበት ደረጃ ላይ እንደርሳለን። ትልቁ ምስል ከተጋረደ እለታዊ እንቅስቃሴያችን ትንሽ ይሆናል፤ አይናችንን በቀረበው ነገር ልክ ይያዛል። ዛሬ ከእይታ ውስንነት የተነሳ እንቅስቃሴያችን በሰፊው የተገደበ እንደሆነ እናስተውላለን። የፖለቲካ ስሪታችን እንዲሁም አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ጉዟችን የሚገነባ ሳይሆን የሚያፈርስ ሆኖ ይታያል። በመቀራረብ አቅምን አሰባስቡ ድምር ውጤቱ ሁሉንም አሸናፊ ከሚያደርግ ጉዞ ይልቅ ሁሉም በጋራ ተሸናፊ የሚሆንበት መንገድን የመረጥን ይመስላል።

ተቃርኖው መቆሚያው የት እንደሆነ እርግጠኛ ባንሆንም የእይታ ልክ ግን የሚሰራው ስራ ስለመኖሩ አንዳች ጥርጥር የለንም። ትንሿን ሳንቲም ከአይን ላይ አንስቶ የሚሆን እይታ።

የአይን ህክምና ሰዎች የአይንን የማየት አቅምን ተመልክተው የእይታ ደረጃችን ላይ አስተያየት እንደሚሰጡ ሁሉ በሀገራችን እየተገበርናቸው ባሉት ፖሊሲዎችና መሰል ተግባራት እይታችንን በመመርመር ወደ መፍትሔ መራመድ አለብን። ትንሽዋ ሳንቲም የጋረደችውን ተራራ ተመልክቶ ወደ ተራራው የሚደረገውን ጉዞ ከማደናቀፍ በተራራው ስር ያለውን ሃብት አውጥቶ መጠቀም ተገቢነት እንዳለው አምኖ እይታን ማስተካከል።

በትንሿ ሳንቲም የሚወከል እይታችንን የጋረዱትን ነገሮች ለማንሳት ብንሞክር የምናገኛቸው እውነታዎች በዙሪያችን ያለውን ሁኔታ አግዝፈን በማየት አልችልም ማለታችን፤ በዙሪያችን ያሉ ተስፋ አስቆራጭ ድምጾችን አድምጠን መቆማችን፤ ትናንት ሞክረው ያልተሳካላቸው ሰዎችን ምክር ሰምተን ከጉዞ መታቀባችን፤ ደጋግመን አንኳኩተን ያልተከፈተውን በር አጥብቀን ከማንኳኳት መመለሳችን፤ ከእለት ወደ እለት እየደቀቀ ያለ ኢኮኖሚ የሚፈጥረው ተስፋ ቢስነት ህልማችንን እንደ ቅዠት መቁጠራችን ወዘተ ናቸው።



አንባቢው እንዲረዳው የሚያስፈልገው ነገር በመነሳሳት ወይንም በተቀጣጠለ ልብ ውስጥ አንዳች ነገር ለማሳካት የሚነሱ ሰዎች ተቀምጠው ተግዳሮትን ከሚያወሩ በየትኛውም መንገድ የተሻሉ መሆናቸው ነው። ዛሬ በልባችን ውስጥ ያለውን ድምጽ በሚገባ አድምጠን መሄድ ወደ ምንፈልገው አቅጣጫ መራመድ እንድንችል ከልብ መነሳሳት ያስፈልገናል። ከሁኔታው በላይ መራመድ የሚያስችለን አቅም ከውስጣችን ፈልገን ከፈጣሪ ጋር ለመነሳት የእይታ ምልከታችን ወሳኝነት አለው።

በእይታችን ልክ የምንወርሰውን ተራራ እንመልከት። ተራራው ግዙፍ ነው፤ ተራራው በመካከል ካለው የትኛውም ተግዳሮት በላይ ልናየው የተገባም ነው፤ ተራራው ላይ ደርሰን ከፍታውን በተቆጣጠርን ጊዜ አካባቢውን በሚገባ መቃኘት የምንችልበትም ስፍራ ነው።

### ከተራራው ማዶስ

እይታውን ተራራው ላይ አድርጎ ጉዞን የጀመረ ሰው ከተራራው ጋር ሲደርስ ስኬቱን ያከብራል። በጉዞው የገጠሙትን ተግዳሮቶች እንዴት በድል እያሸነፈ እንደ ዘለቀ ከትዝታው ማህደር እያወጣ ደስታውን ያጣጥማል። ተራራው ጫፍ ጋር ደርሶ መቆም አንድ አመራጭ ሲሆን ሌላው አማራጭ ከተራራው ጫፍ ተነስቶ ሌላኛውን ተራራ ጫፍ መመልከት ነው። ወደ አዲስ ተራራ፤ ወደ በለጠው ከፍታ። ሁኔታ በተግባር ህይወት ውስጥ ቀላል አይደለም፤ ነገርግን የእይታ ሰዎች መገለጫ ነው።

በኢኮኖሚክሱ የሰው ልጅ ፍላጎት በቀላሉ የማይረካ መሆኑን እንረዳለን። በምድር ላይ ያለው ሃብት ውስን ቢሆንም የሰው ልጅ ፍላጎት ግን የሚቀጥል ነው። አንድ ሰው በህይወት ጉዞ ውስጥ ራሱን ሲያገኝ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ እሴትን መያዝ አለበት። ከአንድ ተራራ ወደ ሌላ ተራራ በጽናት የመጓዝ በስተመጨረሻም በአሸናፊነት ማማ ላይ ለመድረስ።

ከተራራው ማዶ ሌላኛውን ተራራ መመልከት ውስጥ ጽናት አለ። እይታን አጥርቶ የመጓዝ ጽናት። ልጆች ማሳደግ ምን ያህል አስቸጋሪ መሆኑን ልጆችን በማሳደግ ህይወት ውስጥ ያለፉ ያውቁታል። ሰዎችን መምራት ምን ያህል አስቸጋሪ መሆኑን በመሪነት ውስጥ ያለፉ ሰዎች ይናገራሉ። አንዳንዱ ወደ ግራ እንሂድ ሲል ሌላው ወደ ቀኝ ሲል በመካከል በሚፈጠረው መሳሳብ አማካኝነት የሚሆን አስቸጋሪነት። ከተራራው ማዶ የሚያዩ ሰዎች የተግዳሮቱ ምንጭ ምንም ይሁን እያንዳንዱን ቀን በእሴት የተሞላን ኑሮን በመኖር ወደ ውጤት ይደርሳሉ።

በህይወት ጉዞ ውስጥ ከአራቱም አቅጣጫ የሚመጣውን ተግዳሮት ተቋቁሞ ወደ ውጤት መድረስ እንዲቻል የእይታ ልክ ወሳኝነት አለው። ነገሮችን በልካቸው ማየት፤ ያየነውን ትልቁን ምስል ጠብቀን መራመድ፤ በብርቱ መነሳሳት።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ከጀብሎ ንግድ ወደ ፋብሪካዎች ባለቤትነት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ገና ከልጅነታቸው አንስቶ ለንግድ ሥራ የተሰጡ ናቸው:: በሕይወት ዘመናቸው ችግር ነው ያሉትን ሁሉ ወደ እድል ለመቀየር ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ:: በጥረታቸውም ስኬታማ መሆን ችለዋል:: ለጊዜ ትልቅ ዋጋ የሚሰጡና የጊዜን ጥቅም በሚገባ መረዳት የቻሉም ናቸው:: ማንም ሰው ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም ከቻለ ስኬታማ መሆን ይችላል የሚል ጠንካራ እምነት አላቸው::

ይህን እምነታቸውን በተግባር በማዋል የወጣትነት ጊዜያቸውን በሥራና ሥራ ላይ ብቻ አድርገዋል:: ተማሪ እያሉ ጀምሮ ትርፍ ጊዜያቸውን ትናንሽ በሚባሉ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ አሳልፈዋል:: ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምረውም ንግድ አዋጭ የሆነ ሥራ ስለመሆኑ በተግባር መረዳት ችለዋል:: በመሆኑም ከልጅነት እስከ ዕውቀት የተሰማሩበትን የንግድ ሥራ በማሳደግ ዛሬ ለበርካቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ያስቻሉ ሶስት ኢንዱስትሪዎች ባለቤት ለመሆን በቅተዋል::

ተወልደው ባደጉበት አካባቢ ከትናንሽ ንግድ ጀምረው፤ በተለያዩ ወጪ ገቢ የንግድ ሥራዎች ውስጥ የተሳተፉት የዛሬው እንግዳችን አቶ ታዬ ተፈሪ ጂማ ይባላሉ:: አቶ ታዬ፤ በአሁኑ ወቅት በቡራዩ ከተማ በታጠቅ ኢንዱስትሪ መንደር ሁለት ፋብሪካዎች እንዲሁም በድሬዳዋ የቡና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ አላቸው:: በቡራዩ ከሚገኙት ፋብሪካዎች አንደኛው ኒው ፍላወር ፎም ይባላል፤ ሁለተኛው ደግሞ ኒው ፍላወር የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ ነው::

የእነዚህ ሶስት ድርጅቶች መስራችና ባለቤት የሆኑት አቶ ታዬ፤ ሰሜን ሸዋ ሰላሌ አካባቢ ተወልደው ሀረር ከተማ ነው ያደጉት:: በጫትና በንግድ በምትታወቀውና ሞቅ ደመቅ ባለችው ሀረር ከተማ ያደጉት አቶ ታዬ፤ በአካባቢው ማደጋቸው በንግዱ ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆኑ እንዳገዛቸው ነው የሚናገሩት::

ከአርሶ አደር ቤተሰብ የተገኙት አቶ ታዬ፤ በቤተሰብ እቅፍ ውስጥ ሆነው ምቾታቸው ተጠብቆ ለመኖር አልታደሉምና ከቤተሰብ ተለይተው ሀረር ላይ ከዘመድ ጋር ነው ያደጉት፤ ከቤተሰብ ውጭ ማደግ በራሱ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ጠቅሰው፣ ለተለያዩ ፍላጎቶች በቀላሉ መልስ ማግኘት አያስችልም ይላሉ:: እሳቸውን ግን ጠንካራና ብርቱ ሳያደርጋቸው እንዳልቀረም ይናገራሉ::

ጎዶሎዎችን ለመሙላትም ሆነ ጎዶሎውን አምኖ ለመቀበል ግን የሰውዬው ምርጫ ወሳኝ ነው፤ ብለው የሚያምኑት አቶ ታዬ፤ ታዲያ የነበራቸው ምርጫ አንድና አንድ ጎዶሏቸውን በጥረታቸው መሙላት ነበር:: እናም ከቤተዘመድ ጋር ሲያድጉ ይገጥማቸው የነበሩ ችግሮችን ሁሉ በራሳቸው ጥረት ለመፍታት ከላይ ታች ብለዋል፤ ወጥተዋል፤ ወርደዋል፤ ሰዎች የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለማለፍ በሚያደርጉት ጥረት ልክ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉና ችግር በራሱ ዕድል እንደሆነ የሚያምኑት አቶ ታዬ፤ በቤተዘመድ እጅ ውስጥ ማደጋቸው ራሳቸውን ለማሸነፍ ጥሩ መንገድ እንደሆነላቸው ይናገራሉ::

ሰዎች ድህነትን እንደ ጥሩ አጋጣሚ ሊጠቀሙበት ይገባል ብለው የሚያምኑት አቶ ታዬ፤ በሕይወታችን ማግኘት የምንፈልጋቸውን ነገሮች ለማግኘት የምንጠቀመው ጥረትና የምናወጣው ኢነርጂ ኃይል ሊፈጥር እንደሚችል ያስረዳሉ:: ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ደግሞ ይበልጥ ፍሬያማ ሊያደርግ የሚችል ቁልፍ መሳሪያ እንደሆነ በመጥቀስ ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው ከልጅነት እስከ ዕውቀት ኑሮን በማሸነፍ ትግል ውስጥ አልፈዋል:: በዚህም ከሱቅ በደረቴ ንግድ ተነስተው ወጪ ገቢ ንግድን አሳልጠው ለበርካታ ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችሉ ሦስት ፋብሪካዎች ባለቤት ለመሆን በቅተዋል፡፡

ወደ ንግድ እንዲገቡ ምክንያት የሆናቸው ችግር ቢሆንም፣ ለንግድ ሥራ ከፍተኛ የሆነ ውስጣዊ ፍላጎት የነበራቸው መሆኑን አቶ ታዬ ያስታውሳሉ:: ሀረር የጫት አገር እንደመሆኑም ለውዝን ጨምሮ የተለያዩ ሸቀጦችን በእጃቸው ይዘው ከቦታ ቦታ ተዘዋውረው ነግደዋል::



**አቶ ታዬ ተፈሪ ጂማ**

ይህ አይነት ንግድ በአካባቢው አጠራር ‹‹ጀብሎ›› ይባላል:: የጀብሎ ንግድ አዲስ አበባ ከተማ ላይ ሱቅ በደረቴ የሚባለው የንግድ አይነት መሆኑ ነው:: ጊዜያቸውን በአግባቡ የተጠቀሙት አቶ ታዬ፤ ከአፍላ ዕድሜያቸው ጀምረው ሀረር ከተማ ላይ የተለያዩ ሸቀጦችን በማዞር የጀብሎ ንግድን አቀላጥፈው ነግደዋል:: በትንሹ የጀመሩት ንግድ መሰረት እስኪይዝ ድረስም በርካታ ውጣውረዶችን አሳልፈዋል::

ከጀብሎ ንግድ ቀጥለው የተለያዩ አልባሳትና የአንሶላ ጨርቆችን በሀረር ዙሪያ በሚገኙ የገጠር ከተሞች በሙሉ ተመላልሰው የነገዱት አቶ ታዬ፤ ለአብነትም ቆቦ፣ ለገገባ፣ ቆሬና አረርቲ፣ ገንደሮባ፣ ዳዱ፣ በደኖና በሌሎችም ገጠራማ አካባቢዎች መኪና በማይታሰብበት በዚያን ወቅት ወጣትነት ትኩስ ኃይል ሆኗቸው በእግራቸው ተመላልሰው መነገድ በመቻላቸው እነሆ ዛሬ ከከፍታው ማማ ላይ ደርሰዋል::

በአሁኑ ወቅት በቡራዩ ከተማ የኢንዱስትሪ መንደር ሁለት ፋብሪካዎችን እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ የቡና ማቀነባባሪያ ፋብሪካን እያስተዳደሩ የሚገኙት አቶ ታዬ፤ ቡናን ከሚያለሙ በሀረር አካባቢ ከሚገኙ አርሶ አደሮችና በሌሎች አካባቢዎች ከሚገኙ አርሶ አደሮች ጋር ትስስር በመፍጠር በያመቱ ቡና ለውጭ ገበያ ያቀርባሉ::

በድሬዳዋ ከተማ በአስር ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ቦታ ላይ ባረፈው በዚህ የቡና ማቀነባበሪያ ፋብሪካቸው ከአርሶ አደሩ የሚሰበሰበውን ቡና በማቀነባበር በመቀሸር፣ በማበጠርና በመልቀም ለሳውዳረቢያ፣ ለአሜሪካ፣ ለጃፓንና ለኮሪያ ገበያ ይቀርባል:: በዚህም ለአገሪቷ የውጭ ምንዛሪ ግኝት የድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ::

በኒው ፍላወር የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ ባለ ሁለት፣ ሶስትና አራት እግር ተሽከርካሪዎች ይገጣጠማሉ፤ በተለይም ባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪ የሆነው ባጃጅ ለበርካታ የአገሪቱ ወጣቶች የሥራ ዕደል በመፍጠር ትልቅ አበርክቶ እያደረገ ይገኛል:: ለማህበረሰቡ የትራንስፖርት ችግርን ከመቅረፍ ጀምሮ ለወጣቶች የሥራ ዕድል እየፈጠረ በመሆኑ ፋብሪካው በተለይ ባለ ሶስት እግር ባጃጆችን በስፋት እንደሚገጣጠም አቶ ታዬ ያብራራሉ::

በአሁኑ ወቅት በየአካባቢው እየተርመሰመሱ ለሚገኙት ባለ ሶስት እገር ባጃጆች እርሳቸው ድርጅት የሆነው ኒው ፍላወር የመኪና መገጣጠሚያ ትልቅ ድርሻ አለው:: በርካታ ቁጥር ያላቸውን ህንድ ሰራሽ ባጃጆች አካላትን ከህንድ እያስመጡ በህንዳውያን ባለሙያዎች በመገጣጠም ለገበያ እያቀረቡ ናቸው::

አብዛኞቹ የባጃጅ ዕቃዎች ከህንድ የሚመጡ ቢሆንም፣ በአገሪቷ አቅም ልክ የሆኑ የተወሰኑ ዕቃዎች ግን በአገር ውስጥ የሚገኙ ስለመሆናቸው አቶ ታዬ፤ ይናገራሉ:: በአገር ውስጥ የማይገኙት ዕቃዎች ደግሞ

**በእነዚህ ሦስት ፋብሪካዎች ውስጥ ሰርተው የሚውሉ፤ እንጀራ መብላት የቻሉና ከራሳቸው አልፈው ቤተሰብ ማስተዳደር የጀመሩ 1400 የሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል**

ከህንድ አገር የሚመጡት የባጃጅ አካላት በአገር ውስጥ ተገጣጥመው በኤጀንቶች አማካኝነት ለገበያ እየዋሉ እንደሆነ ተናግረዋል::

‹‹ከህንዶቹ የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ባጃጆቹን ሙሉ ለሙሉ በአገር ውስጥ መመረት እንዲችሉ የማድረግ ዕቅድ አለኝ›› ያሉት አቶ ታዬ፤ በአሁኑ ወቅትም በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ውስጥ እንዲሰሩ ከህንድ አገር ቀጥረው ያስመጧቸው 20 የሚደርሱ ህንዳውያን ስለመኖራቸው አንስተዋል:: ህንዳውያኑም በዘርፉ ያላቸውን ዕውቀት ለኢትዮጵያውያን በማሸጋገር ኢትዮጵያውያኖች ሰልጥነው ብቁ ሲሆኑ እንደሚመለሱ ነው ያጫወቱን:: በቀጣምይም ይህንን አጠናክሮ በማስቀጠልና አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በማሟላት ሙሉ ለሙሉ በአገር ውስጥ ለመሥራት ጥረት እያደረጉ እንደሆነም አቶ ታዬ ይጠቁማሉ::

ለአልጋ፣ ለሶፋ፣ ለመኪና እና ለሌሎች ተግባራት የሚውለው ፎምም እንዲሁ በኒው ፍላወር ፎም ፋብሪካ ተመርቶ ለተለያዩ ጅምላ ሻጮች ወይም ደግሞ ወኪል አከፋፋዮች ይቀርባል:: በእነዚህ ወኪል አከፋፋዮች አማካኝነትም በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ምርቱ ተደራሽ ይሆናል::

በእነዚህ ሶስት ፋብሪካዎች ውስጥ ሰርተው የሚውሉ፤ እንጀራ መብላት የቻሉና ከራሳቸው አልፈው ቤተሰብ ማስተዳደር የጀመሩ 1400 የሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ስለመሆኑ አቶ ታዬ አጫውተውናል::

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም አቶ ታዬ፤ የተለያዩ አገልግሎቶችን እየሰጡ ናቸው:: ለአብነትም በቡራዩ ከተማ የእርሳቸውን ሁለት ፋብሪካዎች ጨምሮ በርካታ ፋብሪካዎች ለሚገኙበት ታጠቅ የኢንዱስትሪ መንደርና በአካባቢው ለሚገኘው የፌስቱላ ሆስፒታል ጭምር አገልግሎት መስጠት የሚችል የአስፓልት መንገድ ሲሰራ በኢንዱስትሪ መንደር ውስጥ የሚገኙ የፋብሪካ ባለቤቶችን በማስተባበር ሰርተዋል::

አቶ ታዬ፤ በወቅቱ ሃሳቡን ያነሱት በዋናነት በፋብሪካዎች ውስጥ የሚመረቱ የተለያዩ ምርቶች ምግብና መጠጥን የሚጨምሩ እንደመሆናቸው ከብክለት ነጻ እንዲሆኑ በማሰብ ነው:: ከዚህ ባለፈም በአካባቢው ከሁለት መቶ ሺ እስከ ሶስት መቶ ሺ የሚደርሱ ሠራተኞች የሚጠቀሙበት መንገድ መሆኑም ጭምር የመንገዱ አስፓልት መሆን የግድ እንደነበር ነው የሚናገሩት:: ይሁንና በጋራ የጀመሩት የአስፓልት ሥራ ዳር ሳይደርስ ከህዝብ የተሰበሰበው ገንዘብ በአጭበርባሪዎች ተበልቶ ቀርቷል::

ለዚህም ምክንያቱ በሥራው ያላቸው ልምድና ዕውቀት ማነስ እንደነበር ያነሱት አቶ ታዬ፤ በድርጊቱ ቁጭት ገብቷቸው ‹‹ተጀምሮ የሚቀር ሥራ የለም›› በማለት የመንገድ ሥራው እንዲጠናቀቅ በግላቸው ተንቀሳቅሰው ብዙ ዋጋም ከፍለው መንገዱ እንዲጠናቀቅ አድርገዋል::

የአስፓልት መንገድ ሥራውም በአስር ኮንስትራክሽን የተሠራ ሲሆን፣ አቶ ታዬ በግላቸው 35 ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የመንገድ ሥራው እንዲጠናቀቅ በማድረግ ቁጭታቸውን ተወጥተዋል:: በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የአስፓልት መንገዱ ለአካባቢው ማህበረሰብ፣ በኢንዱስትሪው ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞችና በፌስቱላ ሆስፒታል ተገልጋይ ለሆኑ ተጎጂዎች ጭምር ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል::

ከዚህ በተጨማሪም ስድስት ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ ለመንገዱ መግቢያ ያሰሩ ሲሆን፤ ከመግቢያው ጀምሮ አጠቃላይ መንገዱ በጀነራል ታደሰ ብሩ ስም ተሰይሟል:: ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያትም ጀነራሉ በጀግንነት የአገራቸውን ሉዓላዊነት ከማስከበር ባለፈ በአገሪቱ አንድነትን፣ ትምህርትንና ሌሎች በጎ ተግባሮችን በማበርከት ያላቸውን የአገር ፍቅር ስሜት በተግባር ያስመሰከሩ አገር ወዳድ በመሆናቸው ነው ይላሉ::

የአስፓልት መንገዱ ሁለት ነጥብ ስምንት ኪሎ ሜትር ርዝመትና 10 ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን፤ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንዳለውም አቶ ታዬ አስረድተዋል:: መንገዱ በአካባቢው ከሚገኙ ነዋሪዎችና ሠራተኞች ባለፈ የኢንዱስትሪ መንደሩ ምርቶች ንጽህናው በተጠበቀና በተቀላጠፈ መንገድ ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግም መላው የአገሪቱ ህዝብም ተጠቃሚ መሆን እንዲችል የተደረገበት መሆኑን ያብራራሉ::

በእነዚህና በሌሎችም የልማት ሥራዎች በመሳተፍ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ የሚገኙት አቶ ታዬ፤ በተለይም አገራዊ ለሆኑ ማንኛቸውም ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት ቀዳሚ ናቸው:: በዚህም ጥቂት የማይባሉ የምስክር ወረቀቶችንና ዋንጫዎችን ከቡራዩ ከተማ እንዲሁም ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ተበርክቶላቸዋል::

በቀጣይም በተሰማሩበት የሥራ ዘርፎች ይበልጥ ጠንክረው በመሥራት ውጤታማ ለመሆን ዕቅድ እንዳላቸው ያጫወቱን አቶ ታዬ፤ ‹‹እያንዳንዱ ሰው ጊዜውን በአግባቡ ተጠቅሞ ከሰራ ውጤታማ መሆን ይችላል›› በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል::

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ‹‹ያየነው የአሸናፊዋን ኢትዮጵያ ገጽታ ነው››

### - ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

**የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት ትናንት በስኬት ተጠናቅቋል፤ በስነስርአቱ ላይ የተገኙት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ የእንኳን አደረሰን ንግግር አድርገዋል። የፕሬዚዳንቷን ንግግር ሙሉ ቃል እንደሚከተለው አቅርበነዋል።**

አንዳንድ ቀኖች አሉ፤ ከሌሎች ጋር የማይመስሉ፤ ልዩ የሆኑ። አንዳንድ ቀኖች አሉ፤ ደስታም ሆነ ሀዘን በቅጡ ለመግለጽ የማይቻልባቸው። አንዳንድ ቀኖች አሉ፤ ከደስታ ብዛት በርካታ ነገሮችን ለመናገር የማንችልባቸው። ይህ ቀን ዛሬ ነው።

አንዳንድ ቀኖችም አሉ፤ ፈጣሪን በቅጡ የምናመሰግንበት። አንዳንድ ቀኖች አሉ ይህንን ለማየት እንኳን ፈጣሪ በሕይወት አኖረኝ የሚያስብሉ። በተለይ ለኔ ዛሬ እዚህ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዘንድ ሆኜ ይህንን ለመናገር በመቻሌ እግዚአብሔርን በቅጡ አመሰግነዋለሁ።

ይህ ቀን ልዩ ነው። አባይ ላይ ግድብ መስራት በብዙ ትውልዶች እንደ ህልም የሚታይ ነበር። እንደ ሩቅ ህልም፣ እንደ ሩቅ ተስፋ። ነገር ግን ኢትዮጵያዊያን አማኞች አይደለንም እንዴ፤ ስለዚህ ተስፋ መሰነቅ የሚያቅተን አይደለንም።

በአፈ ታሪክ እንደምንሰማው፤ እንደምናየው፤ በተመዘገበም ታሪክ ዓባይ ላይ ግድብ ለመስራት የታሰበ እንደሆነ እናውቃለን። በኋላም ራእይ ይዘው እኛ ባንችል ትውልድ ይሰረዋል ብለው የተናገሩ መሪ ነበሩን። ቀጥሎም ድፍረው ወደፊት ገፍተው ለዚህ ግድብ መሰረተ ድንጋይ ያስቀመጡ መሪ ነበሩ። ይህንን ስራ ያስቀጠሉ መሪም ነበሩ።

ቀዝቅዞ የነበረውን፤ ተቋርጦ የነበረውን ስራ በማስቀጠል በትልቅ ድፍረት ኢትዮጵያን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከልመና፣ ከርሃብ፣ ከችግርና ከኋላ ቀርነት ማላቀቅ አለብን ብለው የተነሱ፣ ይህ ስራ እንዲጠናቀቅ ያደረጉ፣ ከዛም በኋላ አሁን እንደምናየው ግድቡ ኃይል ማመንጨት ድረስ እንዲደርስ ያደረጉ፣ ከአንድም ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት እንዲጀምር ያደረጉ፣ ይህ ሶስተኛው ሙሌት እንዲካሄድ ያደረጉ፤ ተስፋችን እውን እንዲሆን ያደረጉ መሪ ደግሞ አየተናል፤ አሉን።

ይህ ግድብ ከግድብነቱ ያለፈ ነው። ይህ ግድብ የመብራት ኃይል ከማመንጨት ያለፈ ትርጉም አለው። ከጭለማ ወደ ብርሃን ከማሸጋገር ያለፈ ነው። ይህ ትልቁ ግድባችን ጾታ የለውም። ሃይማኖት የለውም። የተለየ ዘር የለውም፣ የተለየ ቀለም የለውም፤ ኢትዮጵያዊ ግድብ ነው።

ኢትዮጵያዊያን ከተባበርን ለዚህ መድረስ እንችላለን ብሎ የሚያሳይ ነው። ይህንን ግድብ ዛሬ ነሐሴ ላይ እዚህ መጥተን አረንጓዴ፣ ቀዝቀዝ ያለ አየር ላይ ሆነን ነው የምናየው። በሀሩር ነው በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ይህንን ግድብ ለዚህ ያበቁት፤ ይህንን ስራ የሰሩት። ኢንጂነሮች አመራር የሰጡ ዛሬ በሕይወት የሌሉ፣ አሁን ደግሞ ያሉት ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮን የመሳሰሉት መርተውታል፤ ለእዚህ አብቅተውታል።

የውጭ ድርጅቶችም በእዚህ ግንባታ ተሳትፈዋል። ነገር ግን ከሁሉም በላይ እናንተ ኢትዮጵያውያን በልታችሁ ሳትጠግቡ፣ ነገ ያልፍልናል ብላችሁ ገንዘብ



ያዋጣችሁ፣ እናንተ ኢትዮጵያውያን ለእዚህ ግድብ የተረባረባችሁ፤ አገር ውስጥም የምትኖሩ ሆነ በውጭ አገር ያላችሁ በእጅጉ ልትመሰገኑ ይገባል።

ይህ ግድብ ከእዚህ በላይ ነው ትርጉሙ፤ ኃይል ከማመንጨት በላይ ነው። ኢትዮጵያውያን እንችላለን የሚለውን የሚያሳይ ነው። ኢትዮጵያውያን ከተባበርን ብዙ መስራት እንችላለን፤ ዛሬ ያየነው ከዚህ በፊት እንዳልኩት የአሸናፊዋን ኢትዮጵያ ገጽታ ነው። ኢትዮጵያ እንደዚህ ነች፤ ኢትዮጵያን እንደዚህ ነው ማድረግ ያለብን። ኢትዮጵያን ዛሬ የደስታ እንባ እንድታፈስ እናደርጋታለን። ነገር ግን የሀዘን እንባ እንድታፈስ አርገናታል። ይህንን ማወቅ አለብን ፤ ማመን አለብን። ከዚህ ለመወጣት መስራት አለብን።

አንችልም እንዳንል እንደምንችል እያሳየን ነው። ስለዚህ በዛሬው ትልቅ ቀን በእውነቱ ልናከብር ፈጣሪያችንን ልናመሰግን፣ አሁን ወደ ልማት እንድናተኩር የሚጋብዘን ነው። ሌላ ምንም ምክንያት የለንም፤ ይህ ኃይል መንጭቶ ለህዝባችን በፍትሃዊነት በዘላቂነት የሚደርስበትን ሁኔታ አመቻችተን አገራችንን ወደፊት እንድትራመድ ማድረግ ይኖርብናል።

እኔ ለማለት የምፈልገው በእውነቱ እንኳን ደስ አለን ነው። ላም አለኝ በሰማይ ከሚለው እንድንወጣ እያደረግን ነው። የኛ ስራ ውይይትን፣ ምክክርን የሚከለክል አይደለም። እንዳውም የዚህ ግንባታ እዚህ መድረስ ለጎረቤት አገሮች ከናይል ተፋሰስ አገሮች ጋር የበለጠ ትብብር ምክክር እንዲኖረን ከአገር አልፎ አካባቢውን ከአካባቢ አልፎ አህጉራችንን ለማሳደግ ነው መነሳት ያለብን።

በጠባብ ማሰብ የለበንም። እናም በጋራ እንድንሰራ የዲፕሎማሲውን በር በሰፊው የሚከፍት ነው። ለማንኛውም ዛሬ ትልቅ ቀን ነው፤ እንኳን ለዚህ አደረሰን፤ ድጋፋችሁ ይቀጥል.፤ በርትተን እንስራ፤ ኢትዮጵያ ላይ ይህንን ያሳየን ሌሎች ተአምሮችን ማሳየት እንደምንችል ነው የምናየው። እንኳን አደረሰን፤ አመሰግናለሁ።

## ከጉባ ሰማይ ስር የተበሰረው ድርብ ድል

መሳኩ ኤሮሴ

ባለፉት ሁለት ቀናት ብቻ በጉባ ሰማይ ስር ድርብ ድሎች ተበስረዋል። በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን /ዩኒት ዘጠኝ/ ከትናንት በስቲያ በይፋ ኃይል ማመንጨት የጀመረ ሲሆን፣ ትናንት ደግሞ በጉጉት ሲጠበቅ የቆየው የሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌትም ተጠናቋል።

የግድቡ ሁለተኛው ተርባይን የተሳካ የተከላና ሙከራ ስራ ከተደረገለት በኋላ ነው ኃይል ማመንጨት የጀመረው። ተርባይኑ ኃይል ማመንጨት መጀመሩና የግድቡ ሶስተኛው ዙር ሙሌት ተጠናቅቆ ውሃ በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ አናት ላይ መፍሰስ መጀመሩ ለኢትዮጵያዊያን ድርብ ድል ነው።

ተርባይኑ ኃይል ማመንጨት በጀመረበት ስነ ስርአት ላይ እንደተገለጸው፤ ተርባይን ዘጠኝ በዚህ የከፍታ መጠን 270 ወይም ከዛ በላይ ሜጋ ዋት ያመነጫል። ግድቡ ሲጠናቀቅ ወይም ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ 640 ሜትር ሲደርስ ግን በሙሉ ሃይሉ 375 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ይኖረዋል።

ተርባይኑ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ለመላው ኢትዮጵያዊያን ትልቅ ድል ነው። ከአፋቸው ከፍለው ለግድቡ ገንዘብ ሲያዋጡ ለነበሩት ኢትዮጵያዊያን በእርግጥም ትልቅ ሀሴትን ፈጥሯል። ከድሃ እስከ ሀብታም፤ ከህጻን እስከ አዋቂ ደስታውን እየገለጸ ይገኛል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ኃይል ማመንጨቱን ያስጀመሩት ሲሆን፣ በዚህ ስነስርአት ላይ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትም ተገኝተዋል። የሁሉም ክልሎች ፕሬዝደንቶች፣ መንግስታዊና የግል ድርጅቶች የደስታ ደግሞ መግለጫ እያወጡ ናቸው።

በተርባይን ዘጠኝ ኃይል የማመንጨት መርሃ ግብር ላይ ንግግር ያደረጉት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዋና ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ እንደተናገሩት፤ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ በ2014 ለማከናወን ከታቀዱት አብይ እቅዶች መካከል በሁለት ተርባይኖችና ጄኔሬተሮች ኃይል ማመንጨት አንዱ ሲሆን፣ ይህ እቅድ ተሳክቶ በሁለቱም ዩኒቶች ኃይል ማመንጨት ተችሏል። የሲቪል ስራዎችን ግንባታ ወደ 95 በመቶ፣ የኤሌክትሮ መካኒካል ፋብሪካና ተከላ ስራ ወደ 61 በመቶ ከፍ በማድረግ፣ እንዲሁም ውሃ ማስተላለፊያ የብረታ ብረት



ስራዎችን ወደ 73 በመቶ ከፍ በማድረግ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 83 ነጥብ 3 በመቶ ለማድረስ ተችሏል።

በቀጣይ ከሁለት እስከ ሁለት ተኩል ዓመታት ውስጥ ግድቡን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ በየደረጃው ሙሊት በማከናወን ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ነው ኢንጂነር ክፍሌ የጠቆሙት፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት አገሪቱ ከምንጊዜም በላይ ከውስጥም ከውጭም የተፈተነችበት ጊዜ ቢሆንም፤ ፕሮጀክቱን ለማሰናከል ከፍተኛ ርብርብ የተደረገበት ጊዜ ቢሆንም በመንግስት ሙሉ ድጋፍና ክትትል ፈተናዎችን በሙሉ በማለፍ የፕሮጀክቱ ግንባታ ሳይተጓጎል አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ማድረስ እንደተቻለ አብራርተዋል።

ዩኒቱን ኃይል ማመንጨት ያስጀመሩት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በበኩላቸው፤ አሁን ያለውን ትውልድ ለብዙ ዓመታት ሲታሰብ፣ ሲተለም፤ ብዙዎች ሲመኙት የነበረውን ዓባይን የመገደብ እና የመጠቀም መሻት በዓይኑ ያየ፣ በእጁ የዳሰሰ፣ በእግሩ የረገጠ ባለ እድል ትውልድ ነው ሲሉ ገልጸዋል። ያለፉት ትውልዶች ተመኝተዋል፣ አስበዋል፤ ይህ ትውልድ ያየውን ግን ማየት አልቻሉም። የዛሬው ትውልድ የቆመበትም መቆም አልቻሉም ብለዋል። ዛሬ ያሉ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ባለ እድልም ባለድልም መሆናቸውን እንዲያስቡና በዚህም እርካታ ሊሰማቸው እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያዊያን ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውን እና ጉልበታቸውን የገበሩለት ፕሮጀክት ነው። ብዙ ንጹሃን ዜጎች ግድቡ ተተግብሮ እንዲታይ ሕይወታቸውን ገብረዋል። የጸጥታ ተቋማት ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። ይህን ሁሉ ተግዳሮት ድል በመንሳት ግድቡ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ መድረሱን አቅልሎ ማየት አይገባም ሲሉ ያስገነዘቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያዊያን ለላቀው ድል እንዲነሳሱም አሳስበዋል።

ኢትዮጵያዊያን ኃይል በማመንጨት ኢኮኖሚ በማሻሻል፤ በጨለማ የሚኖር ህዝብ ብርሃን እንዲያገኝ የመፈለግ እንጂ የታችኞቹን ተፋሰስ አገራት የመጉዳት ዓላማ እንደሌላቸው በተደጋጋሚ መግለጻቸውንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል። ዘንድሮ የተካሄደው ሶስተኛው ሙሊት ያረጋገጠው 22 ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ መያዝ የሚያስችል እንዲሁም ሁለት ዩኒት ማመንጨት የሚያስችል ስራ ቢሰራም በታችኛው ተፋሰስ አገራት ላይ ምንም አይነት የውሃ እጥረት እንዳያጋጥም ኃይል እያመነጨንም ከዚያ ባሻገር በከፍተኛ ግፊት ወደ ታችኛው ተፋሰስ አገራት የሚሄድ ውሃ አንድም ቀን ሳይቋረጥ እንዲሄድ የተደረገበት ዋነኛው ምክንያት የታችኛው ተፋፈስ አገራት ሳይጎዱ የኢትዮጵያን የማደግና የመለወጥ ፍላጎት በተግባር ለማሳየት ነው ብለዋል።

የህዳሴ ግድብ አሁን ያለበት ደረጃ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ብልጽግና እውን የሚሆን፤ የኢትዮጵያን ብልጽግና ማንም ሊያቆመው እንደማይችል፣ ይህ የኢትዮጵያ ምዕራፍ፣ በመከወን፣ በመጨረስ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ የሚያድግ መሆኑን ማሳያ ነው። በዚህ ዓመት ለመስራት የታቀደውን ስራ ከ10 ቀናት በፊት ማጠናቀቅ መቻሉን አስታውቀዋል። ባለፈው ዓመት እየተሰራ ውሃው የቀደመ እንደነበር የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ዘንድሮ ግን የታሰበውን ቀድሞ ማሳካት መቻሉን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያውያን ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት በመጀመሩ እየተደሰቱ ባለበት ማግስትም የግድቡ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት ተጠናቅቆ ባለ ድርብ ድል መሆን ችለዋል። የሶስተኛው ዙር ውሃ ሙሌትም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትናንት በስፍራው ተገኝተው ይፋ አድርገዋል። የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንንን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት ተገኝተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በስነስርአቱ ላይ የሶስተኛውን ዙር ውሃ ሙሌት ከአምና ጋር እያነጻጸሩ አሳይተዋል። አምና በመሃከል ውሃ የሚፈስስበት ቦታ 575 ሜትር ነበር። ዘንድሮ ተጨማሪ 25 ሜትር ከፍ በማድረግ 600 ሜትር ላይ የውሃው ፍሰት ይታያል ሲሉ ጠቅሰው፣ ግራና ቀኝ አምና 585 ሜትር ነበር። ዘንድሮ 611 ሜትር በመድረስ በከፍተኛ ደረጃ ውሃ የመያዝ አቅምችንንና ኃይል የማመንጨት (ኢነርጂ ጀነሬት የማድረግ) አቅማችንን ከፍ አድርጎታል በማለት አብራርተዋል። ይህም በዚህ ስራ ለተሳተፉ ሰዎች እና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ደስታን የሚፈጥር ታላቅ ድል መሆኑን ጠቅሰው ‹‹እንኳን ደስ ያላችሁ፤ እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ›› ሲሉ ገልጸዋል።

‹‹ዓባይ የኢትዮጵያ ኩራት፣ ዓባይ የኢትዮጵያ የብልጽግና ጅማሮ መነሻ፣ ዓባይ ኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ ከፍታ የሚለመልምበት ቦታ መሆኑን ተገንዝበን፤ እስላም ክርስቲያን፣ ጉራጌ ስልጤ፣ ኦሮሞ አማራ፣ ሶማሌ አፋር፣... ሳንል ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጋራ በመደመር አንድ ላይ በመቆም ብልጽግናችንን እውን እንድናደርግ እና ከእርዳታ ከልመና ራሳችንን እንድንገላግል በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ


## ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያ ከፍታ ሁነኛ መገለጫ ነው!

ኢትዮጵያ በርካታ ፈተናዎች ተፈራርቀውባታል። በሀገር ውስጥ ሰላም እንዳይኖር ከማድረግ ጀምሮ ልማትና ዕድገቷን ቁልቁል ለማየት የቋመጡ ከውስጥም ከውጭም በርካቶች ነበሩ። ታላቁን የኢትዮጵያን የህዳሴ ግድብ እንዳትሰራ ብዙ ሴራዎች ተጠንስሶላታል። የገንዘብ እርዳታና ብድር እንዳታገኝ ቀን ከሌሊት ሳይታክቱ ሰርተዋል። ሆኖም በሕዝብና በመንግሥት ጥረት ፕሮጀክቶቹ ቀጠሉ እንጂ አልተቋረጡም። ሰላምና ልማታችንን ለማደናቀፍ ጥረት አደረጉ እንጂ አልተሳካላቸውም። ህልምና ምኞታቸው በተቃራኒው መሆኑ ሲያስደነግጣቸው በዓለም አቀፍ መድረኮች ጭምር ኢትዮጵያን አጀንዳ እስከማድረግ ደረሱ። በዚህ ተስፋ ያልቆረጠው ቆራጥ ሕዝብ ግን ያለ የሌለ ገንዘቡን እያዋጣ፣ እውቀት ያለው በእውቀቱ፤ ጉልበት ያለው በጉልበቱ ጭምር ፕሮጀክቱን እውን ሊያደርግ በአንድነት ቃል ተግባብቶ ወደ ስራው ገብቷል።

የኢትዮጵያ ልማትና እድገት አልዋጥ ያላቸው ጠላቶች ስኬቷን እንጂ ውድቀቷን ለማየት ቋምጠው በመነሳት የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ከፍተኛ ጉዳት ያደርስብናል በሚል የሕዳሴው ግድብ ግንባታም ሆነ የግድቡን ሙሌት ወደ ጸጥታው ምክር ቤት ሲወስዱ ቆይተዋል። ጉዳዩን ዓለም አቀፍ ስጋት ለማስመሰልም እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ታይተዋል። በተለይም ግብፅ የአባል ሀገራቱን ስምምነት በሚጥስ መልኩ አሁንም ጉዳዩን ወደ ጸጥታው ምክር ቤት ከመውሰድ አልተቆጠበችም። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የተፋሰሱን ሀገራት የመጉዳት ሃሳብ እንደሌላት ደግማ ደጋግማ አረጋግጣለች። በጋራ እንልማ ፤በጋራ እንጠቀም ብላለች፤ አሁንም ይሄንን አቋሟን አጠናክራ ቀጥላለች።

ኢትዮጵያ ሀቅ ይዛ ሕዝቧንና መንግሥቷን ተማምና ፤ ማስፈራሪያና ዛቻውን ሁሉ ወደ ጎን ብላ ቆራጥ በሆነው ሕዝቧና መሪዎቿ አሁን ለደረሰችበት ደረጃ ያደረሳትን እርምጃ አንድ ብላ ጀምራለች። ሁለት ብላ ቀጥላ ሶስተኛውን የውሃ ሙሌት በስኬት አጠናቃለች። ይሄ ታላቅ ድል ነው። ለሕዝቡም ትልቅ የአሸናፊነትን መንፈስ ከፍ የሚያደርግ ስኬት ነው። በከፍታችን ላይ የተገኘ ከፍታ ነው። በታሪክ መዝገብ የሚሰፍር የዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያን የጀግንነት ታሪክ ነው።

ይሄ የኢትዮጵያውያን ትጋትና ጥንካሬ ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገም ለሚታሰቡ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ማሳያ ነው። ለዓለም ጭምር ማስተማሪያ ነው። ሌሎች የማይደፈሩ የሚመስሉ ልማቶችን መጀመር ብቻ ሳይሆን መስራትና መጨረስ እንደሚቻልም ማመላከቻ ነው። ኢትዮጵያውያን በፈተና ውስጥ ሆነውም ያስመዘገቡት በርካታ ድሎችን ነው። በአረንጓዴ አሻራ ለዓለም ምሳሌ በሚሆን ደረጃ ግባችንን አሳክተናል። ከራሳችን አልፎ ጎረቤት ሀገራት ለማይበገር የአየር ንብረት ለውጥ የበኩላቸውን እንዲወጡ መሪ ሆነን ተከታይ እንዲሆኑ ማድረግ ችለናል። በዓለም አደባባይ ተጠቃሽ ምሳሌ ለመሆን በቅተናል። በበጋ ስንዴ፣ በመስኖ እርሻ ያቀድነውን ፈጽመናል። ዓለም በስንዴ እጥረት ሲታመስ እኛ ግን እጃችንን ወደ ጎተራችን መልሰናል። ሌላው ቀርቶ በአትሌቲክሱ የተገኙት ድሎች ፈተናዎችን ሁሉ ተጋፍጠን ማሸነፍ እንደምንችል ያሳየንበት ከፍታ ነው። በምንም አይነት ፈተና ውስጥ ሆነን ፈተናን ተጋፍጠን የምናሸንፍ ሕዝቦች መሆናችንን በተግባር ያረጋገጥንበት ነው። ይሄ የሚያስደስት ደግሞም የሚያኮራ ስኬት ነው። ሆኖም በዚህ ተኩራርተን የምንተኛ ሳንሆን አሁንም ወደፊትም የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች በድል እየተወጣን ከከፍታችን ጋር የምንራመድ መሆናችንን የምናረጋግጥበት ነው።



ለሀገራችን ብድርና እርዳታ እስከነፈጓት ዓለም አቀፍ ተቋማት ድረስ ከውስጥና ከውጭ ሆነው የጥፋት ሃይሎች ተባብረው ሲፈትኗት ተንገዳገደች እንጂ አልወደቀችም። አንድነቷን ሳይሆን መለያየቷን ፤ ብሎም መበታተኗን አስበውና አቅደው ሰርተዋል። ሁሉንም ፈተናዎች ግን ያለፈቻቸው በጥበብና በዘዴ ነው። ሁሉንም ፈተናዎችን ያለፈቻቸው በልጆቿ ብርቱ ጥረትና ትጋት ነው። በመሪዎቿ አዋቂነትና በሳል አመራር ሰጪነት ነው። ሀገራዊና ውጫዊ ችግሮች በየአቅጣጫው ቢሰለፉም ያንን ሁሉ መከራ በማለፍ ወደምንፈልገው የብልጽግና ማማ ለመውጣት ከሚያስችሉ ስራዎች ግን ያገደን ነገር የለምና አሁንም እንደከዚህ ቀደሙ የሚያጋጥሙ መሰናክሎችን በመበጣጠስና በማለፍ አስደማሚ የሚባሉ ውጤቶችን እያስመዘገብን ወደ ከፍታው ማማ እንወጣለን።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከትናንት በስቲያ ሁለተኛውን የሃይል ማመንጨት ስራ ጀምሯል። ይሄ በብዙ የዓለም ሀገራት ግምት ይሳካል ተብሎ የሚታሰብ አልነበረም። ህልማቸው ሁሉ በዚህ መልኩ ይሆናል የሚል ሳይሆን ተጨናግፎ ማየት ነበር። ይሄንን ምኞታቸውን እውን ለማድረግ ደግሞ በማደነቀፉና በሴራው ሲተባበሩ ከርመዋል። ሆኖም ግን በምንም መልኩ ከውጥኑ ሸብረክ የሚል መንግሥትና ሕዝብ የለም። ይልቁንም በአንድነት ፣ በጽናትና በመተባበር እንድንጠነክር ምክንያት ሆነውናል። የአንድነታችን መታወቂያ የሆነውን የህዳሴ ግድባችንን በራሳችን አቅም ለመገንባት ወስነን ይሄው አሁን ታላቁ የህዳሴ ግድብን ሁለተኛውን ዩኒት ኃይል እንዲያመነጭ ማድረግና ሶስተኛው ዙር ሙሌት በስኬት እንዲጠናቀቅ ማድረግ ችለናል። ይሄ የጥንካሬያችን፤ የይቻላል መንፈስ ማሳያ ነው። ከከፍታችን የማንወርድ ፣ በተሰለፍንበት ጎራ ሁሉ በድል የምንወጣ ሕዝቦች መሆናችንን ያረጋገጥንበትም ነው!




# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር ሙሌት በስኬት መጠናቀቅን ተከትሉ ትናንት ያስተላለፉት መልዕክት

# "ይህ ኢትዮጵያውያን ተባብረን አምጠን የወለድነው ታሪካዊ ስኬት እና ድል ነው"

- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር
እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን

የዛሬው ቀን ለሁላችንም ልዩ ቀን ነው:: ለዚህ ልዩ ቀን ለመድረስ አስተዋፅዖ ያደረግን ሁሉ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያ ወዳጆች፣ በዓለም አደባባይ በሁሉም ዘርፍ በዲፕሎማሲ፣ በቴክኒክ ስራ፣ በጥናት፣ በሙያው ድርሻ እዚህ ለመድረስ ያበቃችሁን በሙሉ፤ የሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት አባላት ሁላችሁም እንኳን ለዚህ ታሪካዊ ቀን አደረሳችሁ፤ አደረሰን ለማለት እወዳለሁ::

ኢትዮጵያውያን በየዘመኑ ብዙ ፈተናዎችን እየተሻገሩ ጠንካራ አገር ታላቅ ህዝብ ሆነን እዚህ ደርሰናል:: ይህ የዛሬው ልዩ ቀን ለተከታታይ ዓመታት ባደረግነው ርብርብና ስራ በአንድ ድምጽ፣ በአንድ ልብ፣ በአንድ የተባበረ ክንድ ብዙ ፈተናዎችን ተሻግረን ለዚህ ስኬትና ለዚህ ቀን በቅተናል:: ይህ ኢትዮጵያውያን ተባብረን አምጠን የወለድነው ታሪካዊ ስኬት እና ድል ነው:: በዚህ ልንኮራ፣ በዚህ ለላቀ ድልና ለላቀ ስኬት ልንሰለፍ ይገባናል/ይበቃናል::

ይህ የተፈጥሮ ፀጋ ከኢትዮጵያ ማህፀን እየፈሰሰ ለሺህ ዓመታት ተጉዟል:: አሁን ያለ አዲስ ነገር ቢሆን ኢትዮጵያውያን ተባብረን ፀጋውን ለብልጽግና፣ ፀጋውን ድህነትን ለማሸነፍና ለመለወጥ እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅም ለማድረግ አንድ ርምጃ ተጉዘናል:: ዓባይ ብዙ ተብሎለት ለሺህ ዓመታት ተጉዞ አሁን ዛሬ ለኢትዮጵያውያን አንድ ወሳኝ የልማት አቅም ሆኖ ኃይል አመንጭቶ ወደታችናው ተፋሰስ ጉዞውን ቀጥሏል:: ይህ የዛሬው ስኬት እውነት ስለሆነ፣ መብት ስለሆነ፣ ሳይንሳዊም ስለሆነ፣ ፍትሃዊም ስለሆነ ለዚህ በቅተናል::

በተለያየ መልክ ልዩ ልዩ ትርጉም እየተሰጠው፣ ጥርጣሬ እየተዘራበት ብዙ ፈተናዎችና ውጣ ውረዶች አጋጥመውናል:: ነገር ግን ይሄ የተፈጥሮ ፀጋ ለሁላችንም ይበቃል፤ ዋናው ነገር ለሁላችንም የሚበቃ ፀጋ እስከሆነ ድረስ ተከባብረንና ተማምነን የየድርሻችንን ማበልጸግ መጠቀም ስንችል ነው:: 21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀውም እንዲህ አይነት አሰላለፍንና ተጠቃሚነትን ነው:: አንዱን ያገለለ ለሌላው ብቻ የሆነ ፀጋ አይኖርም::

ኢትዮጵያ በእውነትና በፍትህ በዓለም አደባባይ አቋሟን እያሳወቀች፤ ብዙ ብዥታዎችና ጫናዎች ሲደርሱ የእውነት መንገድን እየጠበቀች እዚህ ደርሳለች:: ዛሬ ያሳካችውም ድል (የዓባይ ኃይል ማመንጨት) የዓባይ የሺህ ዓመታት ጉዞ እንደሚቀጥል ያረጋግጣል:: በአንደኛው ሙሌት የታየው ተግባር ይሄው ነው:: በሁለተኛው ሙሌት የተገኘው ውጤትም ይሄው ተግባር ነው:: ሦስተኛው ሙሌት ዛሬም ስንመለከተው ያንኑ የሚያረጋግጥ ነው::

ከዚህ ባለፈ ለተለያዩ ፍላጎቶች የኢትዮጵያን የፍትህ መንገድ ለመጫን፣ ለማዛባት፣ ወደነበረው ለመመለስ የሚደረጉ ጥረቶች ሁሉ ከእውነት ያፈነገጡ፤ የኢትዮጵያውያንንም መብት የሚጋፉ ስለሆነ ተቀባይነትም፣ ቦታም አይኖረውም:: ነገር ግን ይሄ የተፈጥሮ ፀጋ በተፈጥሮ ሁላችንንም ያስተሳሰረ እንደመሆኑ መጠን ተባብረን፣ ተደማምጠን የበለጠ ሁላችንም እንጠቀምበታለን:: ለዚህ እውነት፣ ለዚህ ሳይንሳዊ መንገድ፣ ለዚህ ፍትህ መሰለፍ፤ ቀሪውን ስራም በተሟላ ስኬት ማረጋገጥ ይጠብቀናል::

እንደ ሕዳሴው ማስተባበሪያ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣ የምክር ቤት አባላት፣ የጽህፈት ቤት አመራሮች፣ ሁላችሁም ባለድርሻ አካላት፣ በውጭ የምትኖሩ የዳያስፖራ አባላት፣ በአገራችን በልዩ ልዩ ሙያ እየተሳተፋችሁ ጊዜያችሁን እውቀታችሁን ለፍትህ ለኢትዮጵያውያን ለዚህ ዘመን ታሪካዊ ስራ የሰራችሁ ሁሉ እጅግ እንኮራባችኋለን፤ እጅግ እናመሰግናችኋለን:: ኢትዮጵያውያን ስንተባበር እንዴት እንደሚያምርብን፤ በልዩ ልዩ ትንንሽ አጀንዳዎች ስንጎዳዳ እንዴት አንገት እንደሚያስደፋ በተግባር እያሳየን ነው::

አሁንም ቢሆን ለበለጠ ጠንካራ አገር ግንባታ በየዘመኑ የተፈተነ፣ ለጠንካራ ኢትዮጵያዊ አንድነትና ጉልበት ወደኋላ የማያየው ሰፊው ሕዝባችን፤ እንዲህ አይነት ድሎችን የበለጠ በማጠንከር ለላቀ ጉዞና ከፍታ ተጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል:: የዛሬዋ ቀን ልዩ ናት ስንል የመጨረሻው ነው ማለታችን አይደለም:: ተጨማሪ ስራዎች አሉን፤ ተጨማሪ ንቅናቄ ያስፈልጋል፤ ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልጋል:: በመጪው ጊዜ በበለጠ ድል ታጅበን ለመጪው ዘመን የምናወርሰው በእኛ ታሪክ የምንኮራበት ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል:: መልካም ጊዜና ዘመን ይሁንልን፤ እጅግ አመሰግናለሁ::

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆአስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ጎዳናን ከመለመኛነት ወደ ስራ ማከናወኛነት እየለወጡ ያሉ ባለሙያ

ግርማ መንግሥቴ

“ፍቅር ፍቅር አሉት ስሙን አሳንሰው ...” እንደተባለው ሁሉ ሕይወትንም ስሙን አሳጥረን “ሕይወት” አልነው እንጂ እንደ ስያሜውና አጠራሩ ቀላል አይደለም። በኑሮ ይገለፅ ከተባለም አልጋ ባልጋ ሆኖ አያውቅም።

ሕይወት ባለ ሕይወቱን የማያደርገው የለም። ያወጣዋል፣ ያወርደዋል፤ ይሾመዋል፣ ይሽረዋል፤ ወዘተርፈ። በመሆኑም፣ “ጥረህ ግረህ በወዝህ ብላ” እንደተባለው ነውና ሕይወትን ለመኖር የሚከፈለው ተገቢ የሆነ ዋጋ ከተገቢነቱ ባለፈ ተገቢ አይደለም በሚል ሲያነታርክ አይታይም። የዛሬዋ እንግዳችን እንደሚነግሩን ከሆነ ግን ተገቢ ባልሆነ ምክንያት ተገቢ ያልሆና ዋጋ እየከፈሉ ነውና ሕይወት ለእሳቸው ከላይ እንደ ገለፅነው አይደለም። እንግዳችንን ዋጋ እያስከፈለ ያለው “ጥረህ ግረህ በወዝህ ብላ” በሚለው የመጽሐፍ ቃል መሰረት ሳይሆን በግፈኞች የግፍ አገዛዝ ምክንያት ነው።

ወይዘሮ ጥሩነሽ ገበየሁ (በተለምዶ ጥሩ) ይባላሉ። ባለትዳርና የአራት ሴት ልጆች እናት ሲሆኑ፣ ነዋሪነታቸው እዚሁ አዲስ አበባ፤ የካ ክፍለ-ከተማ፣ ወረዳ 01 (ቀበሌ 07) ነው።

ወይዘሮ ጥሩን ያገኘናቸው የመሀል አዲስ አበባ ዋና ዋና አደባባዮች ከሆኑት በአንዱ፣ በአራት ኪሎ፣ ድላችን አደባባይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (የተፈጥሮ ሳይንስ) ካምፓስን አጥር ተደግፈው ከሕይወት ጋር ሲታገሉ ነው።

ሕይወት ወደ ጎዳና ያወጣቻቸው፤ የስራ ቦታቸው ጎዳና እንዲሆን የዳረገቻቸው ወይዘሮ ጥሩ ሕይወት ገና ለገና ጎዳና ላይ አውጥታኛለችና እንደ ፈለጋት ታድርገኝ በማለት እራሳቸውን ለችግር አጋልጠው እጃቸውን ለልመና አልዘረጉም። በፎቶግራፋቸው ላይ እንደሚታየው እጃቸው እጥፍ - ዘረጋ እያለ ያለው ለስራ፤ ለዛውም የአገር በቀል እውቀት ውጤት ለሆነው ስፌት ተግባር፤ ለዛውም በአለላ በተንቆጠቆጠ ስፌት ነው።

ፎቶግራፍ ሆኖ እንጂ ተንቀሳቃሽ ምስል ቢሆን ኖሮ አንባቢ ወይዘሮ ጥሩነሽ ገበየሁን አድንቆ፤ በስራቸውም ተገርሞ አያበቃም ነበር። ወይዘሮዋ ብርታታቸው ገና ትኩስ ነው፤ ቅልጥፍናቸው የአራት ልጆች እናት ሊያስመስላቸው ቀርቶ ገና በኮረዳነት እድሜ ላይ ያሉ ነው የሚመስሉት። ያሳለፉት መከራና እንግልት ወደ ውስጣቸው ያሰረፀው ጥንካሬን እንጂ ስንፍናን፤ ምርኮኛነትን አይደለም። ሲሰሩ ፍጥነትና ቅልጥፍናቸው የጉድ የሚያስብል ነው። ሲያወሩ እንኳን እጃቸው ከስራቸው ንቅንቅ አይልም፤ አይናቸውም እንደዛው። ባጭሩ ፈጣሪ ለስራ የፈጠራቸው ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል። ግና ምን ያደርጋል አስቀድመን እንዳልነው ... ግፍ እና የግፍ አገዛዝ እስካለ ድረስ ሕይወትና ሕያዋን ለጉስቁልና ብቻ ሳይሆን ጭራሹንም ለጎዳና ሁሉ ሊዳረጉ ይችላሉና የወይዘሮዋ እጣ-ፈንታም የሆነው እንደዚሁ ነው። ግን እጅ አልሰጡም።


ወይዘሮ ጥሩነሽ ገበየሁ

ከወይዘሮ ጥሩ ጋር ጊዜ ወስደን ብዙ ተጫዋውተናል። የሆዳቸውን ሁሉ ነግረውናል። የደረሰባቸውን ሁሉ አንድም ሳይደብቁ አጫውተውናል። የተፈራረቁባቸውን ችግሮች፤ “ደረሰብኝ” ያሉትን በደል ሁሉ አንድ፣ ሁለት ... በማለት ዘርዝረውልናል (ግማሾቹ ከሕግ ጋር የተገናኙ በመሆናቸው እዚህ ባንጠቅሳቸውም)። ግን ምን ያደርጋል፤ ገፃችን የጋዜጣ ነውና ሁሉንም እዚህ ማስፈር አልቻልንም። በመሆኑም፣ ዋና ዋና በደሎቻቸውና ለጎዳና የዳረጓቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር ጥቂቶቹን ብቻ ይዘን ቀርበናል። ይህንንም፣ እራሳቸው ባለ ታሪኳ “እኔ” እያሉ ይነግሩን ዘንድ ፈቅደናልና እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

የቀድሞው መኖሪያዬ ጎጃም፣ ኑንዴን ወረዳ፣ ሞጣ ጊዮርጊስ አካባቢ ነው። ተወልጄ፣ ተኩዬ የተዳርኩት ... እዛው ነው። ነገር ግን በማህበራዊ ችግር፣ በተለይም በወንድሜ ሞት ምክንያት እዛ መኖርን አልፈለኩም። በመሆኑም በ1998 ኣ.ም መልቀቂያዬን ይዤ ወደዚህ፣ አዲስ አበባ መጣሁ። የካ ክፍለ-ከተማ፣ ወረዳ 01 (ቀበሌ 07)ም በነዋሪነት ተመዝግቤ መኖር ጀመርኩ። በ2007 ዓ.ም የቀበሌ ቤት ተሰጠኝ።

ከዛን ጊዜ ጀምሮ እንደ አንድ ነዋሪም የቀበሌ ቤት ተሰጥቶኝ መኖር ጀመርኩ። በአንድ ግቢ ውስጥ ብዙ ሆነን መኖር ጀመርን። ነገር ግን ይህ የቀበሌ ቤት ውስጥ የመኖሬ ጉዳይ ዘላቂነት ሊኖረው አልቻለም። ከዚህም ከዚያም እንቅፋቶች ገጠሙኝ።

የተሰጠኝ የቀበሌ ቤት መብራት እንኳን የለውም። ጠይቄም ሊገባልኝ አልቻለም። የሚገረመው ይሄ አይደለም፤ መብራት ሳልጠቀም የመብራት ክፈይ የሚለው ነገር መምጣቱ ነው። ያልተጠቀምኩበትን አልከፍልም ስል ያጠራቀምኩትን ብር አስያዙብኝ።

ከዚህ ከቀበሌ ቤት ጋር በተያያዘ የደረሰብኝ በደልና መንገላታት እንዲህ በቀላሉ ተቆጥሮ የሚያልቅ አይደለም። ብዙ ግፍ፣ ብዙ በደል ነው የደረሰብኝ። ይሄንን ሁሉ ግፍና በደል ያደረሱብኝ ሰዎች ናቸው፤ አሁንም አሉ።

እኔ ዜጋ ነኝ። እንደማንኛውም ዜጋ እኩል ልታይ ይገባል እንጂ ይህ ሁሉ በደል ሊደርስብኝ አይገባም። ሰው ሁሉ እኩል ነው። በመጨረሻም ከምኖርበት የቀበሌ ቤት በልማት ተነሺ ስም አፍርሰው አባረሩኝ። የተሰጠኝ ምንም አይነት ምትክ የለም። ይሄው በአሁኑ ሰአት እንደምታዩኝ ነው እየኖርኩ ያለሁት። የደረሰብኝ በደል ብዙ ነው። ቀደም ሲል በልማት ተነሺ ስም ብዙ ጉዳት ደርሷል፡፡

በወቅቱ መብቴን ስጠይቅ የሚመልስልኝ የለም። እንደውም እብድ ነች ተብዬ፣ የመጨረሻዋን ልጄን ነፍሰ ጡር በነበርኩበት ሰአት አማኑኤል ሁሉ በመኪና ጭነው ወስደውኛል። ዶክተሩ ነው ጤነኛ ነች ብሎ እንድመለስ ያደረገኝ። ዶክተሩ ነፃ ባያደርገኝ ኖሮ እንደ እነሱ ቢሆን ኖሮ ... ይሄኔ እኔ እዛ አማኑኤል ነበርኩ።

አሁን በምን አይነት ደረጃ ላይ ነው የምትኖሪው ለሚለው እንጦጦ ማርያም አካባቢ የግለሰብ ቤት በወር 2ሺህ 800 እየከፈልኩ ተከራይቼ ነው የምኖረው።

ልጆቼ ከእኔ ጋር አይደሉም። የመጀመሪያዋ ልጄ አግብታለች። ሌሎቹ አሉ። ከአባታቸውና ዘመዶቻቸው ጋር ናቸው።

የትምህርታቸውስ ነገር ለተባለው በእርዳታና ድጋፍ፤ በትምህርት ቤቶቹ ትብብር ይማሩ ነበር። ደብተርና ስክሪፕቶ የሚባል ነገር አላስብም ነበር። አሁን ያ ስለቀረ ትምህርታቸውን አቋርጠዋል።

ይህንን ስራ በተመለከተ ለጠየከኝ፣ ወደዚህ ስፍራ፣ ጎዳና ከወጣሁ ወደ ሶስት አመት እየሆነኝ ነው። ይህንንም ስራ ስጀምርም እንደዛው። በእርግጥ ከዛ በፊትም ሙያው አለኝ፤ እሰራዋለሁ። እዚህ አዲስ አበባ ከመጣንም በኋላ በአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት (የትኛው ክፍለ-ከተማ እንደሆን አላስታውሰውም) አደራጅቶን መስራት ጀምረን ነበር። ድንገት ሳይታሰብ ግን በተኑን፤ ተበተንን። ዳግም መልሰን ለመደራጀት አስበን አልሆነልንም። እነሱም እንደዛ አይነት ነገር ነበር የነገሩን፤ ተመልሰን እንደምንደራጅ ነበር ተስፋ የሰጡን። ግን አልሆነም። ተበተንን፤ በዛው ቀረን።

በወቅቱ ያደራጀን አካል አያያዙ ጥሩ ነበር። ብር መቆጠብም ጀምረን ነበር። እኔም በሶስት አመት ውስጥ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 5ሺህ 690 ብር መቆጠብ የቻልኩት ያኔ ነው። ደብተሩን አልያዝኩትም እንጂ ማየት ይቻል ነበር። ለአባይ ግድብም የአምስት ሺህ ብር ቦንድ ገዝቻለሁ። በወቅቱ ይህ በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ “እንዴት ልትገዛ ቻለች?” በሚል ይመስለኛል ጥሩ ስሜትን አልፈጠረም ነበር። እኔ ግን አሁንም የመግዛት እድሉን ባገኝ ባለችኝ ገንዘብ ቦንድ ለመግዛት ዝግጁ ነኝ። ለአባይ ግድብ ቦንድ መግዛቴን አላቆምም።

የስራውን አዋጭነት አስመልክተህ ለጠየከኝ ስራው ጥሩ ነው። ምንም አይነት የገበያ ችግር የለበትም። እኔ አንድም ጊዜ ገበያ አጥቼ አላውቅም። በትእዛዝ ነው የምሰራው። እንቅብ (700 ብር ነው) እታዘዛለሁ፤ ሙዳይ (500 ብር) እታዘዛለሁ፤ መሶብ (600 እና 700 ብር ነው) እታዘዛለሁ፤ እሰራለሁ። የሳሎን መሶብ (1ሺህ 300 ብር) እታዘዛለሁ፤ በቀጠሯችን መሰረትም ሰርቼ አስረክባለሁ። ሰዎች እየመጡ የሚፈልጉትን ያዙኛል፤ እሰራላቸዋለሁ። እግዚአብሄር ይመስገን የገበያ ችግር የለብኝም።


አሁን ምን ትፈልጊያለሽ ላልከው እኔ የምፈልገው እንደነከርኩህ የነበርኩበት ቀበሌ መልቀቂያዬን ሰጥቶ እንዲሸኘኝ ብቻ ነው። ሌላው፣ መንግስትንም ሆነ ሌሎችን የምለምነው በዚሁ ሙያ እንዲያደራጀኝ፤ አደራጅቶም (ሳያደራጁኝም በግሌም ቢሆን) ትንሽዬ ቦታ እንዲሰጠኝና እዛ ላይ ህጋዊ ሆኜ እንድሰራ ብቻ ነው። ይሄንን ብቻ ነው የማስቸግረው። የምሰራው ስራ በጣም ፈላጊ ስላለው ይህ ከተደረገልኝ ብዙ እንደምሰራ አውቃለሁ። ለሌሎችም እንደምተርፍ አውቃለሁ። በመሆኑም ይሄንን ብቻ ቢያደርጉልኝ በቂዬ ነው።

ለሌሎች፣ መሰል ሰዎች፣ በተለይም ጎዳናን ለመለመኛነት ብቻ ለሚያውሉት የምትመክሪው ካለ ላልከው፤ አዎ አለኝ። ሰዎች ስንባል ስራ ነው መስራት ያለብን። ያለ ስራ ምንም የለም። በመሆኑም የትም ቦታ ሆነን መስራት እንችላለን። ቦታው ሲመቸን ብቻ አይደለም ስራ መስራት የሚገባን። ሳይመቸን መስራትንም መልመድ አለብን።

መንግስት ይህንን በተመለከተ ሰዎችን እያደራጀ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ አለበት። ቅድም እንደ ነገርኩህ መደራጀት ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ሳናውቀው ባይፈርስ ኖሮ ብዙ ጥቅም እናገኝ ነበር። እ... አልኩህ እኮ ንግድ ባንክ እስከ መቆጠብ ደርሻለሁ እኮ።

መንግስት ጎዳና የወጡትንም ሆነ ሌሎችን አደራጅቶ ነይ ካለኝ ባለኝ ሁሉ ላግዘው ፈቃደኛ ነኝ። ስልጠና ከመስጠትና ልምድን ከማካፈል ጀምሮ ያለኝን፤ የምችለውን ሁሉ ለማድረግ ፍቃደኛ ነኝ። ሌሎችም እንደዚሁ ፍቃደኛ ሊሆኑ ይገባል።

# ስፖርት



# የሊግ ኩባንያው መግለጫ ተቃውሞዎችን እያስተናገደ ነው

ቦጋስ አበበ

በየአራት አመቱ ውዝግብ የማያጣው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የፕሬዚዳንትና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ ዘንድሮም የፊታችን ነሐሴ 22/2014 በጎንደር ለማካሄድ ያቀደው ምርጫ ከውዝግብ አልራቀም። የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከሳምንት በፊት እጩ ተወዳዳሪዎችን ይፋ ካደረገ ወዲህ የተለያዩ ውዝግቦች እየተነሱ ይገኛሉ። በተለይም የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው በጠቅላላ ጉባኤ በጸደቀው የምርጫ ህግና ደንብ መሰረት ማንኛውም አካል ለመገናኛ ብዙሃን መግለጫ እንዳይሰጥ ማሳሰቡን የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህን ወደ ጎን ትቶ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማህበር ሰሞኑን በምርጫው ዙሪያ መግለጫ በመስጠቱ በተለያዩ አካላት መካከል ሽኩቻው ጦፏል። የሊግ ኩባንያው መግለጫ ለመስጠት የተነሳበት ዋነኛ ምክንያት በፌዴሬሽኑ በኩል የሚስተዋሉ ችግሮች ወደ ሊጉ እንዳይመጡ በማሰብ መሆኑን የገለጸ ሲሆን፤ ችግሮች ያላቸውን ነጥቦችም በዝርዝር አስቀምጧል። የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ከፊፋ ህግ ውጪ ተመርጧል በሚል ኮንኗል።

ሊግ ኩባንያው መግለጫ ለመስጠት በቦርድ ደረጃ መወሰኑ ከውድድር ውጪ በፌዴሬሽኑ ኃላፊነት ላይ ጣልቃ መግባቱን እንደሚያሳይ ፌዴሬሽኑ መግለጹ የሚታወስ ሲሆን፣ የሊግ ኩባንያው የንግድ ስራ ድርጅት የሚሰራ ተቋም ሆኖ የጠቅላላ ጉባኤ አባል ሳይሆን ስለ ጉባኤውና ምርጫው ማውራት ተገቢ እንዳልሆነም ተቃውሞውን ገልጿል። የሊግ ኩባንያውን አካሄድ ከፌዴሬሽኑ በተጨማሪ ከ16ቱ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማህበር አባል ክለቦች አንዱ የሆነው ቅዱስ ጊዮርጊስ የሊግ ኩባንያውን መግለጫ በይፋ ተቃውሟል።

ክለቡ ጉዳዩን በተመለከተ ለአክሲዮን ማህበሩ




ከትናንት በስቲያ በላከው ደብዳቤ የኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን የፕሬዚዳንታዊና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫን በተመለከተ የሰጠውን መግለጫ መከታተሉን በመግለጽ ማህበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ፣ ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የሰጠው መግለጫ ተገቢነት ያለው ሆኖ እንዳላገኘው ገልጿል።

"ምርጫው ሀገራዊ ጉዳይ እንደመሆኑ አክሲዮን ማህበሩ ባለድርሻ የሆኑትን 16ቱን ክለቦች ጠርቶ ማወያየት ይገባው ነበር" ያለው የቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ፣ መግለጫው ምርጫው በፍትሀዊነት እንዳይካሄድ ተጽዕኖ እንዳይፈጥር ስጋት እንደገባው ጠቁሞ ፤ እንደ ክለብ የተሰጠውን መግለጫ አንቀበልም" ብሏል። ከሊግ ኩባንያው መግለጫ በፊት ወልቂጤ ከተማ፣ ሀድያ ሆሳዕና፣ አዳማ ከተማና ሰበታ ከተማ ተመሳሳይ ተቃውሞ ማቅረባቸው ታውቋል።

የደቡብና ኦሮሚያ ክልሎች የእግርኳስ ፌዴሬሽኖችም ለኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን በላኩት ደብዳቤ የሊግ ኩባንያውን መግለጫ ተቃውመዋል። "የአክሲዮን ማህበሩ ለሀገሪቱ እግርኳስ ዕድገትና ልማት ይሰራል ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን የክለቦችን አቅም ከመፍጠር አንጻር የሚጠበቅና የጀመረውን ስራ ይቀጥላል ቢባልም በማይመለከተው ጉዳይ ላይ ገብቷል" ሲል የደቡብ ክልል እግር ኳስ ፌዴሬሽን ገልጿል።

የክልሉ ፌዴሬሽን ለብሄራዊ ፌዴሬሽኑ በሰጠው ማሳሰቢያም "ብሄራዊ ፌዴሬሽኑ ለአክሲዮን ማህበሩ ከመግለጫው በፊት በሰጠው ማሳሰቢያ መሠረት በህግ እንዲይዘውና ውጤቱን እንዲያሳውቀን እናሳስባለን" በማለት የያዘውን ጠንካራ የተቃውሞ አቋም ይፋ አድርጓል።

በተመሳሳይ የኦሮሚያ እግርኳስ ፌዴሬሽንም አክሲዮን ማህበሩ በፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንታዊና የስራ አስፈጻሚ ምርጫን አስመልክቶ የሰጠውን መግለጫ የማይመለከተው ነው ሲል ኮንኗል። ፌዴሬሽኑ ለብሄራዊ ፌዴሬሽኑ በላከው ደብዳቤ "አክሲዮን ማህበሩ የሰጠው መግለጫ የማይመለከተውና የስፖርት ቤተሰቡን ለማደናገርና የተዛባ ግንዛቤ እንዲይዝ የሚያደርግ ነው" ብሏል። ፌዴሬሽኑ አክሲዮን ማህበሩ ካሳየው ሀላፊነት የጎደለው ተግባሩ እንዲታቀብ ጠይቆ "ፌዴሬሽኑና የኢትዮጵያ ህዝብን በመገናኛ ብዙሀን ይቅርታ እንዲጠይቅ ብሄራዊ ፌዴሬሽኑም አስተማሪ የሆነ ርምጃ መውሰድ እንዳለበት የክልሉ እግርኳስ ፌዴሬሽን በጽኑ ያምናል" ብሏል።

በሊግ ኩባንያው ቅሬታ የቀረበበት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴም ጉዳዩን በተመለከተ ከትናንት በስቲያ መግለጫ አውጥቷል። ሰሞኑን በምርጫው ሂደትና በአስመራጮቹ አግባብነት ዙሪያ ለተነሱበት ጥያቄዎችም ምላሽ ሰጥቷል።

ግንቦት 7 ቀን 2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠው የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከሰኔ 15 ቀን 2014 ዓ.ም አንስቶ ሥራውን በመጀመር ነሀሴ 22 ቀን 2014 ዓ.ም በጎንደር ከተማ ለሚደረገው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የፕሬዝዳንትነትና የሥራ አስፈፃሚ አባልነት ለሚደረገው ምርጫ ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ የገለጸው ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው፣ ሥራው ሲጀመር የድርጊት መረሃ-ግብር ነድፎና አባላቱ የሚመሩበትን የስነ-ምግባር ደንብ አድድቆ መሆኑን ጠቁሟል። የምርጫ ኮሚቴው ባለፉት 50 ቀናት የዕጩዎች ምዝገባን በማጠናቀቅ ተገቢነታቸው ላይም ውሳኔ በመስጠት ዝርዝራቸውን ለሕዝብ ይፋ አድርጓል፡፡

በምርጫ ኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ወገኖች የምርጫ ደንቡ በሚያዘው መሠረት አቤቱታቸውን ለምርጫ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አቅርበው አቤቱታቸው እየተመረመረ እንደሚገኝም በመግለጫው አስቀምጧል።

ይሁን እንጂ አንዳንድ አካላት የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም የምርጫ ኮሚቴው ላይ ብሎም ምርጫው ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር በመሞከር ላይ እንደሚገኙ አሳውቋል። ይህም እጅግ አሳዛኝ ተግባር መሆኑን ጠቁሞ፣ በፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ ተግባሩን በደንብና መመሪያ መሰረት በአግባቡ እየተወጣ ያለውን የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ላይ ውጫዊ ተፅዕኖ ለመፍጠር የታቀደ ድርጊት መሆኑን ኮሚቴው እንደተገነዘበ አስረድቷል። "ይህ በኮሚቴው አባላት ላይ የተጀመረው የስም ማጥፋት ዘመቻ ኮሚቴውን ለአንዲት ሰከንድም ቢሆን ተግባሩን እንዳይወጣ እንደማያደርገው እናረጋግጥላችኋለን" ሲልም ምላሽ ሰጥቷል፡፡

በተለይም የምርጫው ጉዳይ የማይመለከታቸውና የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ያልሆኑ በተለያየ የመገናኛ ዘዴዎች የምርጫውን ተአማኒነት ለማሳጣት እያደረጉ ያለውን እንቅስቃሴ ሕጋዊ መስመሩን ተከትለው እንዲቆም ለማስደረግ ተገቢውን ጥረት እንደሚያደርግ የገለጸው ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው፤ የጠቅላላ ጉባኤው በሰጠው ከፍተኛ ኃላፊነት ምርጫውን በታቀደለት ዕለት ለማካሄድ አስፈላጊውን መሰናዶ እያደረገ መሆኑን አሳውቋል።


## የንግድ ምልክት ምዝገባ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የአመልካች ስምና አድራሻ | ኤምቲኤን ግሩፕ ማኔጅመንት ሰርቪስስ (ፕሮፕራይተሪ) ሊሚትድ MTN GROUP MANAGEMENT SERVICES (PROPRIETARY) LIMITED<br>216 – 14th Avenue, Fairland Roodepoort, Gauteng South Africa |
| 2. | ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀንና ቁጥር | 01/10/2019 እአአ FTM/11036/19 |
| 3. | የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ | የምስል እና የቃል |
| 4. | የንግድ ምልክቱ | MTN |
| 5. | ዓለም አቀፍ ምድብ | 09 እና 38 |
| 6. | ቀለማት | ቢጫ፣ ሰማያዊ፣ ነጭ እና ቀይ |

**ማመልከቻቸው የሚሸፍናቸው ምርቶች እና አገልግሎቶች፡-**

ምድብ 09፡ ኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክ አፓራተሶች፤ የቴሌኮሙኒኬሽን አፓራተስ ሞባይል (ሴሉላር) ስልኮችን እና መሳሪያዎችን ጨምሮ፤ የኮምፒዩተር ሃርድዌር፤ የኮምፒዩተር ሶፍትዌር ፕሮግራሞች፤ የኤሌክትሮኒክ እና የኮምፒዩተር ጨዋታዎች፤ የቪዲዮ ጨዋታዎች፤ የኮምፒዩተር መዝናኛ እና ኮሙኒኬሽን ሶፍትዌር እና አፓራተስ፤ በኮምፒዩተር እና/ወይም በሞባይል (በሴሉላር) ስልኮች እና መሳሪያዎች ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚረዳ አፓራተስ እና ሶፍትዌር፤ ለመቅዳት፣ ለማጠራቀም (ለማከማቸት)፣ ለመቀበል፣ ለማሰራጨት፣ ለማስተላለፍ ወይም ድምፅን፣ ምስሎችን ወይም ዳታን ለማባዛት (ዲጂታል እና አናሎግ ዳታን ጨምሮ) የሚረዳ አፓራተስ፤ በኤሌክትሮኒክ መልክ ያለ ኢንፎርሜሽን እና ዳታ፤ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስርጭት እና መቀበያ አፓራተሶች፤ የቴሌማቲክ አፓራተስ፤ ተሽከርካሪዎችን፣ ሰዎችን እና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ዕቃዎችን በርቀት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር፣ መገኛ ቦታቸውን ለመከታተል የሚረዳ የኤሌክትሮኒክ አፓራተስ፤ ለናቪጌሽን (ለአሰሳ) የሚረዳ አፓራተስ፤ ኮምፒዩተር ፕሮግራሞች፣ የሙዚቃ አፕሊኬሽኖች፣ ምስሎች እና በኢንተርኔት እና ወይም በሞባይል (በሴሉላር) ስልኮች እና ዲቫይሶች ሙዚቃን፣ ምስሎችን እና ዳውንሎድ መደረግ የሚችሉ የኤሌክትሮኒክ ዳታ፤ ስማርት ካርዶች፣ ሲም ካርዶች፣ ማይክሮቺፖች፤ ሞደሞች እና የኢንተርኔት ራውተሮች፤ የኢንተርኔት ሰርች ኢንጂኖች እና ብራውዘሮች (መፈለጊያዎች)፤ ድምፅ መለያ አፓራተሶች እና ሶፍትዌር፤ ቀደም ሲል ለተጠቀሱት ዕቃዎች የሚውሉ ክፍሎች፣ አካሎች፣ መገጣጠሚያዎች እና መለዋወጫዎች ምድብ 38፡ የመገናኛ እና ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች የድምፅ እና የቪዲዮ ጥሪዎች፣ የኮንፍረንስ ስልክ ጥሪዎች (ኮንፈረንስ ኮልስ)፣ ዓለም-አቀፍ የስልክ ዝውውር (ኢንተርናሽናል ቴሌፎን ሮሚንግ)፣ ቪኦአይፒ (ቮይስ ኦቨር ኢንተርኔት ፕሮቶኮል)፣ ኤሌክትሮኒክ መልዕክት፣ የፅሁፍ እና መልቲሚዲያ መልዕክቶች፣ የድምፅ መልዕክት፣ የቪዲዮ መልዕክት እና የፋክስ መልዕክትን ጨምሮ፤ የኢንተርኔት እና የሞባይል (የሴሉላር) ስልክ አገልግሎት አቅራቢዎች፤ በኮምፒዩተሮች፣ በሞባይል (በሴሉላር) ስልኮች እና በዲቫይሶች፣ በኮምፒዩተር ኔትዎርኮች እና በኢንተርኔት አማካኝነት መረጃ፣ መልዕክትና ምስሎች የሚተላለፉበት የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶች፤ ስልክ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) እና የሴሉላር ስልክ መገናኛ አገልግሎቶችን ጨምሮ፣ በሳተላይት የሚደረግ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች፤ የቴሌኮሙኒኬሽን እና ኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢዎች፤ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የአየር ሰዓት አቅርቦት እና በድጋሚ መሙላት (ሪቻርጂንግ)፤ ቴሌኮሙኒኬሽን መልቲሚዲያ አገልግሎቶች፤ የቴሌማቲክ አገልግሎቶች፤ በቴሌኮሙኒኬሽን አፓራተስ አማካኝነት ተሽከርካሪዎችን፣ ሰዎችን እና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ዕቃዎችን በርቀት መቆጣጠር፣ ቁጥጥር ማድረግ፣ መገኛ ቦታቸውን መከታተል፤ ኤም-ፖርታልስ (ማህበረሰቡ በገመድ አልባ መሳሪያ እንዲጠቀም የሚያስችሉ መተግበሪያዎች እና የይዘት ክምችቶች)፤ የኢንተርኔት እና የሞባይል ፖርታሎችን የሚያካትቱ ፖርታሎች የአገልግሎት አቅርቦቶች፤ ምርቶች እና የሞባይል ቴሌኮሙኒኬሽን ይዘቶች፣ ቋሚ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር እና የደብሊው ኤፒ፣ የኤስኤምኤስ፣ የዩኤስኤስዲ ወይም የደብሊውአይጂ አገልግሎት አቅርቦቶችን የሚያካትት የኢንተርኔት አካባቢ እና የድምፅ መለያ አገልግሎቶች፤ መረጃን፣ መልዕክቶችን፣ ድምፆችን፣ ሙዚቃን፣ ምስሎችን፣ ዳታን፣ የስልክ መጥሪያዎችን እና አርማዎችን በኮምፒዩተር እና በሞባይል (በሴሉላር) ስልኮች ማስተላለፍ፤ ለግሎባል ኮምፒዩተር ወይም ለቴሌኮሙኒኬሽኖች ኔትወርክ የተጠቃሚ ተደራሽነት፣ ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች እና ግንኙነቶች አቅርቦት፤ የስርጭት አገልግሎቶች፤ ቀደም ሲል ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ የሚደረጉ የማማከር፣ የመረጃ እና የምክር አገልግሎቶች ናቸው።

አመልካች ኤምቲኤን ግሩፕ ማኔጅመንት ሰርቪስስ (ፕሮፕራይተሪ) ሊሚትድ (MTN GROUP MANAGEMENT SERVICES (PROPRIETARY) LIMITED) ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዘገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ለምዝገባው ተቃዋሚ ካለ ይህ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይባ የሚስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ካልቀረበ በስተቀር ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN Vol. LXXXI No. 337- 7/12/2014 (13/8/2022)